የሉቃስ ወንጌል መክፈቻ

ለመሠረታዊ ደረጃ

አንደኛ ዓመት

1ኛ ዕትም ሰኔ 1977 ዓ.ም.

ማ ው ጫ ገጽ

ክርስቶስ ተወልዶ አደገ 4

ጌታ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት 16

ጌታ ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን መረ 32

ሁለተኛ ጉዞ 36

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት 52

ሐዋርያቱን ብዙ አስተማረ 57

ማስጠንቀቂያዎች 62

ሰዎች መናዘዝ አለባቸው 67

የጠፋ በግ 75

የመጨረሻው ሳምንት 95

ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ 126

የሉቃስ ወንጌል ትምህርት 132

መ ቅ ድ ም

መክፈቻ የተሰኙት መጻሕፍት በተለይም መጽሐፍ ቅዱስን ገና ላልተማሩት ሰዎች የተቀናበሩ ናቸው። የመጻሕፍት ዋና ዓላማ የየመጽሐፉን ይዘት በአጭሩ መግለጥ ነው። በመሆኑም ዓላማው እንደ ጥናት፥ ማብራሪያ ወይም ትርጓሜ አይደለም። ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ቃል የመክፈት ዓላማ ስላለው ተማሪዎች የተለያዩትን ትምህርቶች ሳያጠኑ እንደሚያልፉ የታወቀ ነው፤ መጽሐፉ እያንዳንዱን አንቀጽ ለማብራራት አይሞክርም፤ የታሪኩን አሻሚ ክፍሎችን በሙሉ ለመተርጉም ዓላማው አይደለም። ነገር ግን ተማሪዎች በዚህ መክፈቻ ተመርኩዘው ሲያጠኑ የእግዚአብሔርን ቃል ሲያነቡ ይረዱታል። በግልጽና በደስታ ሊያስተምሩት ይችላሉ።

አዘጋጂዎች

የሉቃስ ወንጌል መክፈቻ

ሉቃስ ሁለት ታላላቅ መጻሕፍትን ጽፎአል። የሉቃስ ወንጌል ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ይናገራል፤ የሐዋርያት ሥራ ስለ ቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ታሪክ ያቀርብልናል። ሉቃስ የሐዋርያው ጳውሎስ የቅርብ ጓደኛ ነበር። እነርሱንም በአንድ ላይ እንደነበሩ በመጀመሪያ በሐዋርያት ሥራ እንመለከታለን፤ የሐዋ.ሥራ 16፡10-11። በሐዋርያት ሥራ መጀመሪያ ምዕራፎች ላይ ሉቃስ ስለ ጴጥሮስና ጳውሎስ እንዲሁም ስለ ሌሎች ጽፎአል፤ ምዕ.1-15። እርሱም ሁልጊዜ፥ «እርሱ እንዲህ አደረገ» ወይም «እነርሱ ወደዚያ ሄዱ» ይል ነበር። ሉቃስ በ16፡10 ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ «እኛ» የሚል ቃል ተጠቀመ። ሉቃስ የራሱን ስም ጠቅሶ አያውቅም፤ ነገር ግን «እኛ» የሚለው ቃል ሉቃስ ከጳውሎስ ጋራ በጢሮአስ እንደነበር ያመለክታል።

ሉቃስ ከጳውሎስ ጋራ ወደ ፊልጵስዩስ ሄደ፤ ከዚያም ለጥቂት ዓመታት ቆየ። ጳውሎስ እንደገና ተመልሶ በፊልጵስዩስ አገኘው፤ የሐዋ.ሥራ 20፡6። ሉቃስ ጳውሎስ እስረኛ ወደሆነበት ወደ ኢየሩሳሌም አብሮት ሄደ። ጳውሎስ በሰንሰለት እንደታሠረ ወደ ሮም ሲሄድ ሉቃስም ወደዚያው ሄደ፤ የሐዋ. 28፡16። ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ሆኖ አራት ደብዳቤዎችን ወደ ኤፌሶን ሰዎች፥ ፊልጵስዩስ፥ ቆላስያስና ፊልሞና ጻፈ። ከእነዚህ በሁለቱ ስለ ሉቃስ ጽፎአል፤ ቆላ.4፡14፤ ፊልሞና 24። በኋላም ጳውሎስ ተመልሶ ወደ እስር በገባ ጊዜ ሉቃስ ብቻ ከእርሱ ጋር ቆየ፤ 2ጢሞ.4፡11።

ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው ሉቃስ ሐኪምና ከአሕዛብም ወገን እንደነበረ ነው።

ከጳውሎስ ጋር አብረው በተጓዙበት ወቅት ሉቃስ በጣም ረድቶታል። ጳውሎስም በጣም ወደደው። እነዚህንም ሁለት ሰዎች ከግማሽ በላይ የሆነውን የአዲስ ኪዳን ክፍል እንዲጽፉ መንፈስ ቅዱስ መራቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ በጠቅላላው 66 መጻሕፍት አሉት፤ በአዲስና በብሉይ ኪዳን። ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሰውን እንደፈጠረና ሰውም በኃጢአት እንደወደቀ ይነግረናል። ሰዎችንም ከኃጢአታቸው የሚያድን አዳኝ አንድ ቀን እንደሚመጣ እግዚአብሔር ቃል ገባ። አብዛኛውን የብሉይ ኪዳን ክፍል ስለ አብርሃም ዘሮች ስለሆኑት ስለ እስራኤል ሕዝቦች ይናገራል። በእግዚአብሔር የሚታመኑት እስራኤላውያን የሚመጣውን አዳኝ ይጠባበቁ ነበር።

አዲስ ኪዳን አዳኝ መምጣቱን ያሳየናል። በአራቱ ወንጌሎች ስለ ጌታ ኢየሱስ ሕይወትና ሞት እናነባለን። ስለ ቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ሥራ እናነባለን። አዲስ ኪዳን፥ ጳውሎስ፥ ጴጥሮስ፥ ያዕቆብ፥ ዮሐንስና ይሁዳ በዚያን ጊዜ ለነበሩት ቤተ ክርስቲያናት ወይም ክርስቲያኖች የጻፉአቸውን 21 ደብዳቤዎች ይዟል። የዮሐንስ ራዕይ ደግሞ ወደፊት ጌታ ተመልሶ ሰዎችን እንደሚባርክ ያስረዳናል።

እግዚአብሔር ሰዎችን ሊባርክ ይፈልጋል፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያ መጥቶ ስለ ኃጢአታችን መሞት ነበረበት። አራቱ ወንጌሎች የእግዚአብሔር

ጠቅላላ ግዕከላዊ ራዕይ እንደሆኑ ትመለከታለህ። ብሉይ ኪዳን የክርስቶስን መምጣት ይጠባበቃል። ማንኛውም ነገር ያለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊሆን አይችልም።

መንፈስ ቅዱስ እነዚህን አራት ወንጌሎች ለምን ሰጠን? ምክንያቱም ሌላ ማንኛውም መጽሐፍ ስለ አስደናቂው አዳኛችን የተሟላ እውነት ስለማይገልጽልን ነው። በብሉይ ኪዳንም እንኳ ስለ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ታሪክ፡- በዘፀአት፥ ዘሌዋውያን፥ ዘኍልቁና በዘዳግም ውስጥ እናገኛለን። የይሁዳ ንጉሥ ታሪክ በሳሙኤል፥ በመጽሐፈ ነገሥትና በመጽሐፈ ዜና ይገኛል፤ ታሪኩ ሁለት ጊዜ ተጽፏል ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ልጅ ወደዚህች ዓለም እንደ ሕፃን መጥቶ አደገ። ስለ እግዚአብሔር በምናስብበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ የእርሱ አገልጋይ እንደነበር ነው። ለእስራኤል ሕዝቦች ንጉሣቸው ሆኖ መጣ። ማቴዎስ ጌታን የይሁዳ ንጉሥ መሆኑን ያመለክታል፤ ማርቆስ ደግሞ የእግዚአብሔር አገልጋይ ይለዋል። ሉቃስ ሲጽፍ ቅዱሱ ሰው ሲለው ዮሐንስ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ይነግረናል። አራቱም ወንጌሎች አስፈላጊ መሆናቸውን ትመለከታለህ። ሁሉም ስለ ጌታ አንድ ዓይነት ነገር አልጻፉም። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ሁለት የተለያዩ ታሪኮች እንዴት እውነት ይሆናሉ ብለው ይገረማሉ። መንፈስ ቅዱስ እነዚህን የአራት ወንጌሎች ጸሐፊዎች ትክክል ያልሆነ ነገር እንዲጽፉ ያላደረገ ለመሆኑ እርግጠኞች እንሆናለን።

ማቴዎስ፥ ማርቆስና ዮሐንስ ይሁዳውያን ነበሩ፤ ሉቃስ ግን ከአሕዛብ ወገን ነበረ። እርሱም ክርስቶስ ይሁዳውያንን ብቻ ላይሆን ሰዎችን ሁሉ ለማዳን ስለመጣ ደስ ይለው ነበር። ሉቃስ ሦስተኛውን ወንጌል በሚጽፍበት ጊዜ ጌታ የዓለም አዳኝ እንደሆነ ያመለክታል።

የሉቃስ ወንጌል

የሉቃስ ወንጌል 24 ምዕራፎች አሉት፤ ጠቅላላ መጽሐፉን ለመረዳት ሰባት ነጥቦችን ማስታወስ ያስፈልጋል።

1ኛ) ክርስቶስ ተወልዶ አደገ፤ ምዕራፍ 1 እና 2።

1. ዮሐንስ እንደሚወለድ የተናገረው ቃል፤ 1፡1-25
2. ጌታ ኢየሱስ እንደሚወለድ ገብርኤል የገባው ቃል፤ 1፡26-56
3. ዮሐንስ ተወለደ፤ 1፡57-80
4. ጌታ ኢየሱስ ተወለደ፤ 2፡1-21
5. ማሪያምና ዮሴፍ ሕፃኑን ኢየሱስን ወደ ቤተ መቅደስ አመጡ፤ 2፡22-40
6. ጌታ ኢየሱስ በ12 ዓመቱ፤ 2፡41-52።

2ኛ) ጌታ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት፤ 3፡1-4፡13።

1. ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስን አጠመቀው፤ 3፡1-22

2. የማሪያም የዘር ሐረግ፤ 3:23-38

3. ሰይጣን ጌታን ፈተነው፤ 4:1-13።

3ኛ) የጌታ ሥራና ትምህርት በገሊላ፤ 4:14-9:62።

1. የመጀመሪያ ጉዞ፤ 4:14-6:49

2. ሁለተኛ ጉዞ፤ 7:1-8:56

3. ጌታ 12 ሐዋርያቱን ላከ፤ 9:1-9

4. ጌታ አምስት ሺህ ሰዎችን መገበ፤ 9:10-17

5. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ጴጥሮስ መሰከረ፤ 9:18-27

6. ጌታ በክብር ተገለጠ፤ 9:28-50

7. ጌታ ከገሊላ ለመጨረሻ ጊዜ ወጣ፤ 9:51-62።

4ኛ) የጌታ ትምህርት ከዮርዳኖስ ማዶ፤ 10:1-19:27።

አሥራ ሁለት ምሳሌዎች

1. ርህሩሁ ሳምራዊ፤ 10:25-37

2. ጥያቄ አቅራቢው ወዳጅ፤ 11:1-13

3. የሀብታሙ ሰው ሞኝነት፤ 12:13-21

4. የበለስ ዛፍ ምሳሌ፤ 13:6-9

5. የሰናፍጭ ዘር ምሳሌ፤ 13:18-19

6. የእርሾው ምሳሌ፤ 13:20-21

7. የታላቁ ግብዣ ምሳሌ፤ 14:15-24

8. ጠፍቶ የተገኘው በግ፥ የወርቅ መሃለቅና ልጅ፤ 15:1-32

9. ብልህ መጋቢ፤ 16:1-9

10. አመፀኛው ዳኛ፤ 18:1-8

11. ትዕቢተኛው ፈሪሳዊና ትሑቱ ቀራጭ፤ 18:9-14

12. የአሥሩ አገልጋዮች ምሳሌ፤ 19:11-27

5ኛ) የመጨረሻው ሳምንት፤ 19:28-22:53።

1. ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ፤ 19:28-48

2. የጌታ ጠላቶች፤ 20:1-47

3. ጌታ ስለ ወደፊቱ ነገር ተናገረ፤ 21:1-38

4. ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ለመስጠት ተስማማ፤ 22:1-6

5. የመጨረሻው እራት፤ 22፡7-38

6. ጌታ ኢየሱስ ወደ አባቱ ጸለየ፤ 22፡39-46

7. ይሁዳዊያን ጌታን ያዙት፤ 22፡47-53

6ኛ) ክርስቶስ በመስቀል ላይ በምስማር ተቸነከረ፤ 22፡54-23፡56

1. ኢየሱስ ተፈረደበት፤ 22፡54-23፡25

2. ኢየሱስ ተሰቀለ፤ 23፡26-49

3. ኢየሱስ ተቀበረ፤ 23፡50-56

7ኛ) ጌታ ኢየሱስ ከሞት ተነሣ፤ ምዕራፍ 24

ክርስቶስ ተወልዶ አደገ ምዕራፍ 1 እና 2

የሉቃስን ወንጌል በምናነብበት ጊዜ የጌታ ኢየሱስን ክብር እንመልከት፤ በዚህም የበለጠ እንድንወደውና እንድናገለግለው ይረዳናል። በሉቃስ ወንጌል የንጹሑን ሰው ክብር ለማንበብ አንቸገርም። በመጀመሪያው ሉቃስ ቴዎፍሎስ ለተባለው ሰው እንደጻፈ እናነባለን፤ 1፡1-4። ከሉቃስ ሌላ ብዙዎች ስለ ጌታ ኢየሱስ ታሪክ ጽፈዋል። ከእነዚህም ውስጥ እውነቱን ጽፈው ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ መርቶአቸው ስለ ጌታችን የሕይወት ታሪክ የጻፉ አራት ሰዎች ብቻ ናቸው። እነዚህ ጽሑፎች ከሌሎች 65 መጻሕፍት ጋር እስከ ዛሬ ድረስ ለእኛ ተቀምጠዋል። በዓለም ሌሎች የቆዩ ብዙ መጻሕፍት አሉ። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፉት እነዚሁ 66 መጻሕፍት ብቻ ናቸው። ሉቃስ በነበረበት ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ስለ ጌታ ኢየሱስ እውነት ያልሆነ ጽፈዋል። አሁንም ተመሳሳይ እውነት ያልሆኑ ይጽፋሉ። አንዳንድ ብልህ የሚመስሉ ሰዎችም እውነት ያልሆኑ ነገሮችን ይጽፋሉ። ስለ እውነትነቱ እርግጠኞች ልንሆን የምንችለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ሉቃስ ስለ ጌታ ኢየሱስ መረጃዎችን ያገኘው ኢየሱስን ካዩትና ትምህርቱንም ካዳመጡት ሰዎች ነው። ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አላቸው፤ ሉቃ.24፡48፤ የሐዋ.1፡8። ሉቃስ ራሱ ጌታ ኢየሱስን አላየውም፤ ትምህርቱንም አልሰማም። መንፈስ ቅዱስ ግን ስለ ጌታ ኢየሱስ እውነቱን ብቻ እንዲጽፍ መራው።

ቴዎፍሎስ ማን እንደነበረ አናውቅም። ሉቃስ ግን «የተከበረ ቴዎፍሎስ» ይለዋል፤ ቁጥር 3። በዚህም ቴዎፍሎስ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን እንደነበረ እንገምታለን። ሉቃስ ሌላ መጽሐፍ ለቴዎፍሎስ ጽፎአል፤ የሐዋ.ሥራ 1፡1። ቴዎፍሎስ የሚለው ስም «እግዚአብሔርን የሚወድ» ማለት ነው። አንተም እግዚአብሔርን ብትወድ የሉቃስ ወንጌል ላንተም ነው። ቴዎፍሎስ የሚለው ስም ይሁዳዊ ሳይሆን የግሪክ ነው። እርሱም እውነትን ለማወቅ የሚሹትን ሰዎች ሁሉ ይወክላል።

ዛሬም በእጃችን ባለው በእግዚአብሔር ቃል እውነቱን ለማወቅ እንችላለን፤ ዮሐ.8፡32። መንፈስ ቅዱስ እውነትን እንድንገዛት እንጂ እንዳንሸጣት ያሳስበናል፤

ምሳ.23:23። ጌታ ኢየሱስ ግንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ቢያደርግ እውነትን ያውቃል ብሎ አስተማረ፤ ዮሐ.7:17፤ 8:32።

1. አጥማቂው ዮሐንስ እንደሚወለድ የተነገረው ቃል፤ 1:5-25

ስለ አጥማቂው ዮሐንስ አባት ዘካሪያስ ስለሚባለው ቁስ እናነባለን። እርሱም በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ይኖር ነበር። ሄሮድስም ጌታ ኢየሱስ ሕፃን በነበረበት ጊዜ ሊገድለው ሞከረ፤ ማቴ.2:16። ሌላው ሄሮድስ የአጥማቂው ዮሐንስን አንገት ቆረጠ፤ ማቴ.14:10። እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ ለፍርድ በቀረበበት ጊዜ ሳቀበት፤ ሉቃ.23:11። አሁንም ሌላው ሄሮድስ ሐዋርያው ያዕቆብን አንገት ቆረጠ፤ የሐዋ.12:2። በዚህ ምዕራፍ ሄሮድስ የእስራኤል ንጉሥ ነበር። እግዚአብሔር ግን አልመረጠውም ነበር። ሄሮድስ ይሁዳዊ እንኳ አልነበረም። ሥልጣኑን ያገኘው ግን በዚያን ዘመን ዓለምን ይገዙ የነበሩትን የሮም ነገሥታት በማስደሰት ነበር። የሉቃስ ወንጌል ስለሚመጣው እውነተኛ የእስራኤል ንጉሥ ይናገራል።

በብሉይ ኪዳን ጊዜ እውነተኛ የእስራኤል ቁሳውስት ሁሉም የአሮን ልጆች ወይም ዘሮች ነበሩ። ንጉሥ ዳዊት ቁሳውስትን በ24 ቡድን ከፈላቸው። አንዱ የቁሳውስት ቡድን በአንድ ጊዜ በቤተ መቅደሱ ያገለግላል። ዘካሪያስ በስምንተኛው ቡድን ውስጥ ነበር፤ 1ዜና 24:10። ዘካሪያስ ከካህኑ ከአሮን ዘር የነበረችውን ኤልሳቤጥን አገባ፤ 1:5። ዘካሪያስና ኤልሳቤጥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያከብሩ ነበር፤ ይህ ግን ያለ ኃጢአት ነበሩ ማለት አይደለም። ያለ ኃጢአት የነበረ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነበር፤ ሮሜ 3:10፤ 1ጴጥ.2:22። ዘካሪያስና ኤልሳቤጥ ጥሩ ኑሮ ነበራቸው። እግዚአብሔር ግን አንድም ልጅ አልሰጣቸውም፤ ቁ.7። በጣም ስላረጁ እግይወልዱበት ደረጃ ላይ ደረሱ። የአብርሃምና የሣራን ታሪክ አስታውሰው እግዚአብሔር ችሎታ እንዳለው አወቁ፤ ዘፍ.18:11፤ 21:1-2:5። ይስሐቅና ርብቃም ልጅ እንዲያገኙ ጸለዩ፤ ዘፍ.25:21። የእግዚአብሔር ፈቃድ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ የግኑሄ ባለቤት ልጅ አልነበራትም፤ መሳ.13:2-3።

እግዚአብሔርን ለማስደሰት የእርሱን ፈቃድ መፈጸም አለብን። የእግዚአብሔርን ፍቅር የምናውቅ ከሆነ ለጸሎታችን መልስ ባይሰጠንም እንኳ በእርሱ እንተማመናለን።

ዘካሪያስ ወደ ቅዱሱ ቦታ ገብቶ ዕጣን ማጠን ነበረበት፤ ምዕ.1:8-9። በእስራኤል ድንኳንና ቤተ መቅደስ ሁለት ክፍሎች ነበሩ። እነርሱም ቅድስትና ቅድስተ ቅዱሳን ናቸው። ከቁስ በስተቀር ወደ ቅድስት ማንም ሊገባ አይችልም። ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ሊገባ የሚችለው ሊቀ ካህኑ ብቻ ነው። የሚገባውም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። በመጀመሪያው ክፍል ማለትም በቅዱሱ ቦታ ሦስት ነገሮች ነበሩ። እነርሱም፦ በቀኝ በኩል ዳቦ የተቀመጠበት የወርቅ ጠረጴዛ፥ ዘፀ.37:10-16፤ 40:22። በግራ በኩል የወርቅ መቅረዙ ማቆሚያ፥ ዘፀ.37:17-24፤ 40:24። የወርቅ የዕጣን ማጨሻ ነበረ፤ ዘፀ.37:25-28፤ 40:26። በሁለቱ ክፍሎች መካከል መጋረጃ ተሰቅሏል፤

ዘፀ.36:35። የወርቅ የዕጣን ማጨሻው በመጋረጃው ፊት ለፊት ነበር። ከመጋረጃው ኋላ የወርቅ ሳጥን ጽላት የሚባለው በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ነበር። ቁሱ ጠዋትና ማታ በእግዚአብሔር ፊት በወርቅ ዕጣን ማጨሻው ላይ ያጥናል፤ ዘፀ.30:7-8። ዘካሪያስ ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ገብቶ ዕጣን በሚያጥንበት ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር።

ድንኳኑና ቤተ መቅደሱ እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን ያስተምሩናል። ቁሱ በሕጉ መሠረት በተወሰነ ጊዜ ወደ ውስጥ መግባት ይችላል። ሕዝቡ ግን ከአጥሩ ውጭ ይቆያል። አሁን ግን ሁሉም የተለየ ነው። እኛ ክርስቲያኖች ሁላችንም ቁሶች ነን፤ 1ጴጥ.2:5-9። እግዚአብሔር ቅዱስ ቦታ እንድንሠራ አላዘዘንም። ነገር ግን በኢየሱስ ደም በኩል በጣም ቅዱስ ወደሆነው እንድንገባ ተነግሮናል፤ ዕብ.10:19-22። ይህም ማለት በማንኛውም ጊዜና ስፍራ እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ልናመልከው እንችላለን፤ ዮሐ.4:21-24።

ዘካሪያስ ዕጣን በሚያጨስበት ጊዜ በድንገት መልአክ አጠገቡ ቆሞ አየ፤ ምዕ.1:11። መልአኩም ለዘካሪያስ ሚስቱ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ነገረው። የሕፃኑም ስም ዮሐንስ ይባላል። ብዙዎች ሕፃኑ በመወለዱ ደስ ይላቸዋል። መልአኩም የሚወለደው ሕፃን ታላቅ ይሆናል፤ 1:15፤ ዘኁ.6:3። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ይሆናል፤ ብዙ ሰዎችንም ወደ እግዚአብሔር ይመልሳል፤ 1:15-16፤ 3:7-14። መልአኩም ዮሐንስ በመንፈስና በኃይል እንደ ኤልያስ ሆኖ ሕዝቡን ለጌታ ያዘጋጃል፤ 1:17። ነቢዩ ኤልያስ ንጉሡን እንኳን ለመናገር አልፈራም ነበር፤ 1ነገ.17:1፤ 21:17-22። ኤልያስ የበአልን ደካማ ነቢያትን ተቃወመ፤ 1ነገ.18:17-40። አጥማቂው ዮሐንስ የገሊላውን ገዢ ሄሮድስን ክፉ ነገር በማድረጉ ገሰጸው፤ ሉቃ.3:19። እግዚአብሔር ሚልኪያስን ከጌታ ቀን በፊት ኤልያስን እልካለሁ ብሎ ነበር። ኤልያስም የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው ይመልሳል፤ ሚል.4:5-6። ይህ ትንቢት አጥማቂው ዮሐንስ በተገለጠ ጊዜ በከፊል እውነት ሆነ፤ ማቴ.11:14። ኤልያስ ግን ጌታ ኢየሱስ ዳግመኛ ከመመለሱ በፊት ይመጣል፤ ማቴ.17:10-13።

ዘካሪያስ ልጅ እንዲኖረው ይጸልይ ነበር፤ ነገር ግን ይህን አስደናቂ ቃል መልአኩ በነገረው ጊዜ ሊያምን አልቻለም። ዘካሪያስም ይህ ቃል ኪዳን እንደሚፈጸም መልአኩን ምልክት እንዲያሳየው ጠየቀው። ምክንያቱም እርሱና ባለቤቱ አርጅተው ነበር። እግዚአብሔር በገብርኤል ይህንን መልእክት ሲልክ ሁለቱም ማርጀታቸውን ያውቅ ነበር። መልአኩም ለዘካሪያስ ምልክት አሳየው። ይህ ቃል ኪዳን እውነት እስከሆነበት ጊዜ ድረስ ዘካሪያስ መነጋገር አልቻለም።

ዘካሪያስ የእግዚአብሔርን ቃል ስላላመነ ለዘጠኝ ወር ያህል መነጋገር አልቻለም። ባለቤቱ ኤልሳቤጥ ግን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አምና ጌታን አመሰገነች፤ 1:24-25። ለአምስት ወር ያህል ይህንን ታላቅ ዜና ለማንም አልተናገረችም። ነገር ግን እግዚአብሔር ልጅ ስለሚሰጣት በጣም ተደስታ ነበር። በእስራኤል ውስጥ እያንዳንዷ ሴት ልጅ እንዲኖራት ትፈልጋለች። ምክንያቱም ልጅ የሌላቸው ሁሉ የእናቶችን ያህል

አይከበሩም ነበር። ኤልሳቤጥ እንደ ራሄል ነበረች፤ ራሄል ልጅ እንደሚናራት ባወቀች ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገነች፤ ዘፍ.30:23።

2. ጌታ ኢየሱስ እንደሚወለድ ገብርኤል የገባው ቃል፤ 1:26-56

እግዚአብሔር በገብርኤል በኩል ለማሪያም እስኪናገራት ድረስ አንድ ወር አለፈ፤ 1:26-38። ማሪያም በናዝሬት ትኖር ነበር፤ የዳዊት ዘር የሆነውን ዮሴፍን እንደምታገባው ቃል ገብታለት ነበር። በዚህ ጊዜ ማሪያም ድንግል ነበረች፤ ከዚያ በፊት አላገባችም፤ ፥ ከማንም ወንድ ጋራ አልተገናኘችም ነበር። ገብርኤል ማሪያምን «እጓቺ የተባረከሽ» ሊላት ሰላምታው አልገባትም ነበር፤ 1:28-29። ገብርኤልም ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ አላት። ይህም ስም በብሉይ ኪዳን ኢያሱ ከሚለው ጋራ አንድ ነው። የሁለቱም ስሞች ትርጉም «እግዚአብሔር አዳኙ» ማለት ነው። ኢያሱ የእስራኤልን ሕዝብ ከጠላቶቻቸው አዳናቸው፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ እኛን ከሞት አዳነን። መልአኩም ለማሪያም ልጁ ታላቅ እንደሚሆን፥ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል፥ ለዘለዓለምም የእስራኤል ንጉሥ ይሆናል አላት፤ 1:31-33።

ማሪያም የመልአኩን ቃል አመነች፤ ነገር ግን ሳታገባ ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል አላወቀችም ነበር። የማሪያም ጥያቄ ከዘካሪያስ ጥያቄ የተለየ ነበር፤ 1:34፡ 18። ዘካሪያስ የመልአኩን ቃል አላመነም፤ ምልክትም ፈለገ። ማሪያም ቃሉን አመነች፤ ነገር ግን ምን ማድረግ እንዳለባት ለማወቅ ፈለገች። መልአኩም ባል ሳታገባ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በእሷ ላይ እንደሚያርፍ አስረዳት። ልጁም ቅዱስና የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ይጠራል። መልአኩም እምነቷን እንድታጠነክር ለማሪያም ምልክት ሰጣት። የማሪያም ዘመድ የሆነችው ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ነገራት። በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላልና።

ሰዎች ዛሬ ማንኛዋም ሴት ያለ ባል ልጅ እንደማትወልድ ያምናሉ። መጽሐፍ ቅዱስን ለማመን እምቢተኞች ሆኑ፤ የማሪያምን ታሪክና ስለ ሌሎች ተአምራት ስለሚናገር እውነት አይደለም ይላሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ዓለምን ከምንም ለመፍጠር የሚችልና ፍጹም ኃያል ነው። እግዚአብሔር ዓለምንና ሰውን ፈጠረ። እግዚአብሔር ከሰው የበለጠ ታላቅ ኃይል አለው፤ እኛ ለማድረግ የማንችለውን ለማድረግ ችሎታ አለው።

የሚያስደንቀው ነገር ደግሞ እግዚአብሔር ሰው መሆኑ ነው። ሰው ለመሆን ለምን እንደፈለገ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽልናል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለወደደን ይህን እርምጃ ወሰደ። እግዚአብሔር እንዴት ሰው እንደሆነም መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ካለ አባት ከድንግል ተወለደ። ይህ አስደናቂ እውነታ እግዚአብሔርን እንድንወደው ያደርገናል። ስለዚህ አስደናቂ እውነት በአያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን መልእክት እናነባለን። እዚህ ላይ ሉቃስ የእግዚአብሔር ልጅ እንዴት እንደሚወለድ ይነግረናል። ማሪያም የተነገራትን አልቀበልም አላለችም። ነገር ግን ራሷን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፋ

ሰጠች። ማሪያም በነገሩ ሳትኩራራ በፈቃደኝነት በመቅረቧ በጣም ያስደስታል። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ እኛንም በከባድ ፈተና እንዲሁም በማይገባን ነገር ውስጥ እንድናልፍ ይጠይቀን ይሆናል። ግንኛውንም ነገር እግዚአብሔር ለበጐ እንዳደረገው ማመን አለብን። ማሪያም ይህንን በመሰለው አስቸጋሪ ጊዜ እግዚአብሔርን በመታዘዟ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እናት በመሆን ክብር አግኝታለች።

በሚቀጥለው የጥናታችን ክፍል ስለ ማሪያምና ኤልሳቤጥ እንመለከታለን፤ 1:39-56። ማሪያም ለኤልሳቤጥ ሰላምታ በሰጠችበት ጊዜ በኤልሳቤጥ ማሕፀን ያለው ሕፃን ተንቀሳቀሰ። አጥማቂው ዮሐንስ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላ መልአኩ ተናግሯል፤ እናቱም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ማሪያምን አወደሰች። ኤልሳቤጥም የጌታ እናት መጥታ ስለጐበኘቻት ለእርሷ ክብር እንደሆነ አሰበች፤ ቁ.43። እርሷም ማሪያምን፥ «ከሴቶች ሁሉ የተባረክሽ ነሽ» አለቻት። ማሪያም የጌታችን እናት በመሆኗ ከፍተኛ ክብር ነበራት። ሰዎች ወደ ጌታ ኢየሱስ ከመጸለይ ፋንታ ወደ እርሷ እንደሚጸልዩ አልጠበቀችም ነበር። ማሪያም ታላቅ ሴት ነበረች፤ ለራሷም አዳኝ እንደሚያስፈልጋት ታምን ነበር፤ ቁ.47። ሰዎችንም ለጌታ ኢየሱስ እንዲታዘዙ ትመክር ነበር፤ ዮሐ.2:5። እንዲት ሴት የጌታን እናት ባመሰገነች ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ሌሎችም ከማሪያም የበለጠ በረከትን ሊያገኙ ይችላሉ፤ እነርሱም የእግዚአብሔርን ቃል የሚጠብቁ ናቸው አላት፤ 11:27። ጸሎታችንን ለእግዚአብሔር አብና ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር በሰማይም ሆነ በምድር ለማንም ማቅረብ አይገባም።

የኤልሳቤጥ አባባል የማሪያምን እምነት ከፍ አደረገው። ማሪያምም ለእግዚአብሔር የክብር ዝማሬ አቀረበች፤ 1:46-55። ይህ አባባል የሚያመለክተው ማሪያም የእግዚአብሔርን ቃል እንዳመነችና ስለሚመጣውም አዳኝ እንዳመሰገነችው ነው። የማሪያም መዝሙርም እንደሚያመለክተው ማሪያም ብሉይ ኪዳንን በሚገባ እንደምታውቅ ነው። የተጠቀሱትን ቁጥሮች ብትመለከት የማሪያም መዝሙር የቱን ያህል ትርጉም እንዳለው ትረዳለህ።

ቁጥር 46ን ከ1ሳሙ.2:1 ጋር አንብብ።

ቁጥር 47ን ከመዝ.35:9 ጋር አንብብ።

ቁጥር 48ን ከመዝ.138:6 ጋር አንብብ።

ቁጥር 49ን ከመዝ.71:19፤ 99:3፤ 111:9፤ 126:2-3 ጋር አንብብ።

ቁጥር 50ን ከመዝ.103:17 ጋር አንብብ።

ቁጥር 51ን ከመዝ.98:1፤ 118:15 ጋር አንብብ።

ቁጥር 52ን ከ1ሳሙ.2:7-8 ጋር አንብብ።

ቁጥር 53ን ከ1ሳሙ.2:5 ጋር አንብብ።

ቁጥር 54ን ከመዝ.98:3 ጋር አንብብ።

ማሪያም እግዚአብሔርን ያመሰገነችው፡-

ስላሳያት ደግነት ቁ.48-49

- በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ስላሳየው ምሕረት ቁ.50-53

- ለእስራኤላውያን የገባው ቃል እውነት በመሆኑ ነው፤ ቁ.54-55።

እስከ ዮሐንስ መወለድ አካባቢ ድረስ ማሪያም ከኤልሳቤጥ ጋር ቆይታ ወደ ናዝሬት ተመለሰች። በዚያን ጊዜም ማሪያም ራሷ ልጅ እንደምትወልድ ለሁሉም ግልጽ ሆነ፤ የናዝሬት ሕዝቦችና ዮሴፍም ጭምር ይህ ሊሆን የቻለው በኃጢአት ስለወደቀች ነው ብለው አሰቡ። ዮሴፍ ጻድቅ ሰው ነበረ፤ የሙሴንም ሕግጋት ያውቅ ነበር። ዮሴፍ ማሪያምን ይወዳታል፤ ነገር ግን ስለ ኃጢአቷ መቀጣት አለባት ብሎ አሰበ። በሕጉ መሠረት ማሪያም በሞት መቀጣት ነበረባት፤ ዘዳግ.22፡21። ቢያንስ ቢያንስ ዮሴፍ ማሪያምን ላለማግባት ይችላል፤ ዘዳ.24፡1። ዮሴፍ ስለዚሁ ነገር ሲያስብ መልአኩ መጣና እውነቱን አስረዳው፤ ማቴ.1፡18-25። ዮሴፍም የመልአኩን መልእክት አምኖ ማሪያምን ሚስቱ አደረጋት። አንዳች ነገር ከማድረጋችን አስቀድሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠበቅን መሻት አለብን።

3. ዮሐንስ ተወለደ 1፡57-80

የኤልሳቤጥ ሕፃን በተወለደ ጊዜ ጐረቤቶችዋና ዘመዶችዋ መጥተው ከእርሷ ጋር እግዚአብሔርን አመሰገኑ። በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት ሕፃኑን በስምንተኛው ቀን ገረዙት፤ ዘሌ.12፡3። ዘመዶችዋ ሕፃኑ የአባቱን የዘካሪያስን ስም ይይዛል ብለው አስበው ነበር፤ ኤልሳቤጥ ግን ስሙ ዮሐንስ ነው አለች። ዘካሪያስ በዚህን ጊዜ መናገርና መስማት አይችልም ነበር፤ 1፡22 ቁ62። ጓደኞቹም በምልክት የልጁን ስም ጠየቁት፤ እርሱ በጽሑፍ «ዮሐንስ» ብሎ መለሰ።

ብዙ ሰዎች በዚያን ጊዜ አያነቡም ወይም አይጽፉም ነበር። በዛሬውም ጊዜ እንዲሁ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ከቻልን ስለ እርሱም ለሌሎች መመስከር ግዴታችን ነው። ኤልሳቤጥና ዘካሪያስ በዘመዶቻቸው ቃል ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል እንደተመላለሱ ለማወቅ እንችላለን። ሕፃናትለወላጆቻቸው መታዘዝ አለባቸው፤ ነገር ግን እኛ ክርስቲያኖች ከአባቶቻችን ከንቱ ኑሮ ተዋጅተናል፤ 1ጴጥ.1፡18-19።

መልአኩ ለዘካሪያስ እነዚህ ነገሮች እውን እስኪሆኑ ድረስ መናገር እንደማይችል ነገረው፤ 1፡20። ዘካሪያስም የእግዚአብሔር ቃል ተቀብሎ የሕፃኑን ስም ዮሐንስ አለው። ከዚያ በኋላ እንደቀድሞው መነጋገር ቻለ። ሰዎችም ስለሆነው ነገር ተገረሙ፤ ዮሐንስ ምን ዓይነት ልጅ ይሆን? አሉ። ዘካሪያስም ምላሱ የእግዚአብሔርን ክብር ለመናገር መዋል እንዳለበት ተግረ።

ዘካሪያስ ይህንንም ትምህርት ከሙሴ ታሪክ ማወቅ ነበረበት። ሙሴ በፈርዖን ፊት ቢቀርብ ጥሩ ተናጋሪ አልሆንም ብሎ ፈራ። እግዚአብሔር አምላክም እርሱን እግዚአብሔር የሰዎችን አፍ ሠራ አለው። እግዚአብሔር ሙሴን በጥሩ ሁኔታ እንዲናገር

ይረዳዋል ወይም የመናገር ችሎታውን ይወስድበታል፤ ዘጸ.4:10-12። ዘካሪያስ ምላሱን የእግዚአብሔርን ቃል ለማመኑን ለመግለጽ ተጠቀመበት፤ 1:18። ለዘጠኝ ወር ያህል ፈጽሞ መነጋገር አልቻለም ነበር። እንደገና መነጋገር በቻለ ጊዜ ግን ምላሱን እግዚአብሔርን ለማመስገን ተጠቀመበት። ይህ ለእያንዳንዳችን ጠቀሜታ ያለው ትምህርት ነው።

በምዕራፍ አንድ መጨረሻ ላይ ዘካሪያስ እግዚአብሔርን ያመሰገነበትን ቃል እናገኛለን። ለዳዊትና ለአብርሃም የገባው ቃል በመፈጸሙ ዘካሪያስ በመጀመሪያ ለእስራኤል አምላክ ምስጋና አቀረበ፤ 1:68-75፤ መዝ.132:17-105:8-9። እግዚአብሔር ይመጣል ተብሎ የተነገረለት አዳኝ ገና አልተወለደም፤ መቼ እንደሚመጣ ግን ዮሐንስ ያውቃል ብሎ ዘካሪያስ አመነ፤ ቁ.17። ለማሪያም በመልአኩ በኩል የተነገረውንም ጭምር ያመነ ይመስላል፤ 1:32 እና 76።

እግዚአብሔር እስራኤልን ከጠላቶቻቸው እንደሚያድናቸው ዘካሪያስ ከብሉይ ኪዳን ተገነዘበ። ስለዚህ እግዚአብሔርን ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ ሊያገለግሉት ይችላሉ፤ 1:74-75።

አንዳንድ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ያዳናቸው የሚያስደስታቸውን ነገር ለማድረግ እንዲችሉ ይመስላቸዋል። እግዚአብሔር ያዳነን ግን እኛም በቅድስናና በጽድቅ ሕይወት እንድናገለግለው ነው፤ 1ጴጥ.1:15፤ 1ዮሐ.3:7።

ዘካሪያስም ሕፃኑ ወደፊት ምን እንደሚሠራ ተናገረ፤ 1:76 እና 79። የእግዚአብሔር መልእክተኛ ይሆናል፤ ከጌታ ኢየሱስም ፊት ቀድሞ ይሄዳል። ሰዎች በእግዚአብሔር ምሕረት የኃጢአትን ይቅርታ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። በጨለማ ለነበሩት ብርሃን ይሰጣል፤ እግሮቻቸውንም በሰላም መንገድ ይመራቸዋል፤ዮሐ.1:6-8።

የምዕራፍ 1 የመጨረሻው ቁጥር እንደሚያስረዳን ዮሐንስ የእግዚአብሔርን ኃይል አወቀ። የእስራኤልን ሕዝቦች የማስተማር ታላቅ ሥራ እስኪጀምር ድረስ በበረሃ ኖረ። ይህ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ከተወለደ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው። ይህንንም በምዕራፍ 2 እናነባለን። ሉቃስ ወንጌሉን በመጻፍ ነገሮችን በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ፈለገ፤ 1:3። ይህ ማለት ከእያንዳንዱ ቁጥር በፊት ስላለፈው ቁጥር የሆነውን ይናገራል ማለት አይደለም። ሉቃስ በምዕራፍ አንድ መጨረሻ ክፍል ውስጥ ስለ ዮሐንስ መወለድ ይነግረናል፤ እንዲሁም ታላቅ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ስለ ዮሐንስ ታሪክ በጥቂቱ ያወሳል። ሉቃስ የዮሐንስን ታሪክ እንደገና በምዕራፍ 3 ይጽፋል፤ ነገር ግን በመጀመሪያ በምዕራፍ ሁለት ያለውንና ጌታ ኢየሱስ ሲወለድ ምን እንደተፈጠረ ማወቅ አለብን።

በምዕራፍ 1 የሚከተሉትን እንመለከታለን፡-

የእግዚአብሔርን ቃል ለሰዎች - ገብርኤል ለዘካሪያስ ቁ.13-17።

- ገብርኤል ለማሪያም ቁ.30-35።

የሰዎችን ቃል ለእግዚአብሔር - የማሪያም ምስጋና ቁ.46-55።

- የዘካሪያስ ምስጋና ቁ.68-79።

4. ጌታ ኢየሱስ በቤተልሔም ተወለደ፤ 2፡1-21

በመጽሐፈ ኢያሱ እግዚአብሔር እንዴት አድርጐ የእስራኤልን ምድር ለሕዝቦቹ እንደሰጠ ማንበብ ትችላለህ። ጠላቶቹ እስራኤላውያንን ወደ ባቢሎን እንዲወ ስዷቸው ጌታ ፈቀደላቸው። በ2ኛ መጽሐፈ ነገሥትና በ2ኛ መጽሐፈ ዜና ታነባለህ። መጽሐፈ ዕዝራ የፋርስ ንጉሥ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ መፍቀዱን ይገልጻል፤ ነገር ግን በቁጥጥሩ ሥር ነበሩ። በኋላም ግሪኮች ፋርስንና ሌላም ብዙ አገር ለአጭር ጊዜ ገዙ። ከዚያም የሮም ሰዎች የግሪክን ወታደሮች አሸንፈው አብዛኛውን የዓለም ክፍል እስራኤልን ጭምር ገዙ። የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ስለ ታላቁ የሮም ንጉሥ ስለ አውግስጦስ ይናገራል። ሰዎች ሁሉ ስማቸውን በእርሱ መንግሥት መጻሕፍት ውስጥ እንዲመዘገቡ አውግስጦስ አዘዘ። ይህም ሰዎች ሁሉ ግብር መክፈላቸውን እርግጠኛ እንዲሆን ነበር። እስራኤል የሦሪያ ክፍል ነበረች። ዮሴፍና ማሪያም በገሊላ ውስጥ በናዝሬት ከተማ ይኖሩ ነበር፤ ነገር ግን በኋላ ወደ ቤተልሔም ሄዱ፤ ምክንያቱም ዮሴፍ የዳዊት ዘር ስለነበረ ነው፤ 1ሳሙ.16፡1 እና 13። በቤተልሔም ይኖሩ በነበረበት ጊዜ የማሪያም ወንድ ልጅ ተወለደ። እንዲሞቀውም በጨርቅ ጠቀለለችው። እዚህ ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደማንኛውም ሕፃን ልጅ እንደተወለደ እንመለከታለን። ከመወለዱ በፊትም ሙሉ የፅንስ ዕድገቱን ጨርሶ ተወለደ። ማንኛዋም እናት ለልጇ እንክብካቤ እንደምታደርገው ሁሉ ማሪያምም ልጇን ተንከባከበችው።

በቤተልሔም የእንግዶች ማረፊያ ሆቴል ነበር፤ ነገር ግን ለማሪያምና ለአዲሱ ልጇ ቦታ አልነበረም፤ 2፡7። ዮሴፍና ማሪያም የከብቶች ጋጣ አግኙና ማሪያም ሕፃን ኢየሱስን ከዚያ ወለደች። ይህም የእግዚአብሔር ልጅ ወደዚህች ዓለም በመጣ ጊዜ ሰዎች አለመቀበላቸውንና እምቢተኝነታቸውን ያሳያል።

የሰማይ መላእክት ግን መሢህ መምጣቱን አወቁ። በመጀመሪያ መልአኩ በምሽት በጐች ለሚያግዱ ተገለጠ። እረኞች ደነገጡ፤ ነገር ግን መልአኩ መልካም ዜና እንዳመጣ ነገራቸው። አዳኙ ክርስቶስ ጌታ በዚያች ዕለት በቤተልሔም ተወለደ። መልአኩም እረኞቹ ሕፀኑን ማግኘት እንዲችሉ ምልክት ሰጣቸው። ከዚያም ከመቅድበት ቁጥራቸው ብዙ የሆነ መላእክት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ አዩ፤ 2፡13-14።

መላእክት መንፈስ ስለሆኑ ሰው ብዙውን ጊዜ ሊያያቸው አይችልም። መላእክት እንደ እግዚአብሔር መልእክተኞች ያገለግላሉ፤ አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ይናገራሉ። መልአኩ ለእረኞቹ የሕፃኑን ስም አልነገራቸውም፤ ነገር ግን አዳኝ ተወልዷል፤ «እርሱም ክርስቶስ ጌታ ነው» ብሏቸዋል። እረኞቹም የእስራኤል ገዢ በቤተልሔም በዳዊት ከተማ እንደሚወለድ አወቁ፤ ሚክ.5፡2። ክርስቶስ ወይም መሲህ እንደሚመጣ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ቃል ገብቷል። ክርስቶስ ደግሞ አምላክ ነው፤ ስለሆነም እያንዳንዱ ሰው ለእርሱ መታዘዝ አለበት። ይህ መልካም ዜና ለእረኞች ብቻ ወይም ለእስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሰው መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፤ 2፡10። ክርስቶስ መጣ፤ ለእግዚአብሔርም ክብር አመጣ፤ ለሰዎችም ሰላምን ቁ.14። ጌታ

ኢየሱስ ክርስቶስ እውነትም ለአባቱ ክብርን አመጣ። ክርስቶስ ጌታ አሁንም በእርሱ ለሚያምኑ ሰላምን ይሰጣል፡ ሮሜ 5፡1።

የመልአኩ መልእክት ከእግዚአብሔር እንደነበረ እረኞቹ አመኑ፤ 2፡15። ወደ ቤተልሔም ሄደው ወዲያው ማሪያምንም፡ ዮሴፍንም፡ ሕፃኑን ኢየሱስንም አገኙ። መልአኩ ያለውንም ለማሪያምና ለዮሴፍ ተናገሩ። ማሪያም እነዚህን ነገሮች ሁሉ አስታወሰች፡ እረኞቹም ሰላዩትና ስለሰሙት እግዚአብሔርን አመሰገኑ። አብዛኛውን የቤተልሔም ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ አልተቀበሉትም። ጥቂት እረኞች ሊያዩት ሄዱ። ከዚህም የምንረዳው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያምኑና የሚወዱት ጥቂቶች መሆናቸውን ነው።

እግዚአብሔር አብርሃምን ወንዶችንና ሕፃናትን እንዲገርዝ ነገረው። ይህም የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ነበር፤ ዘፍ.17፡11-12። በኋላም የእስራኤልን ወንዶች እያንዳንዱን ወንድ ሕፃን እንዲገርዙ እግዚአብሔር አዘዘ፤ ዘሌ.12፡3። ጌታ ኢየሱስ የአብርሃም ልጅ፡ የዳዊት ልጅ ነበር፤ በሕጉ መሠረትም በስምንተኛው ቀን ተገረዘ፤ 2፡21።

በኋላም ሐዋርያው ጳውሎስ ከአይሁዳውያን ጋራ ስለ ግዝረት ብዙ ችግር ነበረበት። ጳውሎስ ወንጌልን ለብዙ ሰዎች ሰበከ፤ እምነታቸውን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማድረግ እንደሚድኑ አስተማረ። ጳውሎስ ከሄደ በኋላ ከኢየሩሳሌም ሌሎች ሰዎች መጥተው መገረዝ እንዳለባቸው ለሰዎች ተናገሩ፤ የሙሴን ሕግ እንጠብቃለን አሉ፤ የሐዋ/ሥራ 15፡1። ጌታ ኢየሱስ ተገርዞ ነበር፤ ሕግጋቱንም ጠብቋል። ነገር ግን ለማዳን መንገዱ የሚያስፈልገው ይኸ ነው ብሎ አላስተማረም።

ዛሬ ብዙዎች ለመዳን ሕጉን መጠበቅ አለብህ ብለው ያስተምራሉ። በኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጥ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ዮሐ.3፡16። ሕግን ለሚጠብቁ የዘላለም ሕይወት ይሰጣል አይልም፤ ገላ.2፡16። ይህ የወንጌል መልእክት ነው። ጽድቅ ከእግዚአብሔር ነው ብለህ የምታምን ከሆነ እረኞቹ እንዳደረጉት ወደ ክርስቶስ ና።

5. ማሪያምና ዮሴፍ ሕፃን ኢየሱስን ወደ ቤተ መቅደስ አመጡ ሉቃስ 2፡22-40

ከዚያ በኋላ ማሪያምና ዮሴፍ ሌላ የሙሴን ሕግ እንዲፈጽሙ ወደ ቤተ መቅደስ አመጡት። በማንኛውም ቤተሰብ የመጀመሪያው ልጅ ወንድ ከሆነ እናትና አባቱ ወደ እግዚአብሔር ማምጣት ነበረባቸው፤ ዘፀ.13፡12-13። በዘሌዋውያን መሠረት ማሪያም መስዋዕት ማቅረብ ነበረባት፤ ዘሌ.12፡2-8። ማሪያምና ዮሴፍ ጠቦት ማምጣት ስላልቻሉ ሁለት እርግቦች አመጡ። ከዚህም የምንረዳው የእግዚአብሔር ልጅ ከድሃ ሠራተኛ ቤተሰብ መወለዱን ነው፤ 2ቆሮ.8፡9። ከታላቅ ሀብት ይልቅ መልካም ስምን ምረጥ፤ ምሳ.22፡1።

የእግዚአብሔርን ቃል የሚያምኑ በኢየሩሳሌም ሁለት ሰዎች ነበሩ፤ አዳኝ ይመጣል ብለውም ይጠባበቁ ነበር። ከእነዚህም አንዱ ስምዖን ነበር። አዳኙን ሳያይ እንደማይሞት መንፈስ ቅዱስ አሳየው። ማሪያምና ዮሴፍ ሕፃን ኢየሱስን ወደ ቤተመቅደስ በሚያመጡበት ጊዜ ስምዖንን መንፈስ ቅዱስ ወደዚያ መራው። ሕፃን ኢየሱስ የዓለም አዳኝ መሆኑን ስምዖን አወቀ፤ 2፡29-32።

ስምዖን ዮሴፍንና ማሪያምን ባረካቸው፤ ግን ማሪያም ትልቅ ሐዘን ደግሞ እንደሚገጥማት አስጠነቀቃት፤ ቁ.35። ስምዖን ይህንን ማስጠንቀቂያ ለማሪያም ለምን ነገራት? ለምን ዮሴፍን አላለውም? ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ስለ ዮሴፍ አናነብም። ጌታ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት ዮሴፍ ሞቶ ሊሆን ይችላል። የልጇን የኢየሱስን በመስቀል ላይ መሞት አይታ ያዘነችው ማሪያም ብቻ ነበረች።

ሌላ አማኝ ሐና የምትባል በኢየሩሳሌም ነበረች። ባለቤቷ ከመሞቱ በፊት ለሰባት ዓመታት አብራ ቆየች። አሁን ግን በጣም አርጅታለች። እርሷ እግዚአብሔርን ትወድ ነበር፤ ሁልጊዜም በቤተ መቅደስ ትውል ነበር፤ 2፡37። እርሷም ሕፃኑ እዚያ በነበረበት ወቅት ገባች። አዳኝ ስለላከ እግዚአብሔር አመሰገነች። መሢሁ እንደሚመጣ ይጠባበቁ የነበሩ ሌሎች ሰዎችን ታውቃለች፤ ለሁሉም ስለ ሕፃኑ ነግራለች።

ማሪያምና ዮሴፍ ወደ ናዝሬት ተመለሱ፤ ሕፃን ኢየሱስም አደገ፤ ጠንካራም ሆነ፤ 2፡39-40። ወደ ናዝሬት ከመመለሳቸው በፊት ምን እንደተፈጠረ በማቴዎስ ወንጌል እናነባለን። እግዚአብሔር ለአንዳንድ ብልህ ሰዎች የይሁዳ ንጉሥ መወለዱን ገለጸ። እነዚህ ጠቢባን ንጉሡን ለመፈለግ ከወደ ምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። ንጉሥ ሄሮድስ ይሁዳዊ አልነበረም፤ አዲስ ንጉሥ መወለዱን በሰማ ጊዜም አልተደሰተም። ቁሳውስት መሲህ በቤተልሔም እንደሚወለድ ነገሩት፤ ሚክ.5፡2። ሄሮድስም ለጠቢባኑ ሰዎች እሱም መጥቶ ለሕፃኑ ንጉሥ እንደሚሰግድለት ነገራቸው፤ ነገር ግን ሊገድለው ፈልጐ ነው። ጠቢባን ሰዎቹ ማሪያምንና ሕፃን ኢየሱስን ባገኙ ጊዜ ሰገዱለት፤ የሰገዱላት ለማሪያም አልነበረም። እነርሱም ትልቅ ዋጋ ያለው ስጦታ ሰጡት። ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ እግዚአብሔር ስለነገራቸው በሌላ መንገድ ወደ ቤታቸው ተመለሱ፤ ማቴ.2፡1-12።

ጠቢባኑ ወደ እርሱ ሳይመለሱ ስለቀሩ ሄሮድስ በጣም ተናደደ፤ ወታደሮቹንም ወደ ቤተልሔም ልኮ ወንዶች ሕፃናትን ሁሉ እንዲገድሉ አዘዘ። እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ዮሴፍን ይህ እንደሚሆን አስጠነቀቀው፤ ወደ ግብፅም እንዲሄድ ነገረው። ከዚህም በኋላ ሄሮድስ ሞተ፤ እግዚአብሔርም ዮሴፍ በገሊላ በሚገኘው ወደ ቤቱ ወደ ናዝሬት እንዲመለስ ነገረው፤ ማቴ.2፡13-23።

ከዚህ የሚከተሉት አንዳንድ ቁጥሮች በመዝሙር መልክ ስለተጻፉ ደስ ይላሉ። ገብርኤል ለዘካሪያስ 1፡14-17 ዘካሪያስ ያለው 1፡68-79 ገብርኤል ለማሪያም 1፡32-33፤ 35 መልአኩ የተናገረው 2፡14 ማሪያም ያለችው 1፡46-55 ስምዖን ያለው 2፡29-32፤ 34-35።

6. ጌታ ኢየሱስ አሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ
2:41-52

በእነዚህ ቁጥሮች ከምናነበው በስተቀር ስለ ጌታ ኢየሱስ ቀደም ስላሉት ጊዜያቶች ምንም አናውቅም። ናዝሬት ጥሩ ከተማ ነበረች ብለው ሰዎች አይገምቱም፡ ዮሐ.1:46። ጌታ ኢየሱስ ማንበብና መጻፍ ቻለ፤ ሉቃ.4:16፤ ዮሐ.8:8። ዮሴፍ አናጢ ስለነበረ ልጁን ኢየሱስን የእንጨት ሥራ እንዳስተማረው ጥርጥር የለውም። በቤቱም ውስጥ ቢያንስ ቢያንስ ስድስት ታናናሾች ልጆች ነበሩ፤ ማቴ.13:55-56።

ዮሴፍና ማሪያም ለፋሲካ በዓል በየዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር። ይህም የሚደረገው በመጀመሪያው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን ነበር፤ ዘሌ.23:5። ጌታ ኢየሱስ አሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜም ከዮሴፍና ከማሪያም ጋር ወደ ግብጣው ይሄድ ነበር። ግብስጣው በተፈጸመ ጊዜ ዮሴፍና ማሪያም ወደ ናዝሬት ተመለሱ፤ ኢየሱስ ግን ወደ ኋላ ቀረ። ሌሎች ብዙ ሰዎችም ወደ ገሊላ ተመለሱ። ዮሴፍና ማሪያም ልጃቸው ኢየሱስ ከሌሎች ሰዎች ጋራ ይሆናል ብለው ገመቱ። በመሸም ጊዜ ፈለጉት፤ ሊያገኙት ግን አልቻሉም። በሚቀጥለው ጠዋት ጉዞአቸውን እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም አደረጉ፤ በሦስተኛውም ቀን በቤተ መቅደስ አገኙት። ከአስተማሪዎች ጋር ተቀምጦ ያዳምጣቸው ነበር፤ ጥያቄም ይጠይቃቸዋል፤ ለጥያቄአቸውም መልስ ይሰጥ ነበር። ማሪያምም ዮሴፍና እርሷ ይፈልጉት እንደነበረ ነገረችው። በአባቱ ቤት እንደሚሆን ማወቅ ነበረባቸው አለ። የተናገረውንም አላጤኑትም ነበር፤ ግን አብሮአቸው ወደ ናዝሬት ተመለሰ፤ ያሉትንም ይፈጽም ነበር፤ 2:41-52።

ከእነዚህ ቁጥሮች ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አንዳንድ አስደናቂ ነገሮችን እንማራለን። እንደ ሰው ልጅ ሰውነቱ አደገ፡ ጠነከረም። በጥበብም አደገ፤ 2:52። የእግዚአብሔርን ቃል ይወድ ነበር፤ ቁ.46። በአባቱም ቤት በቤተ መቅደስ መሆን ፈለገ፤ ቁ.49። የጌታችን የመጀመሪያዎቹ ቃሎች ስለ አባቱ ነበር። ኢየሱስ ሕፃን በነበረበት ጊዜ ብዙ ነገሮች ተናግሯል፤ ነገር ግን ለእኛ የተሰጡን የመጀመሪያ ቃሎች በምዕራፍ 2 ይገኛሉ፤ 2:49። እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ በቤተ መቅደስ ከሚገኙ አስተማሪዎች ይበልጣል፤ ነገር ግን እንደ ሕፃን መጠየቁና አለማስተማሩም ትክክል ነበር። ቁ.46። እንደ ልጅም ለዮሴፍና ለማሪያም መታዘዙ ትክክል ነበር። ሕጉን ሊፈጽም መጣ፤ ማቴ.5:17። ሕጉም ለአባትና ለእናትህ ክብር ስጥ ይላል፤ ዘፀ.20:12። እኛን ክርስቲያኖችንም መንፈስ ቅዱስ ይህኑን ያስተምረናል፤ ኤፌ.6:1-2፤ ቆላ.3:20።

እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት ልጁን ወደደው፤ ዮሐ.17:24። የአባቱን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸም ልጁ ወደዚህ ዓለም መጣ፤ መዝ.40:7-8። ታዲያ ለምን በቁ.52 ላይ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ ሆነ ይላል? እግዚአብሔርም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃዱን በሚገባ የፈጸመ ሰው መሆኑን ተመለከተ። ይህንንም ለማድረግ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በታሪክ የመጀመሪያው ሰው ነበረ። ይህም እግዚአብሔር አብን

በጣም አስደሰተው። እግዚአብሔር አብ ልጁን የበለጠ ይወደዋል፤ ምክንያቱም ልጁ ሕይወቱን አሳልፎ ስለሰጠው ነው፤ ዮሐ.10፡17።

እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ ይወዳል፤ ነገር ግን ቃሉን ስናከብር ደግሞ የበለጠ ይወደናል፤ ዮሐ.14፡32። እግዚአብሔር በልጁ እንደተደሰተ ሁሉ እኛንም ልጁን እንድንመስልለት ይፈልጋል። ክርስቶስን እየመሰልን ባደግን ቁጥር እግዚአብሔር አብ በጣም ይደሰታል።

ጌታ ኢየሱስ ወደዚህች ዓለም እንዴት እንደተወለደ በማቴዎስ 1 እና በሉቃስ 2 እናነባለን። በሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ደግሞ እነዚህ ድርጊቶች የቱን ያህል ከፍተኛ ቦታ እንደሚሰጣቸው እንመለከታለን። ሰው በመጀመሪያ በኃጢአት በወደቀ ጊዜ እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚመጣ ቃል ገባለት፤ ዘፍ.3፡15። ለአብርሃም አዳኙ ከዘሩ እንደሚወለድ ቃል ገባለት፤ ዘፍ.22፡18። ይህ ቃል ኪዳን ወደ ይስሐቅ ተላለፈ፤ ዘፍ.26፡4። ወደ ያዕቆብም፥ ዘፍ.28፡14። የሚመጣው አዳኝ ሰው እንደሚሆን ደግሞ ግልጽ ነበር።

ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ደግሞ ራሱ እግዚአብሔር እንደሚመጣ ያስረዱናል፤ ኢሳ.25፡9፤ 40፡10፤ ሚል.3፡1። ትንቢት የተነገረለት አዳኝ እንዴት አምላክም ሰውም ሊሆን ይችላል? እውነቱን በአዲስ ኪዳን እንመለከታለን። ቃል እግዚአብሔር ነበረ። ይህም ቃል ሰው ሆነ፤ ዮሐ.1፡1 እና 14። በተጨማሪም ሌሎች ጥቅሶችን ተመልከት፤ ሮሜ 9፡5፤ 1ቆሮ.15፡47፤ 1ጢሞ.3፡16። እግዚአብሔር ከፈለገ ሰው ለመሆን ኃይል እንዳለው ማመን አለብን። ሰውም ለመሆን የፈለገበት ምክንያት ስለሚወደን ነው። ሰዎችን ከኃጢአታቸው ሊያድናቸው የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከርስቶስ ሰው ብቻ ቢሆን ኖሮ ሕይወቱን ሊሰጥ የሚችለው ለሌላ አንድ ሰው ብቻ ነበር። ወደዚህ ዓለም መጥቶ እንዲያድነን የእግዚአብሔር ፍቅር መራው። በመጀመሪያ ስለወደደን እንወደዋለን።

ከመጀመሪያው አንሥቶ ጌታ ኢየሱስን ብዙ ሰዎች እንዳልተቀበሉት ግልጽ ነበር፤ ዮሐ.1፡11-12። ሄሮድስ ሊገድለው ሞከረ። ቄሳውስት በብሉይ ኪዳን የተናገረውን ያውቁ ነበር፤ ነገር ግን ይህንን አዲስ የተወለደውን አዳኝ ለማየት አልፈለጉም። የሆቴሉ አስተናጋጆች በቤተልሔም ቦታ ሊያገኙለት አልቻሉም።

በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር መላእክት አዳኝ እንደሚመጣ አበሰሩ፤ በተወለደም ጊዜ ተደሰቱ። ኤልሳቤጥና ዘካሪያስ ልጃቸው ዮሐንስ ስለ አዳኙ መምጣት እንደሚናገር አወቁ። ማሪያምና ዮሴፍም የእግዚአብሔርን መልእክት አመኑ። ጌታ ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ ስምዖንና ሐና በጣም ተደሰቱ፤ እረኞቹና ጠቢባኑ ከምስራቅ እንዲሁ ተደሰቱ።

አሁንም እንደ ጥንቱ ነው። ብዙ ሰዎች ጌታ ኢየሱስን ይወዳሉ፤ ስለ እርሱም ለሌሎች ይመሰክራሉ፤ ነገር ግን ብዙ የሚጠሉትም አሉ። ሌሎችም ትተውታል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም የላከው አዳኝ ነው። ከእግዚአብሔር ወገን ለመሆንህ እርግጠኛ ነህ?

7. ጌታ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት 3:1-4:13

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጌታ የወጣትነት ጊዜ ምንም አይነግረንም። ወደ ኢየሩሳሌም በሄደበት ጊዜ አሥራ ሁለት ዓመቱ ነበር፤ 2:42። ታላቁን ሥራውን በጀመረበት ጊዜ ሠላሳ ዓመት ይሆነው ነበር፤ 3:23። ከላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች መሃከል ስለ አጥማቂው ዮሐንስ እናነባለን። ከብዙ ጊዜ በፊት ጥቂት ሰዎች ጌታ ኢየሱስ በወጣትነት ጊዜው ምን ይሠራ እንደነበረ ታሪኩን ለመጻፍ ሞክረዋል። ከነዚህም ታሪኮች ውስጥ አንዳንዶቹ እውነት ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን እርግጠኞች ልንሆን አንችልም። የመጽሐፍ ቅዱስ 66 መጻሕፍት በሙሉ እውነት መሆናቸውን እናውቃለን። እግዚአብሔር አንድ ቀን በመንግሥተ ሰማያት የበለጠ ይነግረናል፤ አሁን ግን ይህንን እንድናውቅ ስላደረገን ልናመሰግነው ይገባናል።

1. ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስን አጠመቀው 3:1-22

ሉቃስ ጠንቃቃ ጸሐፊ ነበር፤ ድርጊቶችን በቅደም ተከተል እንዲጽፍ መንፈስ ቅዱስ መራው፤ 1:3። በሉቃስ መጽሐፍ ከምዕራፍ 3-24 ያለው አብዛኛውን ስለ መጨረሻዎቹ ሦስት ዓመታት ነው። ሉቃስ እነዚህን ምዕራፎች ሲጀምር የሰባት ገዢዎችን ስም በመጥቀስ ነው። ስለዚህ እነዚህ ነገሮች መቼ እንደተፈጸሙ ለማወቅ እንችላለን። ሌሎች የቆዩ መጻሕፍት ጌታ ኢየሱስ እዚህ ዓለም ይኖር በነበረበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ይነግሩናል። ከአውግስጦስ ሞት በኋላ ጢባርዮስ የሮም ንጉሥ ነበር፤ 2:1። ስለ ሌሎችም ነገሥታት በአዲስ ኪዳን እናነባለን። ለምሳሌ:- የሐዋ/ሥራ 25:8-12፤ ፊል.4:22። ንጉሡ ጲላጦስን የይሁዳ ገዢ እንዲሆን ሾመው። ሄሮድስ የገሊላ ገዢ ነበር፤ ወንድሙም ፊልጶስ በሰሜን ምዕራብ የምትገኘውን ኢጡሪያስ ይገዛ ነበር። ነገር ግን በሌላ ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ ስላሉ አናገኝም። በእነዚህ ሰዎች አገር በተለያዩ ጊዜያቶች ጌታ ኢየሱስ ይኖር ነበር።

ሮማውያን የእስራኤልን ምድር በሙሉ ይገዙ ነበር፤ ነገር ግን ለአይሁዳውያን ሕጋቸውንና ሃይማኖታቸውን በሚመለከት ነፃነት ሰጥቶአቸው ነበር። ካህኑ ከፍተኛ ሥልጣን ነበረው። እንደተለመደው በአንድ ጊዜ ሊኖር የሚችለው አንድ ብቻ ነው፤ ነገር ግን በእነዚህ ዓመታት ውስጥ አናስና ቄያፋ ሁለቱም ካህን ተብለው ነበር። ቄያፋ የሁለት ሰዎች ታናሽ ነበር፤ የአናስንም ልጅ አግብቶ ነበር፤ ዮሐ.18:13። እነዚህ ሁለት ሰዎች ጌታ ኢየሱስን ለመግደል ይፈልጉ ነበር። ጲላጦስና ሄሮድስ ከእነዚሁ ሰዎች ጋራ ተስማሙ። በ3:1-2 ስለተጠቀሱት ሰባት ሰዎች ግን ብዙ አናነብም።

በዚህን ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ወደ አጥማቂው ዮሐንስ መጣ። ኤልያስና ሌሎች ነቢያት በዚህ አባባል ተጠቅመዋል፤ 1ነገ.17:2፤ ኤር.1:4፤ ሕዝ.1:3፤ ኢዩ.1:1፤ ዮና.1:1፤ ሚክ.1:1፤ ሶፎ.1:1፤ ሐጌ 1:1፤ ዘካ.1:1። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ዮሐንስ በበረሃ ነበረ፤ 1:80። ዮሐንስ ከፀጉር የተሠሩ ልብሶችን ይለብስ ነበር፤ በበረሃ የሚገኘውንም ይበላ ነበር፤ ማቴ.3:4። በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ወደሚኖሩ ሰዎች ሄደ። ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙና እንዲጠመቁ ነገራቸው፤ 3:3።

መንግሥተ ሰማያትም ቀርባለች አላቸው፤ ማቴ.3:2። ዮሐንስ ከእግዚአብሔር ተላከ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነው፤ የእግዚአብሔርም በግ ነው ብሎ አስተማረ፤ ዮሐ.1:6-8:29። ዮሐንስ ሰዎች ለእግዚአብሔር እንዲዘጋጁ የሚጠራ ድምፅ ነበር፤ ኢሳ.40:3-5። ዮሐንስ ከኃጢአታችሁ ተመለሱ እያለ ሰዎችን ለጌታ ኢየሱስ መምጣት አዘጋጃቸው። ሁሉም ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው፤ ቁ.5። ዛሬ ሁሉም ሰዎች ስለ አዳኙ መምጣት መልካም ዜና እንዲሰሙ ፈቃዱ ነው፤ ነገር ግን ክርስቶስ እንደገና በተመለሰ ጊዜ እያንዳንዱ ሕይወት ያለው ሰው ሁሉ ያየዋል፤ ቁ.6።

ከ400 ዓመት በፊት ከነገራቸው ከሚልክያስ ዘመን የእስራኤል ሕዝቦች ከነቢይ በኩል የእግዚአብሔርን ቃል አልሰሙም ነበር። ዮሐንስ ሲሰብክ ብዙ ሰዎች መጡ። አንዳንዶቹ እንደ እንድሪያስ የመሳሰሉት በእውነት ጌታን ይፈልጉ ነበር፤ ዮሐ.1:35-40። ሌሎች ደግሞ ወደ ጌታ ለመመለስ የፈለጉ ያስመስሉ ነበር። ዮሐንስም እነዚህን እንደ እባቦች ናቸው አላቸው፤ ማቴ.3:7። በኋላም ጌታ ኢየሱስ የእስራኤል አስተማሪዎች የነበሩትን ፈሪሳውያንን ተመሳሳይ ቃል ተናገራቸው፤ ማቴ.12:34፤ 23:33። ዮሐንስ ለሰዎቹ መናዘዛቸውን ለማሳየት ጥሩ ሥራዎችን እንዲሠሩ ነገራቸው። የአብርሃም ዘሮች ስለነበሩ ጥሩ ሰዎች ነን ብለው ያስቡ ነበር፤ 3:8። ዮሐንስ የአብርሃም ዘሮች እንኳን ቢሆኑ ከኃጢአታቸው መመለስ አለባቸው። የፍርድ ቀን ተቃርባለች፤ እግዚአብሔርም የሰውን እውነተኛ ፍጥረት ይገልጣል፤ 3:9።

ከእነዚህ ትምህርቶች አንዳንዶቹን በማቴዎስና በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ታገኛለህ፤ ማቴ.3:1-12፤ ማር.1:4-8። ሦስት ጥያቄዎችና መልሶች በሉቃስ ውስጥ ብቻ አሉ፤ ሉቃ.3:10-14። ዮሐንስ ለሕዝቡ ንስሐ የገቡ ከሆኑ ድሆችን በመርዳት ሊያሳዩት ይችላሉ አላቸው፤ 3:11። ቀራጮች ሕጉ ከሚያዘው በላይ ሰዎችን ለማስከፈል ይሞክራሉ። ቀራጮች ከኃጢአታቸው ከተመለሱ ይህንን ከማድረግ ይቆጠባሉ። አንዳንድ ወታደሮችም በቂ ገንዘብ አይከፈለንም ብለው ስለሚያስቡ በሌላ መንገድ ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ይሞክራሉ። እነርሱም ይህንን ማቆም አለባቸው።

ሕዝቡ ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ሲሰብክ በሰሙ ጊዜ የሚመጣው አዳኝ ይኸ ይሆን ብለው አሰቡ፤ 3:15-17። ዮሐንስም ሌላ ከእኔ የበለጠ ይመጣል አላቸው። ዮሐንስ የክርስቶስ አሽከር እንኳ ለመሆን እንደማይችል ራሱን ቆጠረ፤ 3:16። ዮሐንስ ሰዎችን በውኃ አጠመቀ፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ለሚያምኑት መንፈስ ቅዱስን ይልካል። እርሱም በቀሩት ሰዎች ላይ የእሳት ፍርድ ያመጣል። ገበሬው እህሉን በሚወቃበት ጊዜ መልካሙን እህል ከገለባው ይለያል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም አማኞችን ከማያምኑ እንዲሁ ዛሬም ይለያል፤ 3:17፤ 2:34።

በልጁ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖርበታል እንጂ ሕይወትን አያገኝም፤ ዮሐ.3:36።

ሉቃስ ነገሮችን እንደ ድርጊታቸው ቅደም ተከተል እንዳልጻፈ ተመልከተናል፤ 1:80። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሄሮድስ ዮሐንስን አሰረው በማለት በዮሐንስ ታሪክ ላይ ተጨማሪ ነገር ጽፎልናልና፤ 3:18-20። ይህም የሆነው ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስን

ካጠመቀው በኋላ መሆን አለበት፣ 3፡21። እያንዳንዱ ድርጊት የተፈጸመበትን ትክክለኛ ቅደም ተከተል ለማወቅ አራቱንም ወንጌሎች ማንበብ አለብን።

ዮሐንስ መልካም ዜና ለሕዝቡ ሰበከ፣ 3፡18። ኃጢአታቸው ይቅርታ እንደሚደረግለትና አዳኙ እንደሚመጣ ነገራቸው። ሕዝቦችም ኃጢአትኞች መሆናቸውን ለመናገር አልፈራም። ዮሐንስ ሄሮድስንም እንኳ አልፈራም። ሄሮድስ የፊልጶስ ሚስት የነበረችውን ሄሮዲያዳን አገባ። ዮሐንስም ሄሮድስን የሌላ ሚስት የሆነችውን ማግባት ትክክል አልነበረም አለው። ሄሮድስ ዮሐንስ መልካም ሰው እንደነበረ ያውቃል። ዮሐንስን ይፈራው ነበር፡ ሚስቱ ዮሐንስን እንዲያስረው ስለፈለገች እስር ቤት አስገባው፣ ማር.6፡17-20።

ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስን እንዳጠመቀው እንመለከታለን፣ 3፡21-22፣ ይህም በጌታ ሕይወት ከታላላቅ ድርጊቶች ውስጥ አንዱ ነበር። በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ ለመጠመቅ ጌታ ኢየሱስ ከገሊላ መጣ፣ ማቴ.3፡13-17። ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስ እኔን ቢያጠምቅ መልካም ነበር ብሎ አሰበ፣ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ትክክል የሆነውን ለማድረግ ፈለገ። ከውኃውም ውስጥ ሲወጣ የእግዚአብሔር መንፈስ በላዩ ላይ እንደ እርግብ ሲወርድበት ሁለቱም አዩት። ይህ እግዚአብሔር ለዮሐንስ ያሳየው ምልክት ነበር፣ ዮሐ.1፡32-33። ከዚያም እግዚአብሔር ከሰማይ ተናገረ፣ «አንተ የተከበርክ ልጄ ነህ፣ በአንተ በጣም ተደስቻለሁ»።

ሰዎችን ሁሉ ከኃጢአታቸው መመለስ እንዳለባቸው ዮሐንስ ከማጥመቁ በፊት ነገራቸው። ጌታ ኢየሱስ ምንም ኃጢአት አልነበረበትም፣ ነገር ግን ዮሐንስ እንዲያጠምቀው ፈለገ፣ ብዙ ሰዎች ዛሬ ጥምቀት ምን ማለት እንደሆነ አይረዱም። ጌታ ኢየሱስ ከውኃ ውስጥ እንደወጣ እንመለከታለን፣ ማቴ.3፡16፣ ማር.1፡10። ዮሐንስ በዚያን ጊዜ ብዙ ውኃ በነበረበት በዮርዳኖስ ወንዝ ሄኖን በተባለ ሥፍራ ሰዎችን አጠመቀ፣ ዮሐ.3፡23። ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስን በውኃ ውስጥ በማጥለቅ እንደገና አወጣው፣ ይህም ሞቶ በኋላ ደግሞ በሕይወት መነሣትን የሚያመለክት ነው። በተጠመቅን ጊዜ ሞቶ ከተነሣው ከክርስቶስ ጋር ኅብረት እንዳለን ማሳየታችን ነው፣ ሮሜ 6፡3-6። ስለ ጥምቀት ማወቅ የሚገባን ትልቅ ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን እንደማያደርገን ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ጌታ ኢየሱስን መቀበልና በስሙም ማመን አለብን፣ ዮሐ.1፡12። የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ሌሎችም የክርስቶስ መሆንህን እንዲያውቁ መጠመቅ አለብህ።

ከእነዚህም ጥቅሶች እንደምንረዳው እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህ እውነታ በብሉይ ኪዳን በሚገባ አልተገለጸም፣ ነገር ግን ገብርኤል ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ ስለ እግዚአብሔር አብና ስለ እግዚአብሔር ልጅ ተናግሯል፣ ሉቃ.1፡32 እና 35። የእግዚአብሔር አብ ድምፅን በልጁ ደስ እንዳለው በተናገረ ጊዜ እንሰማለን። እግዚአብሔር አንድ ነው። ነገር ግን አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህንን ጥልቅ የሆነውን እውነት ሙሉ በሙሉ ልንረዳው አንችልም፣ ነገር ግን ይህንን አስደናቂ አምላክ ልናመልከውና ልንወደው እንችላለን።

እግዚአብሔር አብ በልጁ በኢየሱስ በሚገባ ተደስቷል። ይህም የሚያረጋግጠው ጌታ ኢየሱስ ምንም ኃጢአት እንዳልሠራ ነው፤ ማቴ.12፡18፤ ሉቃ.9፡35። የጌታ ኢየሱስ ደስታ የአባቱን ፈቃድ ማድረግ ነው፤ መዝ.40፡7-8። የአብ ደስታ ደግሞ በዚህች ዓለም ልጁ ያለ ኃጢአት ሲኖር ማየት ነበር። ሌላ ማንም ያለ ኃጢአት የኖረ ሰው የለም።

2. የማሪያም የዘር ሐረግ 3፡23-38

ቄስ ወይም ሌዋዊ 30 ዓመት ሲሆነው ጌታን ለማገልገል ይጀምራል፤ ዘኍ.4፡3። ጌታ ኢየሱስም ሥራውን በጀመረ ጊዜ ተመሳሳይ ዕድሜ ነበረው፤ 3፡23። ሰዎች እርሱ የዮሴፍ ልጅ ነው ብለው አሰቡ። መንፈስ ቅዱስ በእናቱ በማሪያም ላይ እንደወረደ አላወቁም፤ 1፡35።

ሌላው የዚህ ምዕራፍ ክፍል ከዮሴፍ እስከ አዳም ያለውን የሰዎች የስም ዝርዝሮች ያቀርባል። ይህን የመሰለ የአባቶችና የልጆች ስም ዝርዝር የዘር ሐረግ ይባላል። ሌላው የጌታ ኢየሱስ የዘር ግንድ በማቴዎስ ይገኛል፤ ማቴ.1፡1-16። በማቴዎስ ዝርዝሩ ከአብርሃም ጀምሮ እስከ ዮሴፍ የማሪያም ባለቤት ድረስ ነው። ምንም እንኳ በተገላቢጦሽ ቅደም ተከተል ቢሆንም በማቴዎስ የተዘረዘሩት ስሞች ከአብርሃም ጀምሮ እስከ ዳዊት ያለው በሉቃስ ከተዘረዘረው ጋር አንድ ነው፤ ማቴ.1፡2-6፤ ሉቃ.3፡31-34። ከዳዊት እስከ ዮሴፍ /የማሪያም ባለቤት/ ያለው ዝርዝር በማቴዎስና በሉቃስ ያለው የተለያየ ነው። ዳዊት ብዙ ልጆች ነበሩት። ነገር ግን ሁለት የታወቁ ልጆች ሰለሞንና ናታን ነበሩ፤ 2ሳሙ.5፡14። በሰለሞን በኩል ያለው የዳዊት የዘር ሐረግ በማቴዎስ ይገኛሉ በሉቃስ ደግሞ በናታን በኩል ያለውን የዘር ሐረግ እናገኛለን።

ይህ ልዩነት ለምን ሆነ? ዮሴፍ /የማሪያም ባለቤት/ የሁለት የተለያዩ ሁለት አባቶች ልጅ ማለት የያዕቆብና የኤሊ ልጅ ሊሆን አይችልም፤ ማቴ.1፡16፤ ሉቃ.3፡23። ይህንን ለማስረዳት ሉቃስ ሲጽፍ ዮሴፍ የኤሊ ልጅ ነበረ። አለማለቱን እንገነዘባለን፤ ነገር ግን «የኤሊ» ብቻ ነው ያለው። አንዳንድ የመጽሐፍ ትርጉሞች ልጅ የሚለውን ቃል ይጨምራሉ። ነገር ግን በቆየው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም። ከዚህም መረዳት የሚገባን ዮሴፍ የኤሊ እንጀራ ልጅ መሆኑን ነው። ማሪያምም የኤሊ ልጅ ነበረች። ይህም ማለት በሉቃስ ወንጌል የምናገኘው የማሪያምን የዘር ሐረግ ሲሆን በማቴዎስ ወንጌል ደግሞ የዮሴፍን የዘር ሐረግ እናገኛለን። ዮሴፍ በሰለሞን በኩል የዳዊት ዘር ነው፤ ማቴ.1፡20። ዳዊትም የማሪያም ልጅ አባት ወይም ዘር እየተባለ ይጠራል፤ ሉቃ.1፡32። ስለዚህ ዳዊት በናታን በኩል የማሪያም ዘር ነው። ዮሴፍ የጌታ ኢየሱስ እውነተኛ አባት አይደለም፤ ነገር ግን የማሪያም ባለቤት ስለሆነ በሕጉ መሠረት የጌታ ኢየሱስ አባት ነው።

ይህ ደግሞ በኤርምያስ ያለውን አስቸጋሪ ጥቅስ ለመረዳት ያስችላል፤ ኤር.22፡30። የይሁዳ ንጉሥ አኮኒያን የሰለሞን ልጅ ነበር። ይህ ጥቅስ የአኮኒያን ልጅ የሆነ ማንም የዳዊትን ዙፋን አይወርስም ይላል። ዮሴፍ የአኮኒያን ልጅ ነበር፤ ማቴ.1፡12። ዮሴፍ

የጌታ ኢየሱስ እውነተኛ አባት ቢሆን ኖሮ ኢየሱስ የአኮኒያን ዘር ይሆን ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ በዳዊት ዙፋን ላይ ሆኖ አይነግሥም ነበር፤ ኤር.22:30። ማቴዎስ ምዕራፍ አንድንና ሉቃስ ምዕራፍ ሦስትን አንድ ላይ በማገናኘት ጌታ ኢየሱስ በማሪያም በኩል እውነተኛ የዳዊት ልጅ እንደሆነ እንመለከታለን። የእግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ተፈጸመ፤ ሉቃ.1:32-33። አንዳንድ ሰዎች ስሕተት አለበት ብለው ስለሚገምቱ በመጽሐፍ ቅዱስ አያምኑም። ነገሮችን በጥንቃቄ በማገናዘብ እነዚህን ልዩነቶች ማስወገድ ይቻላል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ በዳዊትና በአዳም መካከል ስለነበሩ ሰዎች በመጠኑ እናነባለን። የሰለሞን ዘሮች በይሁዳ ነገሡ። የእነርሱም ታሪክ በመጽሐፈ ነገሥትና በመጽሐፈ ዜና ይገኛል። ከናታን በኋላ ስለኖሩት ስለሌሎች ሰዎች ምንም አናውቅም፤ ሉቃ.3። ከዘሩባቤል በስተቀር ከኢኮኒያም በኋላ ስለነበሩት የሚታወቅ የለም፤ ማቴ.1:12፤ ዕዝራ 3:2።

ሉቃስ ከአሕዛብ ወገን ነበር፤ ነገር ግን የሁሉም አባት ከሆነው ከአዳም አንሥቶ ያለውን የጌታ ኢየሱስን የዘር ሐረግ ይዘረዝራል። ማቴዎስ በይሁዳዊያን በኩል ያለውን ጻፈ፤ ስለዚህ የጌታ ኢየሱስን የዘር ሐረግ እስከ አብርሃም ያለውን ብቻ ጽፎአል። የእግዚአብሔር መልካም ዜና ለሁሉም ሰዎች በመሆኑ ደስ ይለናል። ሉቃስ መንፈስ ቅዱስ እየመራው ከማቴዎስ የበለጠ እውነቱን ግልጽ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ የምንረዳው ይህንን መልካም ዜና ለሁሉም ሰዎች ማድረስ እንዳለብን ነው።

3. ሰይጣን ጌታ ኢየሱስን ፈተነው 4:1-13

ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ከእግዚአብሔር ሕዝቦች ወገን መሆኑ ለሁሉም ሰዎች አሳይቷል። በእናቱ በማሪያም በኩል የጌታ ኢየሱስን የዘር ሐረግ ስንመለከት ክርስቶስ ሰው እንደሆነና የሰውም ልጅ እንደሆነ ነው። ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ፈታኙ ሰይጣን በፊቱ ተደቀነ። ሰይጣን እንደ አንድ ጠንካራ ሰው ነበር፤ ሉቃ.11:21-22። ሰይጣን ከእርሱ የበለጠ ጠንካራ እስካልመጣ ድረስ ሰዎችን በባርነት ለማቆየት ችሎታ አለው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያ ሰይጣን በፈተነው ጊዜ አሸነፈው፤ ከዚያም የኃጢአት ባሮችን ነፃ አወጣ፤ ጌታ ሥራውን ጀመረ፤ ሉቃ.4:14።

በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለፈታኙ ምን እንደሚያስተምር እንመልከት። እርሱም ዲያብሎስ እንዲሁም ሰይጣን ተብሎ ይጠራል፤ ቁ.2፤ ማቴ.4:10። በእግዚአብሔርና በልጁ የተፈጠረ ነው፤ ቆላ.1:16። በመጀመሪያ መልካም መልአክ ነበረ፤ ስሙም የንጋት ኮከብ ይባል ነበር። እርሱም ከእግዚአብሔር ፍጡር ሁሉ ኃጢአት ለመሥራት የመጀመሪያው ነበር። ይህም የሆነው «ራሴን እንደ ታላቁ አደርጋለሁ» ባለ ጊዜ ነበር፤ ኢሳ.14:12-14። ሰይጣን እንደ እባብ ሆኖ ሔዋንን ፈተነ፤ ዘፍ.3:1። አዳምና ሔዋንም በኃጢአት ወደቁ። ሰይጣን አሁንም ሰዎችን ለመፈተን ይጥራል፤ ነገር ግን በመጨረሻ ወደ እሳት ባሕር ይወረወራል፤ ራዕይ 20:10።

በዚህ ምዕራፍ ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር፤ 4:1። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ለጌታ ኢየሱስ በመለኪያ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ነው የሰጠው፤ ዮሐ.3:34። መንፈስ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስን ወደ ምድረ በዳ መራው። ለአርባ ቀናትም ፈተነው።

እግዚአብሔር ግንንም በኃጢአት አይፈትንም፤ ያዕ.1:13። ጌታ ኢየሱስ ወደ ፈተና እንዳንገባ መጸለይ እንዳለብን አስተምሮናል፤ 11:4፤ 22:40። እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል፤ ምን ያህል ደካሞችም እንደሆንን ያውቃል። አንዳንድ ጊዜ እንደ አብርሃም እንድንፈተን ይፈቅድልናል፤ ዘፍ.22:1። ሰይጣን ሁልጊዜ በአእምሮአችን ጥርጣሬ እንዲገባ ለማድረግ ዝግጁ ነው፤ ወደ ኃጢአትም እንድንገባ ከቻለ ያደርጋል። ኢዮብን ሰይጣን እንዲፈትነው እግዚአብሔር ፈቅዷል። በመጀመሪያ ኢዮብ የነበረውን ሁሉ ሰይጣን ወሰደበት። የኢዮብ ልጆች ተገደሉበት። ከዚያም ኢዮብ በጣም ታመመ፤ ኢዮ.1:6-2:8። ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት እንዲፈትን ሰይጣን ተፈቀደለት፤ 22:31-32። ሰይጣን ጳውሎስን ለመጉዳት መልእክተኛ ላከ። ጳውሎስ በጣም እንዳይኩራራ እግዚአብሔር ይህንን ፈቀደ። የእግዚአብሔር ፀጋና ኃይል ለማንኛውም ፈተና በቂ እንደሆነ ጳውሎስ ተረዳ፤ 2ቆሮ.12:7 እና 10። መፈተን ኃጢአት አይደለም፤ ነገር ግን ራስን ወደ ፈተና ማግባት ኃጢአት ነው። ስለ ኃጢአት ማሰብ ሊያስደስተን ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ በተፈተነ ጊዜ ተሠቃየ፤ ዕብ.2:18። በእርሱ ውስጥ ግን ኃጢአት አልነበረም።

በዚህች ዓለም በጣም አስከፊ የሆነ መንፈሳዊ ትግል አለ፤ ኤፌ.6:12። ሰይጣንና አገልጋዮቹ እግዚአብሔርንና ወገኖቹን ይጠላሉ። ጌታ ኢየሱስን መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድረ በዳ መራው፤ ሰይጣንም ፈተነው። ጌታ ኢየሱስ ሰው እንደመሆኑ መጠን ከአርባ ቀን ጾም በኋላ በጣም ተራበ። ሰይጣን አብዛኛውን ጊዜ የሚፈትነን ሰውነታችን በደከመ ጊዜ ወይም በታመመ ጊዜ ነው። የክርስቲያን ሰውነት የእግዚአብሔር ስለሆነ ልንከባከበው ይገባል፤ 1ተሰ.5:23።

ሰይጣን ጌታ ኢየሱስን ተናገረው፤ በኃጢአት እንዲወድቅ ሦስት ጊዜ ፈተነው። በመጀመሪያ «የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እነዚህን ድንጋዮች ዳቦ አድርጋቸው» አለው። እርግጥ ሰውነቱ የሚያስፈልገውን ምግብ መብላት ለጌታ ኢየሱስ ኃጢአት አይደለም። እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ ድንጋይን ወደ ዳቦ ለመለወጥ ኃይል ነበረው። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ሁልጊዜ አባቱ ያለውን ብቻ ያደርግ ነበር። በራሴ ሥልጣን የማደርገው አንዳችም ነገር የለም ማለት ይችል ነበር፤ ዮሐ.8:28። ጌታ ኢየሱስ የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል በመድገም ሦስት ጊዜ በሰይጣን ላይ ድል አገኘ፤ 4:4፤ 8 እና 12። የእግዚአብሔር ቃል እንደ መንፈስ ሰይፍ ነው፤ እርኩስን ልንዋጋበት እንችላለን፤ ኤፌ.6:17። ጌታ ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ ሲያስተምር ከተለያዩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ይጠቅስ ነበር። በፈተናው ጊዜ ዘዳግምን ብቻ ተጠቀመ፤ 8:3፤ 6:13 እና 16። የዘዳግም መጽሐፍ ሙሴ ከመሞቱ በፊት ያስተማረውን ይዟል። እግዚአብሔር ከግብፆች እንዳዳናቸው ለእስራኤል ሕዝብ ይነግራቸው ነበር፤ እንዲሁም በምድረ በዳ በሚጓዙበት ጊዜ ከጠላቶቻቸው ሁሉ አዳናቸው፥ ረዳቸውም። በዘዳግም

ውስጥ ዋናው ትምህርት የሰው ኃላፊነት ወደ እግዚአብሔር መምጣት መሆኑን ነው። «ሰው በእህል ብቻ አይኖርም» አለ፤ ማቴ.4:4። እግዚአብሔር የሚናገረው ቃል ያስፈልገናል አለ። ብዙ ሰዎች ምግብ በመፈለግ ጊዜያቸውን ያጠፋሉ፥ ደስታንም በዚህች ዓለም ይሻሉ። ለእውነተኛ ደስታ የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልገናል። ክርስቲያኖችም እንኳ ቢሆኑ የእግዚአብሔር ቃል ትንሽ ካወቁ ይረካሉ። በእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቃል ለመኖር መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ማንበብ አለብን።

ሰይጣንም የዓለምን ግዛት በሙሉ በአንድ ጊዜ ለጌታ ኢየሱስ አሳየው። ሰው ሊያደርገው የማይችለውን ሰይጣን አስደናቂ ነገሮችን ሊያደርግ ይችላል። ተአምራት የሚሠራውን ዝም ብለን ማመንና መከተል የለብንም፥ ማቴ.24:24። በማንኛውም በኩል እንደ እግዚአብሔር ቃል መሄድ አለብን። ጌታ ኢየሱስ ለሰይጣን ወድቆ ቢያመልከው የዓለምን ክብር እንደሚሰጠው ተናገረው። ሰይጣን አሁንም ሰዎችን የዓለምን ክብር ሁሉ እሰጥሃለሁ እያለ ወደ ኃጢአት እንዲገቡ ለመፈተን ይሞክራል። አንዳንድ ክርስቲያኖች በጨዋታዎችና በስፖርት ክብር ይፈልጋሉ፥ አንዳንዶችም ወደ ኮሌጅ በመግባት አንዳንድ ክርስቲያኖች ከፍተኛ ቢሮዎችን ለማግኘት በመጣር የዚህን ዓለም ክብር ለማግኘት ይፈልጋሉ።

ጌታ ኢየሱስ ሰይጣንን ለእግዚአብሔር አምላክ መስገድ አለብን፥ እርሱም ብቻ ግገልገል ይገባናል አለው። ምስሎቹን ወይም ሌሎች አማልእክትን ማምለክ አይገባንም። እግዚአብሔርን ማምለክ በጣም አስፈላጊ ነው፥ ዮሐ.4:23-24። ማርያም ልታመልከው በጌታ እግሮች ሥር ተቀመጠች፥ ማርታም አገለገለችው፥ ሉቃ.10:39-42።

በሦስተኛው ጊዜ ሰይጣን እራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ በጥቅስ ተጠቀመ፥ መዝ.91:11-12። እግዚአብሔር በመዝ.91 ለክርስቶስ ብዙ ቃል ኪዳን አድርጓል። እግሮቹን ከድንጋይ ጋር ቢያጋጭ እንኳን የእግዚአብሔር መላእክት ከመውደቅ ያድኑታል። ስለዚህ ሰይጣን ጌታ ኢየሱስን ከቤተ መቅደሱ ጫፍ ላይ ቁልቁል ዝለል፥ እስቲ እግዚአብሔር ይጠብቅህ አለው። በዚያን ጊዜ የነበሩት አይሁዳውያን መሲሁ በአስደናቂ ሁኔታ ይመጣል ብለው ግምት ነበራቸው። ጌታ ኢየሱስ በድንገት ከሰማይ ወርዶ ቢሆን ኖሮ ይሁዳዊያን እንደ ንጉሣቸው በተቀበሉት ነበር።

ሰይጣን ዛሬም ሰዎች እንዲከተሉት ሙከራ በሚያደርግበት ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቀማል። የተሳሳተ ትምህርትን እውነት ለማስመሰል መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም ይችላል። ሰይጣን እኛን ለማታለል መጽሐፍ ቅዱስን በሚጠቀምበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ጌታ ኢየሱስ በመዝሙረ ዳዊት ምዕ.91 ያለውን ያውቅ ነበር። ሰይጣን ቁጥር 11 እና 12 ደጋግሞ አለ፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ከዚያ ባለው ቁጥር ሳይጽናና እንዳልቀረ ጥርጥር የለውም። ይህ ጥቅስ መሢሁ አንበሳንና እባብን ለማሸነፍ ይችላል ይላል፤ መዝ.91:13። አንበሳውና እባቡ ሁለቱም የሰይጣን ምሳሌዎች ናቸው፤ 1ጴጥ.5:8፤ ራዕይ 12:9። ጌታ ኢየሱስ መጨረሻው ጊዜ በሰይጣን ላይ ድልን ይጐናፀፋል፤ ሉቃ.10:18። እዚህ ላይ ግን ጌታ እንደገና የእግዚአብሔርን ቃል ተጠቀመ። እግዚአብሔር ቃሉን ይጠብቅ እንደሆነ ለማየት

እግዚአብሔርን አልፈተነም። እግዚአብሔር እግሮቹ ከድንጋይ ቢጋጩ እንደሚጠብቀው ቃል ገብቷል። ነገር ግን ከከፍተኛ ቦታ ቢዘል አላለም። እግዚአብሔር እንደሚጠብቀን ቃል ገብቷል፤ ይሁዳ 24፤ ነገር ግን በእርሱ ላይ ኃጢአት እየሠራን ልንፈትነው አይገባም።

ከዚህ በኋላ ሰይጣን ጌታ ኢየሱስን ለጊዜው ተወው፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ብዙ ፈተናዎች ነበሩበት፤ ሉቃ.22፡28፤ ዕብ.2፡18-4፡15። በእነዚህ ሁሉ ፈተናዎች ጌታ ኢየሱስ አሸንፎ ነበር። አንዳንድ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ እንደማንኛውም ሰው ኃጢአት ሊሠራ ይችላል ብለው ያስባሉ። እነዚህ ሰዎች ኃጢአት ምን እንደሆነና ክርስቶስም ማን እንደሆነ አልገባቸውም። ኃጢአት እግዚአብሔር የሚጠላውን ማድረግ ነው። ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ፍጡር አልነበረም። እርሱ አምላክ ነበር፤ ነውና፥ ለዘላለምም ይሆናል፤ ዮሐ.10፡30። እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው። እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ፈቃድ የተለየ ለማድረግ አይቻለውም። በፈተና ጊዜ ለሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል መመለስ እንዳለብን ጌታ ኢየሱስ ምሳሌ ሆኖልናል። እንደ እኛ ሰዎች የሆኑ ሰይጣንን በእግዚአብሔር ኃይል ማሸነፍ ስለቻሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ምሳሌ እናገኛለን። ከሁሉም የሚበልጠው ትምህርት ክርስቶስ በኃጢአት አለመውደቁ ነው፤ እንደዚህ ዓይነት አዳኝ ነው የሚያስፈልገን።

በማቴዎስ ምዕ.4 የመጨረሻዎቹ ሁለት ፈተናዎች በተለያየ ቅደም ተከተል ናቸው። የሰይጣን ቃላት የፈተናው ሦስተኛ ክፍል ነበሩ፤ ሉቃ.4፡5-7። ከሦስተኛው ፈተና በኋላ ጌታ ኢየሱስ ሰይጣን ከፊቱ እንዲሄድ ገሰጸው፤ ሰይጣንም ሄደ፤ ማቴ.4፡10-11። በሉቃስ ውስጥ የሚገኘው ፈተና ቅደም ተከተል ደግሞ ሦስት ነገሮችን ያስከትላል፤ 1ዮሐ.2፡16። ሔዋን በኤደን ገነት ውስጥ ስለ ፍሬው በተመሳሳይ ሁኔታ አሰበች፤ ዘፍ.3፡6።

1ዮሐ.2፡16	ዘፍ.3፡6	ሉቃ.4፡1-13
የሥጋ ፍላጐት	ለምግብ መልካምነት	ድንጋይን ዳቦ ማድረግ
የዓይን አምሮት	ለዓይን አስደሳችነት	የዓለም ክብር
የኑሮ ትምክሕት	ብልህ ያደርገናል	የእግዚአብሔር ልዩ ቃል ኪዳን

እነዚህ ሦስት ነገሮች የሥጋ ፍላጐት፥ የዓይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት ከዓለም ናቸው እንጂ ከአብ አይደሉም። ዓለም አብን ከመውደድ ታግደናለች፤ የአብ ፍቅርም ዓለምን ከመውደድ ያስጥለናል። ሔዋን እግዚአብሔርን ከመውደድ ይልቅ ከፉ እንደሆነ ገመተች። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አብን ወደደ፤ በሰይጣንም ላይ ድልን ተቀዳጀ። እኛም በእግዚአብሔር ከተማመንን በተመሳሳይ ሁኔታ ድል እናደርጋለን፤ 1ዮሐ.5፡4።

3. የጌታ ሥራና ትምህርት በገሊላ 4:14-9:62

ጌታ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት የእስራኤል ሕዝቦችን ለሦስት ዓመታት ያህል አስተማረ። በመጀመሪያው ዓመት እስከዚህም የታወቀ አልነበረም። በዚህም ዓመት የሆነውን በጥቂቱ በዮሐንስ እናነባለን፤ ዮሐ. 1:19-4:54። በሁለተኛው ዓመት ብዙ ሰዎች ጌታ በሄደበት ይከተሉት ነበር። ጌታ ኢየሱስ የታመሙትን ፈወሰ፤ የሞቱትንም አስነሣ። የጌታ ኢየሱስ አስደናቂ ሥራዎች በአፋጣኝ ተሰራጩ። ቁጥራቸው ብዙ የሆነ ሰዎችም ወደ እርሱ መጡ። ይህም ስለ እግዚአብሔር ለማስተማር መክፈቻ ሆነለት። እግዚአብሔር ሰዎችን ይወዳል፤ ኃጢአታቸውንም ይቅር ሊላቸው ዝግጁ ነው ብሎ አስተማረ። በሦስተኛው ዓመትም ብዙ ሰዎች ይከተሉት ነበር፤ ነገር ግን ጠላቶቹ እያየሉ መጡ። ጌታ ኢየሱስ የሁለተኛ ዓመት ሥራውን አብዛኛውንና የሦስተኛ ዓመቱን ግማሽ የሚሆነውን ጊዜ በሰሜናዊ ገሊላ ነበር። በዚህ ጊዜ የሆነውንም ታሪክ በሉቃስ እንዲሁም በማቴዎስና በማርቆስ ወንጌሎች እናነባለን፤ ሉቃ. 4:9። ከዚያም በኋላ በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ወደሚገኘው ፐሪያ ወደተባለ አገር ሄደ። ስለዚህም በሉቃስ 10-19 እናነባለን።

1. የመጀመሪያ ጉዞ 4:14-6:49

ጌታ ኢየሱስ ሁለት ጉዞዎችን በገሊላ አደረገ። እነዚህም አንደኛውና ሁለተኛው ጉዞ ተብለው ይጠራሉ። በመጀመሪያ የትውልድ ከተማውን ናዝሬትን ጐበኘ፤ 4:16-30። እዚያ ያሉት ሕዝቦች እንደአስተማረ አይቀበሉትም፤ ስለዚህ በገሊላ ወንዝ ዳርቻ ወደምትገኝ ቅፍርናሆም ሄደ፤ 4:31፤ ማቴ. 4:13። ከዚያ ብዙ የገሊላን ከተሞች ጐበኘ፤ ሉቃ. 4:6፤ በኋላም ወደ ቅፍርናሆም ተመለሰ፤ 7:1። ይህ የመጀመሪያ ጉዞው ነበር። ሁለተኛው ጉዞውን በገሊላ በሉቃ. 8 እና 9 እናነባለን። ጌታ ለመጨረሻ ጊዜ ከገሊላ ወጥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፤ 9:51።

ዮሐንስ ካጠመቀውና ሰይጣን ከፈተነው በኋላ ጌታ ለታላቅ ሥራው ተዘጋጀ። መንፈስ ቅዱስ በሙሉ ኃይሉ ከእርሱ ጋራ ነበረ፤ 4:14። ይህም የሚያሳየን ጌታ ለሰይጣን እንዳልተሰጠና በኃጢአትም እንዳልወደቀ ነው። ወደ ገሊላ በመጣ ጊዜ ወዲያው ታዋቂ ሆነ። ይሁዳዊያን በሰባተኛው ቀን የሚሰበሰቡበት በእያንዳንዱ ከተማ ምኩራብ ነበረ። ጌታም ወደ ምኩራቡ ገብቶ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምር ነበር፤ 4:15።

ናዝሬት 4:16-30

ጌታ ኢየሱስ በመጀመሪያ ወደ ናዝሬት ተመለሰ። በሰባተኛውም ቀን ወደ ምኩራብ ገባ። ከኢሳይያስ 61 ቁጥር 1 እና 2 እንዲያነብ ተሰጠው። እያንዳንዳቸው ኢየሱስን ይመለከቱት ነበር። እርሱም እነዚህ ቃላት በዚያን ቀን ተፈጸሙ አለ። በመጀመሪያ በንግግሩ መብሰል የተነሣ እያንዳንዳቸው ተደነቁ።

የእግዚአብሔር መንፈስ በጌታ ኢየሱስ ውስጥ እንደነበር አይተናል፤ 4:1፤ 14፤ 18። የእርሱ ሥራ መልካሙ ዜና ለድሆች መሰበክ እንደሆነ ለሰዎች ተናገረ። የታወሩ ዓይኖቻቸው ባሮችና በሰይጣን ዓይናቸው የታወረውን ነፃ ለማውጣት መጣ። በእምነት ወደ እርሱ የሚመጡትን ለመቀበል ጊዜው የእግዚአብሔር ፀጋ የበዛበት ነበር፤ 4:19። አሁንም በእግዚአብሔር ፀጋ ውስጥ ነን፤ 2ቆሮ.6:2። ጊዜው ካለፈ ግን ማንም የእግዚአብሔርን ይቅርታ ሊያገኝ አይችልም፤ 25:11-12። ጌታ ኢየሱስ የጥቅሶቹን የመጨረሻ ክፍል እንኳ አላነበበም፤ ኢሳ.61:2። እግዚአብሔር ሰዎችን ስለሚቀጣበት ቀን ይናገራል። የእግዚአብሔር ፀጋ ባለቀ ጊዜ ግን ታላቅ ችግር ይሆናል። ልጁን ያልተቀበሉትን ሁሉ ይፈርድባቸዋል። ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፀጋ ለማብሰር በመጀመሪያ መጣ። ለሁለተኛ ጊዜ ግን በዓለም ላይ ለመፍረድ ይመጣል።

በዓለም ላይ አሁንም ብዙ የመንፈስ ድሆች አሉ፤ እኛም ክርስቲያኖች ለእርሱ ወንጌልን ለማስተላለፍ ታዘናል።

በዚያን ቀን የናዝሬት ሕዝቦች እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስን የዓለም መድኅን እንዲሆን መላኩን ለማመን ዝግጁ አልነበሩም። ጌታን እንደ ዮሴፍ ልጅ፥ እንደ ማንኛውም ተራ ሰው በከተማቸው ያደገ አድርገው ቆጠሩት፤ 4:22። አንድ ቀን ራስህን አድን እንደሚሉት ነገራቸው። የእነርሱም ገዢዎች ጌታ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ ይህንኑ አደረጉ፤ ሉቃ.23:35። ሕዝቦችም በናዝሬት ድንቅ ሥራዎችን እንዲያደርግ ይፈልጉታል፤ በቅፍርናሆም እንዳደረገው ሁሉ ጌታ ኢየሱስ እንደማይቀበሉት አወቀ።

አንድም ነቢይ በአገሩ ተቀባይነትን አላገኘም አላቸው፤ 4:24-27። ሁለት ታላላቅ የእስራኤል ነቢያት ለሌላ አገር ሰዎች ድንቅ ሥራዎችን አደረጉ። ኤልያስ በሲዶና ለአንዲት ድሃ ሴት ምግብ ሰጣት፤ 1ነገ.17:8-16። ኤልያስ የሦሪያን ሰው ንዕማንን በእግዚአብሔር ኃይል ፈወሰው፤ 2ነገ.5:1-14። ይህም የሚያሳየው ካመኑት እስራኤላውያን ይልቅ በእግዚአብሔር ላይ የበለጠ እምነት ያላቸውን ከሌላ ቦታ የመጡትን እንደሚባርክ ነው። በምኩራቡም ውስጥ የነበሩት ሰዎች ይህንን ሰምተው በጣም ተናደዱ። ጌታ ኢየሱስን ከተራራ ጫፍ ላይ ወርውረው ለመግደል ሞከሩ። ጌታ ኢየሱስ ግን አልፈራም። የእነርሱም ድክመት በግልጽ እንዲታይ ከእነርሱ ጋር አብሮ ወደ ተራራው ጫፍ ላይ ወጣ። በሕዝቡም መካከል ተራምዶ ሄደ። ማንም ሊነካው አልደፈረም፤ ነገር ግን የናዝሬት ሕዝቦች ጌታ ኢየሱስ አብሮአቸው እንዲሆን እንዳልፈለጉ ግልጽ ነው፤ 4:28-31።

ቅፍርናሆም 4:31-44

ከናዝሬት 32 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ወደምትገኘው ቅፍርናሆም ሄደ። ሉቃስ በቅፍርናሆም ስለተፈጸመው ሁለት ድርጊቶችን ይነግረናል፤ አንደኛው በምኩራብ ውስጥ ሲሆን ሌላው ደግሞ በጴጥሮስ ቤት ነው። ጌታ ኢየሱስ በምኩራብ በሚያስተምርበት ጊዜ በሥልጣን ቃል ስለሚናገር ሕዝቡ ተደነቁ፤ 4:32። በትሕትና እንደተናገረ፤ በቁ.22 ላይ ተመልክተናል። የሕግ አስተማሪዎች በሥልጣን ቃል

አልተናገሩም፣ ማቴ.7:29። ጌታ ኢየሱስ ግን እውነተኛ ሥልጣን እንዳለው አሳየ፣ ርኩስ መንፈስን ከሰው እንዲወጣ አዘዘ። የእግዚአብሔር ልጅ መናፍስትንና መላእክትን ሁሉ ፈጠረ፣ ቆላ.1:16። ከእነዚህም አንዳንድ መናፍስት ሰይጣንን ተከትሉ፣ ለእግዚአብሔር አልታዘዙም፣ አንዳንድ ጊዜ በሰው ሕይወት ውስጥ እየገቡ ወደ ኃጢአት ይመሩታል። ርኩስ መንፈስ በክርስቲያን ሰውነት ውስጥ ሊኖር አይችልም፣ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ ስለሆነ ነው።

ይህ ርኩስ መንፈስ ጌታ ኢየሱስ ማን እንደሆነ ስለሚያውቅ ክርስቶስ ያለውን መቀበል ነበረበት። አጋንንት በእግዚአብሔር ያምናሉ፣ ነገር ግን ይዋጥታል፣ ያዕ.2:19። ሰዎችም በጌታ ኢየሱስ ኃይል ተደነቁ፣ በመላ አገሩ ያሉትም ሌሎች ስለተፈጸመው ነገርና ስለ እርሱ ሰሙ።

ስምዖን ጴጥሮስ በቤተሳይዳ ይኖር ነብር፣ ዮሐ.1:44። ነገር ግን እርሱም ወደ ቅፍርናሆም ሄደ። ጌታ ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ቤት በሄደ ጊዜ የሚስቱ እናት ታማ አገኘ። ጌታ ኢየሱስም አዳናትና ተነሥታ አገለገለቻቸው፣ 4:38-39። በማቴዎስ አገለገለችው ይላል፣ ማቴ.8:15። ሁለቱም እውነት ናቸው። የእግዚአብሔርን ሰዎች በረዳን ጊዜ እግዚአብሔርን ማገልገላችን ነው። ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው ጴጥሮስ አግብቶ ነበር። በኋላም ጴጥሮስ /ኬፋ/ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ በወጣ ጊዜ ሚስቱንም ይዟት ሄደ፣ 1ቆሮ.9:5። ዛሬ ብዙ ሰዎች ሚስት ያላገቡ የበለጠ ቅዱሳን ናቸው ብለው ያስባሉ። ጴጥሮስ ሚስት እንደነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ሌሎችም ሐዋርያት እንዲሁ ነበራቸው። በዚያን ምሽት ወደ ጌታ ኢየሱስ ብዙ ሰዎች መጡ። ሁሉንም ፈወሳቸው። አጋንንት የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አወቁ፣ ነገር ግን ስለ እርሱ እንዲናገሩ አልፈቀደላቸውም፣ 4:40-41። ጌታ ኢየሱስ ከሰይጣን ምንም ዓይነት ዕርዳታ አልፈለገም፣ እኛም የእርሱ ተከታዮች እንደእርሱ መሆን አለብን። ጳውሎስና ሲላስ በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ከነበረችው ልጃገረድ እርዳታ አልተቀበሉም፣ የሐዋ/ሥራ 16:16-18።

ጌታ በሚቀጥለው ቀን ወደ ገለልተኛ ቦታ ብቻውን ሄደ፣ ሰዎች ግን ተከተሉት፣ 4:42-44። ከእነርሱ ጋር እንዲቆይ ፈለጉ፣ ነገር ግን ይህንን መልካም ዜና ለሌሎችም ከተሞች መስበክ ነበረበት። ሉቃስም በዚህን ወቅት ጌታ ኢየሱስ በይሁዳ እንዳስተማረ ይገልጽልናል። ይህ በተለይ ለመጀመሪያው ዓመት የጌታ አገልግሎት እውነት ነበር። በሁለተኛ ዓመት አገልግሎቱ ወቅት ብዙ ሰዎች ተከተሉት። እርሱም ሁሉንም ፈወሳቸው። ከዚያም የእግዚአብሔርን ቃል አስተማራቸው። ሰዎች በሚያዳምጡን ጊዜ የእግዚአብሔርን ፀጋ መልካሙን ዜና ልንነግራቸው ይገባናል።

ጌታ ኢየሱስ ሦስት ደቀ መዛሙርትን ጠራ፤

5:1-11

አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ በገሊላ ባሕር ዳርቻ ያስተምር ነበር፣ ብዙ ሰዎችም እርሱን ለመስማት ተሰብስበው ነበር። በጴጥሮስ ጀልባ ላይ ሆኖ ሕዝቡን ማስተማር ይችል

እንደሆነ ስምዖን ጴጥሮስን ጠየቀው፤ 5:1-3። ስምዖን ጴጥሮስ ጌታን ከብዙ ወራት በፊት ያውቀው ነበር። ወንድሙ እንድሪያስ ወደ ክርስቶስ መራው፤ ዮሐ.1:40-42። ጌታ ኢየሱስን በማናቸውም መንገድ ለመርዳት ደስተኛ ሆነ፤ ነገር ግን ጌታ ጴጥሮስ ሰለረዳው ሊሸልመው ፈለገ። ወጥቶ ዓሣ እንዲያጠምድ ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን ላከው። ጴጥሮስ በገሊላ ባሕር ውስጥ ዓሣ ማጥመድ ያውቅ ነበር። እያንዳንዳቸውም በምሽት ብዙ ዓሣ እንደሚያጠምዱ ያውቁ ነበር። ጴጥሮስም ጌታ ኢየሱስን ሌሊቱን ሁሉ ለፋን፥ ነገር ግን አንድም ዓሣ ለማጥመድ አልቻልንም አለው። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ያለውን ያደርጋል፤ 5:5።

ጴጥሮስ እዚህ ላይ ጥሩ ምሳሌ ያሳየናል። ምንም እንኳ ሊገባን ባይችልም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመቀበል ፈቃደኞች መሆን አለብን።

ጴጥሮስ ለጌታ ታዘዘ፤ ቁጥሩ እጅግ የበዛ ዓሣም አጠመደ። ጓደኞቹን ለእርዳታ ጠራት ነበረበት። ዓሣው ከመብዛቱ የተነሣ ሁለቱም ጀልባዎች ወደ ባሕር መስጠም ጀመሩ፤ 5:6-7። ጴጥሮስ ይህንን ሁሉ ዓሣ ወደ መረቡ ሊያመጣ የሚችል ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ መሆኑን አወቀ። በጌታ ፊት ወድቆ ከእጠገቡ እንዲርቅ ጠየቀው፤ ምክንያቱም ኃጢአተኛ ነበረ። ይህን መናገር በጣም መጥፎ ነገር ነበር። ጌታን ከእኛ እንዲርቅ ፈጽሞ መጠየቅ አይገባንም። ጴጥሮስ የጠየቀውን ጌታ ኢየሱስ አለማድረጉ ለጴጥሮስ ጥሩ ነበር። ጌታ እንዳይፈራ ነገረው። ከአሁን ወዲያ በዓሣ ፋንታ ሰዎችን ማጥመድ ይችላል ይህም ማለት ጴጥሮስና ሌሎችም ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት ይችላሉ ማለት ነው። ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ ይህንን ሲሰሙ ደስ አላቸው። እነርሱም መረባቸውን ትተው ጌታ ኢየሱስን ለመከተል ፈቃደኞች ነበሩ፤ 5:11። እንድሪያስም ከአንዱ ጋር ነበር፤ ማቴ.4:18፤ ማር.1:16-20።

ከዚህ ታሪክ ውስጥ ስምዖን ጴጥሮስን የምንመለከተው፡-

1. ጌታ ኢየሱስ ጀልባውን እንዲጠቀምበት መርዳቱን፤ 5:1-3

2. ነገሩ ባይገባውም እንኳ ለጌታ መታዘዙን፤ ቁ.4-7

3. ኃጢአተኛ መሆኑንና መናዘዙን፤ ቁ.8-9

4. ሁሉን ነገር ትቶ ጌታ ኢየሱስን መከተሉን፤ ቁ.10-11

ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስን ከፊቱ እንዲሄድ በጠየቀው ጊዜ ስሕተተኛ ነበር፤ ነገር ግን ኃጢአተኛ መሆኑን መናዘዙ ትክክለኛ ነበር። ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ክብር አየ፤ ከአፉ መልካም የማይወጣው ኃጢአተኛ መሆኑን ንስሐ ገባ። እግዚአብሔር ንጹሕ አደረገው፤ ለእግዚአብሔርም ሥራ ተላከ፤ ኢሳ.6:1-10።

ጌታ ለምፃሙን አነፃ 5:12-16

ሌሎች ጸሐፊዎችም ስለዚሁ ለምፃም ሰው ይነግሩናል፤ ማቴ.8:1-4፤ ማር.1:40-45፤ ነገር ግን ሐኪሙ ሉቃስ ሰውየው በለምፅ የተወረሰ እንደነበር ያነግረናል። ይህ ሰው የጌታ ኢየሱስን ኃይል ያውቅ ነበር፤ ነገር ግን ይረዳው እንደሆነ

እርግጠኛ አልነበረም፤ 5:12። ጌታ ኢየሱስ ይህንን ለማድረግ አልተጠራጠረም፤ «ፈቃደኛ ነኝ» አለ፤ ሰውየውንም አነፃው። ከዚያም በላይ ሰውየውን ዳሰሰው። ለምፃሙ በከተማው ውስጥ ሊኖር አልቻለም። ንጹሕ ስላልሆነ እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ቤተ መቅደስ አይገባም ነበር። ማንኛውም ሰው ንጹሕ ያልሆነውን ከነካ እርሱም ንጹሕ አይሆንም፤ ዘሌ. 13:45-46፤ ዘኍ. 19:22 አንብብ። ጌታ ኢየሱስ ሰውየውን ስለነካ አልረከሰም፤ ነገር ግን ለምፃሙን አነፃው። ለምፃሙንም ራሱን ለቄስ እንዲያሳይና መስዋዕት እንዲያቀርብ ነገረው፤ ዘሌዋ. 14:1-20። ሰውየው እውነት ነጽቶ ከሆነ ቄሱ ያውቃል፤ ሰዎችም ቄሱ የተናገረውን ያምናሉ። ጌታ ኢየሱስ ይህንን ሰው ከለምፁ መዳኑን ለሁሉም እንዳይናገር አዘዘው። ነገር ግን ሰውየው ለብዙ ሰዎች መዳኑን ተናገረ፤ ማር. 1:44-45። ብዙ ሕዝብም ተሰበሰቡ፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ለትንሽ ጊዜ ብቻውን ለመሆን ትቶአቸው ሄደ። ምንም ነገሩ ባይገባንም እንኳ ጌታ ኢየሱስን መታዘዝ እንዳለብን ተመልክተናል። ዛሬ ይህንን መልካም ዜና ለሁሉም ሰዎች እንድንናገር ያሳስበናል፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ከመታዘዝ ችላ ብለናል።

በእነዚህ ሁለት ታሪኮች የእግዚአብሔርን ልጅ ኃይል ተመልክተናል፤ 5:1-16። በባሕር ዳር ላይ ኃይል ነበረው፤ በለምፃሙም ሰውነት ላይ ኃይል ነበረው። ለመራመድ የማይችለውን ሰው ለማዳንም ኃይል ነበረው፤ ቁ. 17-26። በሌላው የዚህ ምዕራፍ ክፍል ውስጥ ፈሪሳውያን ጌታ ኢየሱስን እንዳልተቀበሉት ማየት እንጀምራለን።

መራመድ የማይችለው ሰው 5:17-26

ፈሪሳውያን እነማን ነበሩ? ፈሪሳውያን የአይሁዳውያን መሪዎች ነበሩ። በብሉይ ኪዳን ያምኑ ነበር፤ ነገር ግን ሌላ ብዙ ትምህርት ጨምረውበታል። የሰዎችን ትምህርት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በእኩል ደረጃ ይመለከቱት ነበር። ፈሪሳውያን ከሌሎች ይልቅ ስለ ብሉይ ኪዳን እናውቃለን ብለው ያስባሉ፤ ዮሐ. 7:47-49።

ፈሪሳውያን አጥግቁው ዮሐንስን ግን እንደሆነ እንዲጠይቀው ሰው ላኩ፤ ዮሐ. 1:24-25። ብዙ ፈሪሳውያንና አስተማሪዎች ከሀገሪቱ በሙሉ በአንድ ላይ ተሰብስበው መምጣታቸውን እንመለከታለን፤ 5:17። እነርሱም ሊፈወሱ ይችሉ ነበር፤ ነገር ግን በጌታ ኢየሱስ አላመኑም። መሪዎቹ ጌታ ኢየሱስን ተቀብለው ቢሆን ኖሮ ሕዝቡም እነርሱን ይከተሉ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ግን ከሁሉም በላይ ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማስደሰት ፈለገ። ፈሪሳውያንን አሳምኖ ወደ እርሱ ወገን ለማድረግ ሲል ትምህርቱን አልቀየረም።

ኦራት ሰዎች ጓደኛቸውን ወደ ክርስቶስ ማምጣት በሚሞክሩበት ጊዜ ፈሪሳውያን ከጌታ ኢየሱስ ጋራ በቤት ውስጥ ነበሩ፤ 5:18፤ ማር. 2:3። እነዚህ ሰዎች በእውነት ጌታ ኢየሱስ ጓደኛቸውን እንደሚፈውስ አምነው ነበር፤ ነገር ግን ወደ ጌታ ኢየሱስ ሊጠጉ አልቻሉም፤ ምክንያቱም በዙሪያው ብዙ ሰዎች ስለነበሩ ነው። ስለዚህ በጣራው ቀዳዳ አበጁ። ጓደኛቸውንም ጌታ ኢየሱስ ባለበት በኩል ቁልቁል ሰደዱት። ሽባውም እምነት ነበረው። ጌታ ኢየሱስም ኃጢአቱ ይቅርታ ተደርጕለታል አለ።

ሰውነታችንን ከሚፈውሰን ይልቅ ለኃጢአታችን ይቅርታ መስጠት በእግዚአብሔር በኩል የበለጠ አስፈላጊ ነው፣ ምሕረት አገኘን፣ ከዚያም ተፈወስን፤ መዝ.103:3። በእግዚአብሔር ሰላም ያለው የታመመ ሰው ቶሎ ለመዳን የበለጠ ዕድል አለው። የሆነ ሆኖ በኃጢአት ከመኖር አምኖ መሞት ይመረጣል። ፈሪሳዊያን ጌታ ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር ለማለት እንደሚችል አላመኑም ነበር። ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ ማንም ኃጢአትን ይቅር ለማለት እንደማይችል አወቁ።

ዛሬ ብዙ ሰዎች ኃጢአትን ይቅር ለማለት ከእግዚአብሔር ሥልጣን አለን ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ሥልጣን አይሰጣቸውም። ሰው እንደገና ኃጢአት እንዳይሠራ ለማድረግ በእርግጥ ምንም ኃይል የላቸውም። ኃጢአትን ይቅር ሊል የሚችለውና ከኃጢአትም የሚጠብቅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፤ ይሁዳ 24-25። አመንዝራይቱን ሴት ይቅር አላት፥ ዳግመኛም ኃጢአት እንዳትሠራ ነገራት፤ ዮሐ.8:11። ይህን አዳኝ ነው እኛ የምንፈልገው። ጌታ ኢየሱስ ለፈሪሳውያን የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አልነገራቸውም፤ ነገር ግን ይህንን ሰው /ሽባውን/ በማጠንከር ተነሥቶ እንዲመላለስ በማድረግ የእግዚአብሔር ልጅነቱን አረጋገጠ። ጌታ ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ማንኛው ይቀላል፡- የሰውየውን ኃጢአት ይቅር ማለት ወይስ እንዲራመድ ኃይል መስጠት፤ 5:23። እግዚአብሔር እነዚህን ሁለት ነገሮች ማድረግ ይችላል። ይህ ሰው በፊት ሽባ ነበር፤ አሁን ግን እግዚአብሔርን እያመሰገነ አልጋውን ተሸክሞ ወደ ቤቱ ሄደ። በመጀመሪያ የሰውየው ጓደኞች ሽባውን ወደ ጌታ ለማምጣት ከሕዝቡ መብዛት የተነሣ አልቻሉም ነበር። አሁን ግን በመፈወሱ እጅግ ተደነቁ፤ ቁ.26። ሰዎችን ወደ ጌታ እንዳይመጡ መከልከል ለክርስቲያኖች ስሕተት ነው። አንዳንድ አማኞች በኃጢአት ይኖራሉ፤ አንዳንዶችም ለሰዎች መልካምን አያደርጉም። ወደ ጌታ ለመምጣት የሚፈልጉትን ሰዎች እንዳይመጡ ይህ ድርጊታቸው ሊያግዳቸው ይችላል። በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች ወደ አዳኛችን ለመምጣት ፍላጐት እንዲያድርባቸው የእግዚአብሔርን ፍቅር ማሳየት አለብን፤ ንጹሕ ኑሮም መኖር አለብን።

ጌታ ኢየሱስ ሌዊን ጠራ 5:27-32

አገርን ለማስተዳደር ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ማንኛውም ማሰብ የሚችል ሰው ሁሉ ያውቃል፤ ክርስቲያኖችም የሚደርስባቸውን ቀረጥ ለመንግሥት መክፍለ አለባቸው፤ ሮሜ 13:6-7። በጌታ ኢየሱስ ዘመን ብዙ ቀራጮች ከሚያስፈልገው በላይ ሰዎችን እያስገደዱ የሚያስከፍሉ ደካማ ሰዎች ነበሩ። ቀራጮችም ልዩነቱን ለራሳቸው ያስቀሩ ነበር። ከዚህም በላይ ቀረጡን የሚከፍለው ሰውም መንግሥት በሮም ነበር። የእስራኤል ሕዝቦች ቀራጮችን እንደሚጠሉ አያጠያይቅም።

ሌዊ ወይም ማቴዎስ ቀራጭ ነበር፤ ማቴ.9:9-13። ታማኝ ይሁን አይሁን አናውቅም፤ ነገር ግን እንደ ጴጥሮስ ኃጢአተኛ መሆኑን አወቀ፤ 5:8። በሉቃስ ወንጌል እንደምንመለከተው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን፥ ቀራጮችንና አመንዝራ ሴቶችን ለማዳን ይችላል፤ 7:37፤ 15:1፤ 19:2። ሌዊ ከዚህ በፊት ክርስቶስን

አውቆት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እዚህ ላይ እንዲከተለው ጠራው። ማቴዎስም /ሌዊ/ በአንድ ጊዜ ሥራውን ትቶ ተከተለው። ማቴዎስም ራሱ በወንጌሉ ሁሉንም መተውን ወይም ለጌታ ግብዣ ማድረጉን አይገልጽልንም፤ ማቴ.9:9-10። እነዚህን ነገሮች ከሉቃስ እንማራለን፤ ሉቃ.5:28-29። አሁን የጌታ ኢየሱስ ተከታይ መሆኑን ጓደኞቹ ሁሉ እንዲያውቁለት ማቴዎስ ፈለገ። ፈሪሳዊያን ስለ ጌታ ፀጋ አላወቁም፤ ከኃጢአተኞችና ከቀራጮች ጋራ መብላትና መጠጣቱ ለጌታ ኢየሱስ ስሕተት ነው ብለው አሰቡ። ስለ ጌታ ኢየሱስም ለደቀመዛሙርቱ ነገሯቸው። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ራሱ መለሰላቸው፤ ቁ.31-32። አንድ ሰው በሽተኛ መሆኑን ካላወቀ ወደ ሐኪም አይሄድም። ሁሉም ሰዎች ኃጢአተኞች ናቸው፤ ነገር ግን ብዙዎቹ ይህንን አያምኑም። ጌታ ኢየሱስ እነዚህን መዳን እንደሚያስፈልጋቸው የሚሰማቸውን ለመጥራት መጥቷል። ኃጢአተኞቹ ወደ አዳኙ መጡ፤ ፈሪሳዊያን ግን እምቢ አሉት። አንድን ሰው ወደ ጌታ ለማምጣት በምትሞክርበት ጊዜ በመጀመሪያ ኃጢአተኛ መሆኑን መረዳቱ አስፈላጊ ነው። ይህም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፤ ዮሐ.16:8። አንድ ሰው ኃጢአተኛ መሆኑ ከገባው በጌታ በኢየሱስ እንዴት ማመን እንደሚችል ልታሳየው ትችላለህ። ነገር ግን ሌሎችን ለመርዳት ከፈለግን ማቴዎስ እንዳደረገው ሁሉንም ትተን ክርስቶስን መከተል አስፈላጊ ነው፤ ሉቃ.14:33።

ፈሪሳዊያን ሌላ ደስ ያላላቸው ነገር ነበር። በብሉይ ኪዳን በኃጢአታቸው እንዳዘኑ ለግሳየት የእግዚአብሔር ሰዎች ይጾሙ ነበር። የዮሐንስና የፈሪሳዊያን ተከታዮች ይጾሙ ነበር። ነገር ግን የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ምግባቸውን እንደተለመደው ይበላሉ፤ 5:33። ጌታ ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ሌላ ጥያቄ በመጠየቅ መለሰላቸው። ወደ ሠርግ እራት የተጋበዙ ሰዎች ከሙሽራው ጋር ለመሆን ደስ ይላቸዋል፤ ቁ.34። ጌታ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ሙሽራው እንድትሆን ያዘጋጃታል። እርሱ በተለያቸው ጊዜ ተከታዮቹ መጾም ያስፈልጋቸው ይሆናል። ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ ጋራ አብሮ እያለ መጾም አያስፈልጋቸውም፤ ቁ.35። አሁን ጌታ ኢየሱስ በሰማይ ነው፤ በእርግጥ ግን አጠገባችን አለ፤ ከእኛ ጋርና በእኛ ውስጥ አለ። በአዲስ ኪዳን እንድንጾም አልተነገረንም። ሰውነታችንን በመንከባከብና ኃይላችንን በመጠበቅ ጌታ ኢየሱስን የበለጠ ልናገለግለው እንችላለን።

ጌታ ኢየሱስ ትንሽ ምሳሌ ነገራቸው፤ 5:36-38። የጌታ ኢየሱስ ትምህርት ከብሉይ ኪዳን ሕጎች ጋር ልዩ ነው። በቁጥር 36 እንደሚለው አዲሱንና አሮጌውን ማደባለቅ አይቻልም።

በዚያን ወቅት ወይን የተለመደ መጠጥ ነበር፤ በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ የደስታ ምልክት ነው። ለምሳሌ:- መሳ.9:13። የጌታ ኢየሱስ ትምህርት እንደገና ለተወለዱት ትልቅ ደስታ ይሰጣቸዋል፤ ዮሐ.15:11። እንደገና ያልተወለዱ ሰዎች እንደ አሮጌው የወይን አቁማዳ ናቸው፤ የክርስቶስን ደስታ በውስጣቸው ለማየት አይቻልም፤ 5:37-38። በሌላ በኩል ደግሞ በራሳቸው የሚደሰቱ አሮጌው ነገር በጣም ጥሩ ነው ብለው ያስባሉ። እነዚህ ሰዎች የክርስቶስን አዲስ ደስታ አይፈልጉም፤ ቁ.39። በዚህ

ምክንያት እነርሱም ጌታን ለማወቅ ፍላጐት እንዲኖርባቸው የክርስቶስን ፍቅር ልናሳያቸው ይገባናል።

በሉቃስ 5 አንዳንድ ሰዎች ጌታ ኢየሱስን እንደሚወዱ አሳዩ፤ ሌሎችም የእርሱ ጠላቶች እንደነበሩ አሳዩ። ጌታ ኢየሱስ በሙሉ ኃይል የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አሳዩ።

ወዳጆቹ	ጠላቶቹ	ሥልጣኑ
ጴጥሮስ ለቃሉ ታዘዘ ቁጥር 5	በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ይናገራል አሉ፤ ቁጥር 21	በባሕር ዓሦች ላይ ቁጥር 6
ጴጥሮስ ያዕቆብና ዮሐንስ ስለ እርሱ ሁሉን ነገር ተዉ፤ ቁ.11	ከኃጢአተኞች ጋር ይበላል አሉ፤ ቁጥር 30	ለምፃሙን ለመፈወስ ቁጥር 13
ሌዊ ሁሉን ትቶ ተከተለው፤ ቁጥር 28	ደቀ መዛሙርቱ አይጾሙም አሉ፤ ቁጥር 33	ኃጢአትን ይቅር ለማለት ቁጥር 20 ሽባን ለመፈወስ፤ ቁጥር 25።

ሁለት የሰንበት ቀኖች 6፡1-11

ፈሪሳዊያን በጌታ ኢየሱስ ትምህርት እንዳልተስማሙ ተመልክተናል፤ 5፡21፤ 30፤ 33። በሁለቱም ሰንበት ቀኖች የሆነውን ሉቃስ ይነግረናል፤ ምዕ.6። በመጀመሪያው ሰንበት የጌታ ደቀ መዛሙርት በእርሻ ውስጥ እየሄዱ እሸት ቆርጠው ይበሉ ነበር። እሸት ቆርጦ መብላት ስሕተት አይደለም፤ ዘዳ.23፡25። ፈሪሳዊያን ግን ደቀ መዛሙርቱ የሰንበትን ሕግ ተላልፈዋል ብለው አሰቡ፤ ዘፀ.20፡8-11። ጌታም ስለ ዳዊት አንብበው እንደሆነ በጥያቄ መለሰላቸው፤ 1ሳሙ.21፡2-6። እግዚአብሔር ዳዊትን የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን መረጠው፤ ነገር ግን ከመንገሡ በፊት ከንጉሥ ሳኦል መሸሽ ነበረበት። ዳዊት በራበው ጊዜ ቁሶች የመባ እንጀራ አንሥተው ሰጡት። ይህም እንጀራ ለቁሶች ነበር፤ ዘሌ.24፡5-9። ነገር ግን ቁሶቹ ከዳዊት ጋራ ከእግዚአብሔር ምርጥ ንጉሥና ከሰዎችም ጋራ በተራቡ ጊዜ አብረው ለመከፈል ፈቃደኞች ነበሩ። ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ራሱ የሰንበት ጌታ ነው አላቸው። ከዳዊትም ይበልጥ ነበር፤ ሉቃ.20፡44።

ሰባተኛ ቀን እንደተለየ ቀን አድርገን እንድናከብረው እኛን ክርስቲያናችን አልነገረንም። ጌታ ኢየሱስ በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ከሞት ተነሣ፤ እኛም የምናስታውሰው በዚያ ቀን ነው። የሳምንቱን መጀመሪያ ቀን እግዚአብሔርን ማምለኪያና ቃሉን መስሚያ ለማድረግ መሞከር አለብን። እንደማንኛውም ቀን ለሥራና ለጨዋታ እናውለውም። ይህ ሕግ አይደለም፤ እኛ ከፀጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደለንምና፤ ሮሚ 6:14። የዳንን የመጀመሪያውን ወይም ሰባተኛውን ቀን በመጠበቅ አይደለም። ለመዳን እንዲረዳቸው የተለየ ቀናችን ይጠብቁ ስለነበር ጳውሎስ ለገላቲያ ሰዎች ያስብ ነበር፤ ገላ.4:10-11። በሥራ ሳይሆን በፀጋ ድነናል፤ ቲቶ 3:5፤7 ኤፌ.2:8-9።

በሌላው ሰንበት ጌታ ኢየሱስ በምኩራብ ያስተምር ነበር፤ 6:6-11። ቀኝ እጁ ሽባ የሆነ አንድ ሰው በዚያ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ፈሪሳውያን እንደሚከታተሉት ያውቅ ነበር። በሰንበት ቀን ሰውየውን ቢፈውሰው በሰዎች ፊት ሊወነጅሉት ይችላሉ። በሰንበት መልካምን ማድረግ በሕግ የተደገፈ ነው ወይ ብሎ ጠየቃቸው። የሰውን ሕይወት ማዳንና በሰንበትም መልካምን ማድረግ ከሕግ ውጭ ነው ለማለት አልፈለጉም። ሰውየውን እጁን አያንቀሳቅስም ነበር፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ እንዲዘረጋው ነገረው። እጁም ዳነለት። ይህም ፈሪሳዊያንን ከመቸውም የበለጠ አናደዳቸው። በጌታ ላይ ምን እንደሚያደርጉ እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ።

ፈሪሳዊያን ጌታ ኢየሱስን አይወዱትም ነበር። ኃጢአትን ይቅር ለማለት እንደሚችል መናገር የለበትም ብለው አሰቡ፤ 5:21። ከኃጢአተኞችም ጋር መብላት የለበትም፤ 5:30። ደቀ መዛሙርቱን መጾም እንዲያስተምራቸውና ሰንበትን እንዲያከብሩ ይንገራቸው፤ 5:33፤ 6:2። በሰንበት ቀን ሰዎችን መፈወስ የለበትም፤ 6:7። በእነዚህ አምስት ታሪኮች እንደምንመለከተው ጌታ ኢየሱስ የሰዎችን ሀሳብ እንዲሁም በሽተኞችን መፈወስ ይችል ነበር። ፈሪሳዊያን ሊያታልሉት በሚምክሩበት ጊዜ በጥበብ አሚመልሰላቸውንም ተመልክተናል። ሰይጣንም ሆነ ሰዎችም ሆኑ ጌታ ኢየሱስን ምንም ሊያሳስቱት አልቻሉም።

ጌታ አሥራ ሁለት ሐዋሪያቱን መረጠ 6:12-16

ሉቃስ ጌታ ኢየሱስን ፍጹም ሰው እንደሆነ ያሳየናል። ሰው ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አለበት። ጌታ ኢየሱስ ከተከታዮቹ ውስጥ ጥቂቶቹን ለልዩ አገልግሎት ለመጥራት ፈለገ። በመጀመሪያ ሌሊቱን በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ብቻውን ሲጸልይ አደረ። በሚቀጥለው ቀን ከተከታዮቹ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያቱ እንዲሆኑ ጠራ። በምዕራፍ 5 ስለ ጴጥሮስ ያዕቆብና ዮሐንስ አንብበናል፤ እንዲሪያስም አብሮአቸው እንደነበር በማቴዎስ ወንጌል አንብበናል። ስለ ፊልጶስ የበለጠ በዮሐንስ እንረዳለን፤ ዮሐ.1:43። ባርተሎሜውስ በዮሐንስ ውስጥ ናትናኤል የሚባለው ሰው ሳይሆን አይቀርም፤ 1:45-51። ስለ ቶማስ በዮሐንስ ውስጥ በመጠኑ አውቀናል፤ ዮሐ.11:16፤ 14:5፤ 20:24-28። ስለ ማቴዎስ መጠራት በሉቃስ 5 ውስጥ አንብበናል፤ ነገር ግን ስለ ቀሩት ሰዎች ማለት ስለ አልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፥ ስለ ቀናናዊ

ስምዖንና የያዕቆብ ልጅ ስለሆነ ስለ ይሁዳ የተነገረው በመጠኑ ነው። የአስቆሮቱ ይሁዳ ጌታ ኢየሱስን ለጠላቶቹ አሳልፎ ሰጠው፤ ሉቃ.22:3-6፤ 47-48።

ጌታ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ እነዚህን ሰዎች ጠራ፤ ሌሎች ሊገባቸው የማይችለውን ብዙ ነገርም አስተማራቸው። እርሱም አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ ላካቸው፤ ማቴ.10:5-7። ይህ የእግዚአብሔር መንገድ ነው። ከሁሉም በፊት ስለ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ቃል መማር አለብን፤ ከዚያም ስለ እርሱ ለሌሎች መመስከር እንችላለን።

ጌታ ኢየሱስ አሥራ ሁሉትን ሐዋርያት በመረጠ ጊዜ እንዲያገለግሉት ኃይል ሰጣቸው፤ ማቴ.10:1። በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ሌሎችን ማገልገል እንዳለባቸው በራሱ ምሳሌ አሳያቸው፤ 6:17-19። ሰዎች ከየአቅጣጫው የጌታን ቃል ለመስማትና ለመፈወስ መጡ። አንዳንዶቹ ከሀገሪቱ በስተሰሜን ካሉት ሩቅ ከተሞች ከጢሮስና ሲዶና መጡ። ጌታ ኢየሱስ ራሱ ይህንን ቦታ ቆይቶ ጐበኘው፤ ማቴ.15:21።

ጌታ ኢየሱስ ሰዎችን የእግዚአብሔርን ቃል ሊያስተምራቸው ፈለገ። የቀረው የምዕራፍ 6 ክፍል ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን አስፍሯል። በሌላ ቀን ጌታ ኢየሱስ በተራራ ላይ ነበር ከእነዚህም ብዙ ነገሮችን አስተማረ፤ ማቴ.5-7። በረከትን የሚያገኙ አራት የሕዝቦችን ዓይነት ጌታ ኢየሱስ መዘርዘር ጀመረ፤ 6:20-23። አራት ሌሎች የሚያዝኑትንም ጠቀሰ፤ ቁ.24-26። ዘጠኝ በረከቶች አሉ፤ ማቴ.5:3-12። ለፈሪሳዊያን ወደፊት የሚደርስባቸውን ኃዘን ይነግራቸዋል፤ ማቴ.23፤ ሉቃ.11:38-52።

አራቱ በረከቶች አሁን በኃዘን ላይ ያሉ በኋላ ደስታ የሚኖራቸው ናቸው። ድኃና ረሃብተኛ አማኝ ካላመነ ሀብታም ይሻላል። ጴጥሮስ፥ ያዕቆብ፥ ዮሐንስና ማቴዎስ ሁሉን ትተው ጌታ ኢየሱስን እንደተከተሉ አይተናል። በማቴዎስ ያለው በረከት በመንፈስ ድሆች ለሆኑና ጽድቅን ለተራቡ ነው፤ 5:3 እና 6። ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንደ እርሱ እንዲሆኑ ይፈልጋል። ድኃና ረሃብተኛ መሆን ማለትን በልምድ ያውቃል። ሀብታም ነበረ፥ ነገር ግን ድኃ ሆነ፤ 2ቆሮ.8:9። መዶም ምን እንደሆነ ያውቃል፤ ሉቃ.4:2። የሕመም ሰው ተባለ፤ ኢሳ.53:3። የሰዎችን ክሕደት ምን እንደሆነ በእርግጥ ያውቃል፤ ሉቃ.9:22።

ሰዎች ስለ ክርስቶስ ሲጠሉን ደስ ሊለን ይገባል። ከዚያ በፊት ነቢያትን፥ ሐዋርያትንና ራሱን ጌታ ኢየሱስን ጠልተዋል። ነገር ግን ክፉ ሠርተን ብንሠቃይ በሰማይም ሆነ በምድር ሽልማት አናገኝም፤ 1ጴጥ.2:20።

ወደፊት ሐዘን ስለሚገጥማቸው አራት ዓይነት ሰዎች አራት ማስጠንቀቂያዎች አሉ፤ 6:24-26። ሀብታሞች የሆኑ በሕይወታቸው ይደሰታሉ። አንዳንድ ሀብታሞች በሚቀጥለው ዓለም ኃዘን ያጋጥማቸዋል፤ 16:25። አንዳንድ ሰዎች ተገቢ ደሞዝ ስለማይከፍሉ ሀብታሞች ይሆናሉ፤ ያዕ.5:1-6። ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም ሀብታሞች ለመሆን መሞከር የለብንም፤ በሰማይ ግን ሀብታሞች ልንሆን እንችላለን፤

1ጢሞ.6:7-10፤ ማቴ.6:19-21። በእሱኑ ጊዜ ሀብታሞች የሆኑ ገንዘባቸውን ለጌታ ክብር ማዋል አለባቸው፤ 1ጢሞ.6:17-19።

ጌታ ኢየሱስ ለድሆችና ለሃብታሞች ይናገራል፤ 6:20፤ 24። ለተራቡና ለሚያለቅሱ እንዲሁም ለሞኞች ይናገራል፤ ቁ.21፤ ቁ.25። ማንኛውም ነገር በምትመጣው ዓለም ልዩ ይሆናል። ጌታ ኢየሱስም ሰዎች ስለ እርሱ ሲጠሉን መደሰት እንዳለብን ያስተምረናል፤ ቁ.22-23። ሰዎች ስለ እኛ መልካም ሲናገሩም አደገኛ መሆኑን አስተምሯል፤ ቁ.26።

በሚቀጥለው የምዕራፉ ክፍል ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ስለ ፍቅር ያስተምረናል፤ 6:27-36። በመጀመሪያ ስለ ፍቅር ትዕዛዛት አሉን፤ ቁ.27-31። ከዚያም የፍቅር ምሳሌዎች፤ ቁ.32-36። ወርቃማው ትዕዛዝ ጠላቶቻችንን እንድንወድ ይነግረናል፤ ሌሎች ለእኛ እንዲያደርጉልን የምንፈልገውን ነገር ለእነርሱም ማድረግ አለብን፤ ቁ.27 እና 31። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎቹን የብሉይ ኪዳንን ትዕዛዝ እንዲቀበሉ ነገራቸው፤ ጮሬቤታችሁን እንደራሳችሁ ውደዱ፤ ዘሌ.19:18፤ ሉቃ.10:27። ጠላቶቻችንን እንድንወድ ያስተምረናል፤ ማቴ.5:43-48። ሥጋዊ ሰው መንፈስ ቅዱስ የለውም፤ የእግዚአብሔርን ሕግ ሊጠብቅ አይችልም፤ ሮሜ 8:7። ጠላቶቹንም ሊወድ ፈጽሞ አይችልም።

በክርስቶስ ውስጥ ለሆንን በእኛ ግን ሁኔታው ልዩ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሕጉን ልንጠብቅ እንችላለን፤ ሮሜ 8:3-4። ጌታ ኢየሱስ ጠላቶቹን ወደደ፤ ጸለየላቸውም፤ ሉቃ.23:34። ከሌሎቹ አንዱ በጥፊ አለው፤ ነገር ግን ጌታ በጽሞና መለሰለት፤ ዮሐ.18:22-23። ከእነዚህና ከሌሎችም ብዙ ጥቅሶች እንደምንመለከተው ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስላስተማረው መልካም ምሳሌ አሳያቸው። እኛ እንዲሁ ማድረግ አለብን።

ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ለሌሎች መመስከር እንችላለን፤ ነገር ግን በምናደርገው ደግሞ ለእነርሱ ማሳየት አለብን። አንዳንድ ሰዎችን መውደድ በተለይ ደግሞ ጠላቶችህን ከባድ ነው ትላለህ? እግዚአብሔር ሰዎችን በመልካም እንደሚመለከታቸው ሁሉ እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን። እግዚአብሔር ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን ወደደ። እግዚአብሔር ጠላቶችህን ይወዳል፥ እንድትወደው ይረዳሃል። ጠላትህ ክርስቲያን ቢሆን የአንተ የቅርብ ጓደኛ ይሆናል። ሌላም አለ፡- ጓደኛዬን ብቻ የምወድ ከሆነ ከኃጢአተኞች ጋር ልዩነት የለኝም፤ ምክንያቱም እነርሱም እንዲህ ያደርጋሉና፤ 6:32-34። የአባቴን የእግዚአብሔርን ምሳሌ መከተልና እርሱ እንዳደረገው ማድረግ አለብኝ፤ ቁ.35-36። ኃጢአተኞች በነበርንበት ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ ልጁን በመስጠት ፍቅሩን አሳየን፤ ሮሜ 5:8።

መፍረድ 6:37-45

ለእኛ እንዲያደርጉልን የምንፈልገውን እኛም ለሌሎች ማድረግ አለብን፤ 6:31። እኔ ሌሎችን ሰዎች ይቅር የምል ከሆነ እነርሱም ይቅር ይሉኛል፤ ቁ.37። ለሌሎች

ብሰጥ ለእኔ ደግ ይሆናሉ፤ ቁ.38። እነዚህም ጥቅሶች ለሌሎች ደግ ከሆንኩ እግዚአብሔር ሽልማት ይሰጠኛል፥ ሌሎችን ይቅር ካልኩ እግዚአብሔር እኔን ይቅር ይለኛል ማለታቸው ነው።

ሦስት ዓይነት ኃጢአተኞችና ሦስት ዓይነት ይቅርታዎች አሉ።

1. በሰማይና በምድር ንጉሥ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራት፤ እግዚአብሔር በጌታ ኢየሱስ ለሚያምኑ ኃጢአተኞች ይቅር ይላል። እንደገና ስለተወለዱ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ይገባሉ።

2. በአባታችን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራት፤ ኃጢአታቸውን ለእርሱ ከተናዘዙ አባት ለልጆቹ ይቅርታ ያደርጋል፤ 1ዮሐ1:9። በእነርሱ ላይ ክፉ ያደረጉትን ይቅር ካላሉ እግዚአብሔር ይቅር አይልም፤ ማቴ.6:14-15።

3. በሌላ ሰው ላይ ክፉ ማድረግ፤ አንድ ሰው በእኔ ላይ ክፉ ቢያደርግ እግዚአብሔር እኔን ይቅር እንዳለኝ ማስታወስና በእኔ ላይ ክፉ ያደረገውን ወንድሜን ይቅር ለማለት መዘጋጀት አለብኝ። በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት የሚያደርግ ኃጢአቱ እንዳይገለጥ መደበቅ አለብኝ ማለት አይደለም። ክርስቲያን በኃጢአት ቢወድቅ እርሱን መቅጣት የቤተ ክርስቲያኒቱ ተግባር ነው፤ 1ቆሮ.5:3-5።

በሌላ የሚታየውን ኃጢአት ከመፍረዴ በፊት በእኔ ላይ ያለውን መፍረድ አለብኝ። ሌላው ክርስቲያን ትክክለኛውን መንገድ እንዳላየው ያስፈልጋል ብዬ እገምት ይሆናል። ነገር ግን ዓይነ ስውር ሌላውን ዓይነ ስውር ሊመራው አይችልም፤ 6:39። እኔ ሌላውን የማውቀውን ብቻ ላስተምረው እችላለሁ። ካስተማሪው የሚበልጥ ተማሪ የለም፤ 6:40። ሌላውን ከእኔ የበለጠ ለማድረግ አልችልም። ስለዚህ በመጀመሪያ በራሴ ላይ መፍረድ አለብኝ። ከዚያም ኃጢአታችንን ካስወገድን በኋላ በሌሎች ላይ መፍረድ እንችላለን። በዓይኔ ውስት አንድ ትልቅ ጉድፍ ካለብኝ በወንድሜ ዓይን ውስጥ ያለውን ትንሽ ጉድፍ ለማውጣት ለማየት አልችልም፤ ቁ.41-42። በሌላው ያለውን ኃጢአት ከመፍረዴ በፊት በእኔ ያለውን ኃጢአት ማስወገድ አለብኝ ማለት ነው። በኃጢአት የወደቀውን ወንድም ሊረዱት የሚችሉ መንፈሳዊያን ሰዎች ብቻ ናቸው፤ ገላ.6:1።

ሰው እንደ ዛፍ ነው አለ ጌታ፤ 6:43-45። ዛፍ ሊያፈራ የሚችለው የራሱን ዓይነት ፍሬ ነው። እኔ በውጭ የማደርገው የውስጡን አስተሳሰቤን ይገልፃል፤ እውነተኛ ሁኔታን ያሳያል። ሁሉም ሰዎች ይመሳሰላሉ። ሰው ምን እንደሚያስብ እንዴት እናውቃለን? በመጥፎ ወይም በጥሩ ንግግሩ ወይም ተግባሩ ልናውቅ እንችላለን። ስለ ራስህ ልብ እርግጠኛ ካይደለህ ከእግዚአብሔር አዲስ ግግኘት ትችላለህ፤ ሕዝ.36:26። ጌታ ኢየሱስ እንደገና መወለድ እንደሚኖርብን አስተማረ፤ ዮሐ.3:7።

ብዙ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ሲናገሩ «ጌታ» የሚለውን ቃል ይጠቀሙበታል። ነገር ግን እውነተኛ ጌታችን ከሆነ የሚለንን ማድረግ አለብን። እነዚህ ቃሉን የሚቀበሉ ሰዎች ቤቱን በአለት ላይ እንደሠራ ሰው ናቸው። እነዚህ ቃሉን የሚቀበሉ ፈተና በመጣባቸው ጊዜ አይወድቁም። እነዚህ ቃሉን የማይቀበሉ መሠረት በሌለው መሬት ላይ ቤቱን እንደሠራ ሰው ናቸው። በመከራ ጊዜ ይወድቃሉ።

ሕይወትህን በክርስቶስ በአለቱ ላይ መመሥረትህን እርግጠኛ ነህ? በዚህ ምዕራፍ የሚገኘውን የጌታን ትምህርት ለመቀበል ፈቃደኛ ነህ? በሁሉም መንገሎች ውስጥ ያለውንስ? በመላ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔርን ቃል ትቀበላለህ? ከተቀበልከው እርሱ እውነተኛ ጌታ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝ ተቀብሎ እንደ ጌታ ላለመቀበል ጨርሶ አይቻልም። እግዚአብሔር ሁለቱንም ማለትም ጌታም ክርስቶስም /አዳኝም/ አድርጐታልና፡ የሐዋ/ሥራ 2:36። አዳኝህ ከሆነ ጌታህም ነው፡ ልትታዘዘው ይገባሃል።

ሁለተኛ ጉዞ 7:1-8:56

ጌታ ከናዝሬት ወደ ቅፍርናሆም መሄዱን ተምረናል፡ 4:31። በገሊላ በብዙ ቦታዎች ሰብኮ ወደ ቅፍርናሆም ተመለሰ፡ 7:1። ከዚያ ተነሥቶ ወደ ናይን ሄደ፡ 7:11። ከዚያም ወደ ብዙ ከተሞች፡ 8:1። በኋላም ወደ ጌራሰኖን ሄደ፡ 8:26። ከዚያ በኋላ እንደገና ወደ ቅፍርናሆም ተመለሰ፡ 8:40፡ ማቴ.9:1። በእነዚህ በተለያዩ ቦታዎች ጌታ ያደረገውንና የተናገረውን እናጥና።

የመቶ አለቃው አገልጋይ 7:1-10

በቅፍርናሆም በሮማዊያን ጦር ሠራዊት ውስጥ አንድ መቶ አለቃ ነበር። ከእነዚህ አንዳንድ የሮማዊያን ወታደሮች ውስጥ ለሕዝቡ ታማኞችና ደጐች አልነበሩም፡ 3:14። ይህ የመቶ አለቃ ግን ልዩ ነበር። ለእስራኤል ሕዝቦች ደግ ነበር። በውስጡም እግዚአብሔርን እንዲያመልኩበት ምኩራብ እንኳ ሠርቶላቸዋል። በአራቱ ወንጌሎች ስለ አንድ ሌላ የመቶ አለቃ እናነባለን። ይህ ሰው ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት አይቶታል። እርሱም መልካም ሰው እንደነበረ አወቀ፡ 23:47። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሉቃስ ስለ ሌላ የመቶ አለቃ ይነግረናል።

ጌታ ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም በተመለሰ ጊዜ ይህ የመቶ አለቃ የታመመ አገልጋይ እንዳለው ሰማ። ይህ ሰው አገልጋዩን ይወደው ነበር። ጌታ ኢየሱስ መጥቶ አገልጋዩን ይፈውሰው ዘንድ እንዲጠይቁት የይሁዳ ሽማግሌዎችን ላከበት። እነዚህ ሰዎች ይህ የመቶ አለቃ የጌታን ዕርዳታ አገኘ አሉ፡ ነገር ግን ራሱ የመቶ አለቃው እኔ ለዚህ የተገባሁ አይደለሁም ብሎ አሰበ። ጌታ ኢየሱስ በቃሉ ብቻ ቢያዝዝ በቂ እንደሆነ አወቀ። የመቶ አለቃው የጌታን ሥልጣን ተረዳ። ምክንያቱም እርሱም ራሱ ሥልጣን ስላለው ነው። ብዙ ጊዜ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ይኮራሉ። ጌታ ኢየሱስም በዚህ ሰውዬ እምነት በጣም ተደሰተ። አገልጋዩንም ፈወሰለት።

ይህ የመቶ አለቃ እውነተኛ ትሑት ነበር። ጓደኞቹንና ሽማግሌዎችን ላከ። ምክንያቱም ራሱ ከጌታ ኢየሱስ ጋራ ቀርቦ ለመነጋገር የሚገባው ስላልመሰለው ነው። በኋላ ግን ቀረበ፡ ከጓደኞቹ ጋላ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ጌታ ኢየሱስም በግል አነጋገረው፡ ማቴ.8:13።

ይህ የመቶ አለቃ ይሁዳዊ አልነበረም። የመጣው ከሮም ነበር። ጌታ የዚህን የሰውየ እምነት አየና ብዙዎች ከሩቅ ይመጣሉ፤ መንግሥተ ሰማያትም ይገባሉ አለ፤ ማቴ.8:11-12። እነዚህ ሰዎች ዛሬ ስለ ክርስቶስ እንዴት ሊሰሙ ይችላሉ? ጌታ ከሞት ከተነሣ በኋላ ሥልጣን ሁሉ የእርሱ እንደሆነ ተናግሯል። አገልጋዮቹን እንዲሄዱና እንዲመጡ ይነግራቸዋል፤ ስለ እርሱ በቅርብና በሩቅ ለሚገኙ ሰዎች ቃሉን እንድናደርስ አዝዞናል። የሚገባ ነው በማለት ሰዎች ይህንን የሮሜ መቶ አለቃ ታዘዙት። ስለ ክርስቶስ ምን ታስባለህ? ለፍቅርህና ለፈቃደኛነትህ የሚገባ ነው? እርሱ ብቻ የተገባ ነው፤ ራዕ.4:11፤ 5:12።

የናይን መበለት 7:11-17

ናይን ከቅፍርናሆም 32 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ ከተማ ነበረች። ጌታ ወደ ከተማይቱ በሚገባበት ጊዜ ሰዎች የሞተ ሰው ተሸክመው ከከተማይቱ ይመጡ ነበር። ጌታ ስለ ሞተው ሰውዬ እናት በጣም አዘነ። በመጀመሪያ ባሏ ሞተባት፤ አሁን ደግሞ አንድ ልጇን አጣች። ጌታም እንዳታለቅስ ነገራት፥ ኃዘኗንም ወደ ደስታ ለወጠው። ጌታ ኢየሱስ ራሱ በሰማይ ላለ አባቱ አንድያ ልጅ ነበር። በሞት አልፎ እንደገና እንደሚነሣ ያውቅ ነበር። እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ ሙታን ለማስነሣት ኃይል ነበረው። ወጣቱ ሰውዬም ተነሥቶ መናገር ጀመረ።

ጌታ ኢየሱስ ሌሎች ሁለት ሰዎች ከሞት አስነሥቷል። አንደኛዋ ወጣት ልጃገረድ ነበረች። ከሞት ባስነሣት ጊዜ የሚበላ እንዲሰጣት አዘዘ፤ 8:55። አለዛርን ባስነሣ ጊዜ የመገነዣ ልብሱን ፍቱትና ይሂድ ብሎ አዘዘ፤ ዮሐ.11:44። ሙትን ማስነሣት ለኃጢአተኛ ሕይወትን የመስጠት ምልክት ነው። ጌታ ሕይወት ሰጠን፤ የእግዚአብሔርን ቃልም ሊመግበን ይፈልጋል፤ ከአሮጌው ኑሮአችን እንድንላቀቅ ይፈልጋል። አዲስ ሕይወት ባገኘን ጊዜ ስለ አዳኛችን መናገርና መመስከር አለብን። ይህም እውነተኛ እንደገና መወለዳችንን ያረጋግጣል። እንድሪያስ ለወንድሙ ስለ ጌታ መሰከረለት፥ ፊልጶስም ለናትናኤል፤ ዮሐ.1:41 እና 45። የሰማሪያ ሴት ለከተማው ሰዎች ስለ ክርስቶስ ተናገረች፤ ዮሐ.4:29። አንተም እንዲሁ ማድረግ አለበህ።

ጌታ የሚከተሉትን ከሞት አስነሣ፡-

1. የናይን ወጣት፥ ተነሥቶ መናገር ጀመረ።

2. የቅፍርናሆም ልጃገረድ፥ ተነሥታ መብላት ጀመረች።

3. የቢታንያው አልአዛር፥ ተነሥቶ መሄድ ጀመረ።

የእግዚአብሔር ሰው የሞተውን የሚያስነሣው በእግዚአብሔር ኃይል ብቻ ነው። ኤልያስ ሕፃኑን እንደገና ወደ ሕይወት መለሰው፤ 1ነገ.17:22። ኤልሳም እንዲሁ አደረገ፤ 2ነገ.4:34። የናይን ሰዎች ይህ ወጣት እንደገና ሕያው መሆኑን ተመለከቱ፤ ኢየሱስም አንድ ታላቅ ነቢይ መሆን አለበት አሉ። ብዙዎች እንደ ግል አዳኛቸውና እንደ

ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ሊቀበሉት ዝግጁ አልነበሩም። ነገር ግን ያደረገው መልካም ነገር ዘናው በአገሩ በሙሉ ተሰራጨ።

ከአጥማቂው ዮሐንስ የመጡ መልእክተኞች
7፡18-35

አጥማቂው ዮሐንስ ከእግዚአብሔር የተላከ ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለሰዎች ሊመሰክር የመጣ ሰው ነው። እግዚአብሔር ምልክት ሰጠው። መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ወርዶ ይቀየል፤ ዮሐ.1፡61 33-34። በመጀመሪያ ብዙ ሰዎች ዮሐንስን ተከተሉት። ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ በድፍረት ነገራቸው። ሄሮድስንም እንኳ የወንድሙን ሚስት ማግባቱ ትክክል እንዳልሆነ ነግሮታል፤ 3፡19-20። ሄሮድስ ዮሐንስን ወደ እስር አስገባው።

ምናልባት ዮሐንስ የእስራኤል ንጉሥ ክርስቶስ ቶሎ ከእስር ቤት እንደሚያስወጣው ገምቶ ነበር። ጌታ ኢየሱስ አስደናቂ ነገሮችን እያደረገ መሆኑን ዮሐንስ ይሰማ ነበር። ጌታ ኢየሱስ መጥቶ ዮሐንስን ለምን ከእስር አላስፈታውም? በመጨረሻም ዮሐንስ ሁለት ሰዎችን ይመጣል የተባለው መሲህ አንተ ነህ ወይስ ሌላ ይጠብቁ? ብለው ጌታን እንዲጠይቁት ላካቸው፤ 7፡18-19። መልእክተኞቹም እንደተላኩት ጠየቁ። ጌታ ኢየሱስ በመጀመሪያ በሚያደርገው ነገር መለሰላቸው። ዮሐንስ ይመጣል ብሎ የመሰከረለት ለመሆኑ ማረጋገጫ ብዙ የታመሙ ሰዎችን ፈወሰ። ከዚያም መልእክተኞች ሄደው ያዩትን ለዮሐንስ እንዲነግሩት ላካቸው። ምስክሮች የሚያውቁትን መናገር አለባቸው፤ የሚያስቡትን ወይም አንድ ሰው ስለ ራሱ የሚናገረውን አይደለም። ኢሳይያስ መሢሁ ያደርጋል ያለውን ጌታም እነዚህን ነገሮችን በማድረግ ላይ ነው፤ ኢሳ.61፡1-2፤ ሉቃ.4፡18-19። ጌታ ኢየሱስ ዮሐንስን ከእስር አላስፈታውም፤ ነገር ግን ግመን እንዲያስችለው መልእክት ላከለት።

ጌታ ዛሬም እንደ ቀድሞው ነው። አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪ ጊዜያትን እንድናልፍ ይፈቅዳል። አንዳንድ ጊዜም ራሱ ለእኛ ያዘጋጅልናል። ከዚያም እንደሚወደን እንድናምን በእርሱ ላይ ያለንን እምነት ከፍ ያደርግልናል። እነዚህ ነገሮች በክርስትና ሕይወታችን እንድንጠነክር ያደርጉናል።

ጌታ ኢየሱስ ስለ ዮሐንስ የሚናገረውን መመልከቱ መልካም ነው፤ ዮሐ.7፡24-30። መልእክተኞቹ በሄዱ ጊዜ ሰዎችን ለምን ዮሐንስን ለማየት ሄዱ ብሎ ጠየቀ። ወደ በረሃ የሄዱት በቀላሉ የሚነቃነቅ ሰውን ለማየት አይደለም፤ ቁ.24። ቀጭን የሐር ልብስ የለበሰውንም ለማየት አይደለም፤ ቁ.25። ዮሐንስ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው፤ ሰዎችም በዚህ ተስማሙ። ነገር ግን ጌታ ዮሐንስን ከነቢይ የበለጠ ነው አላቸው። ለእግዚአብሔር ልጅ መንገዱን ሊያዘጋጅ የተላከ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው፤ ቁ.27፤ ሚል.3፡1። ከአጥማቂው ዮሐንስ የሚበልጥ እስካሁን አልተወለደም። ዮሐንስ አሁንም ከእርጌው ሥርዓት ውስጥ ነው። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ መሆን ለእኛ የበለጠ ይሻላል፤ ቁ.28።

ዮሐንስ ያጠመቃቸው ሰዎች ይህንን ሲሰሙ ደስ አላቸው። እግዚአብሔር ትክክለኛ ወይም ጻድቅ እንደሆነ ተስማሙ። እግዚአብሔር ፈሪሳዊያን በዮሐንስ እንዲጠመቁ ፈለገ። ኃጢአተኞች መሆናቸውን አልተስማሙም፤ 7፡29-30።

ስለዚህ ጌታ ለእነርሱ የሚናገረው ቃል አለ፤ 7፡31-35። እንደሚጫወቱ ልጆች ነበሩ አለ። ልጆች እንዲደሰቱ ይጫወታሉ። እነርሱ ግን እንዲያዝኑ ይጫወታሉ። ያደረጉትን ያድርጉ፥ ሌሎቹ ልጆች ከእነርሱ ጋር አይጫወቱም። ፈሪሳውያንም እንዲሁ ነበሩ። ዮሐንስ እንደ ኤልያስ ኖረ፤ ከሰዎች ችግር ደረሰበት፤ ማቴ.3፡4፤ ስለዚህ ሰዎች በውስጡ ዲያብሎስ አለበት አሉ። ጌታ ኢየሱስ እንደ ኤልያስ የሁሉም ወዳጅ ነበር። ስለዚህ ፈሪሳዊያን ብዙ ይበላል፥ ብዙ ይጠጣል ይላሉ። ክርስቲያኖች ሰውነታቸው እንደ መንፈስ ቅዱስ መኖሪያ መሆኑን ማስታወስ አለባቸው፤ 1ቆሮ.6፡19። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ካለ ራሳችንን ለመቆጣጠር እንችላለን፤ ገላ.5፡23። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚነግረን መስከር ኃጢአት ነው፤ ዘፍ.9፡21፤ 1ቆሮ.5፡11። ያለልክ ከመብላትም መቆጠብ አለብን።

ፈሪሳዊያን ደግሞ ጌታ የኃጢአተኞች ወዳጅ ነበር ይላሉ፤ 7፡34። ይህም እውነት ነበር፤ ግሩም እውነት ነው። ነገር ግን ፈሪሳዊያን ይህንን አልወደዱም፤ 5፡30። ጌታ ኢየሱስ ብልሆች የሚያደርገው እንደሚገባቸው ያውቅ ነበር፤ 7፡35። እውነትን ከእግዚአብሔር የተማረ ማንኛውም ሰው ወደ ጌታ ኢየሱስ ይመጣል፤ ዮሐ.6፡45። በልጁ በኩል ካልሆነ በስተቀር አብን የሚያውቀው ወይም ወደ እርሱ የሚመጣ የለም፤ ማቴ.11፡27፤ ዮሐ.14፡6።

ፈሪሳዊው ስምዖን 7፡36-50

አብዛኛዎቹ ፈሪሳውያን ጌታ ኢየሱስን አይወዱትም፤ ነገር ግን ከእነርሱ ውስጥ አንዱ ቢያንስ አብሮት እንዲበላ ጠየቀው፤ 5፡21፤ 6፡2 እና 7። ጌታ ወደ ስምዖን ቤት ሄደ፤ ነገር ግን አሁንም የኃጢአተኞች ወዳጅ መሆኑን አላይቷል። እንዲት ሴትም ወደ ስምዖን ቤት መጣች። ከኃጢአቷ ከመመለሷ በፊት የታወቀች ኃጢአተኛ ነበረች። ጌታ ኢየሱስን አወቀችው፥ ወደደችውም። በኃጢአቷም ተፀፀተች፥ እንባዋንም በጌታ እግር ላይ ታፈሰ ነበር። እግሩንም በራሷ ፀጉር አደረቀችው፤ ከዚያም በእግሩ ላይ ሽቶ አፈሰሰች።

ጌታ ኢየሱስ ከኃጢአቷ የተመለሰች ኃጢአተኛ እንደነበረች አወቀ። ወደ ጌታ እንደመጣችና እንደተቀበላት ስምዖን ይመለከት ነበር። ስምዖንም ስላለፈው ኃጢአቷ ብቻ ያስብ ነበር። ፈሪሳዊያን በሚያድነው፥ ይቅር በሚለውና ኃጢአተኞችን በሚለውጠው የእግዚአብሔር ፀጋ አላመኑም ነበር። ስምዖን ጌታ ኢየሱስ ነቢይ እንዳይደለ ብሎ ወሰነ።

እርሱ ነቢይ ነበር፤ ከነቢይም የበለጠ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ስምዖን በልቡ ምን እንደሚያስብ አወቀ። የሚነግረው ነገርም ነበረው። ስምዖን አዳመጠ፤ 7፡40። በመጀመሪያ ዕዳ ያለባቸውን የሁለት ሰዎች ታሪክ ሰማ። አንደኛው ከሁለተኛው ካለበት ዕዳ በአሥር እጥፍ ያህል ይበልጥ ነበረበት። ዲናር ለአንድ ቀን ሙያ የሚከፈል ደሞዝ

ነው፤ ማቴ.20:2። ሁለቱም የሚከፍሉት ስለሌላቸው ሰውየው ማራቸው። ብዙ ይቅር የተባለ ብዙ ደግሞ መውደድ ይወዳል ብሎ ስምዖን በዚህ ተስማማ። ከዚያም ጌታ ኢየሱስ ታሪኩን አስረዳው። ፈሪሳዊው የሌትዮዋን ያህል ትልቅ ኃጢአተኛ እንደሆነ አያምንም። እርግጥ ስምዖን ብዙ ፍቅር ለጌታ አላሳየውም። ለእግሩ ውኃ፣ ለፀጉሩም ዘይት እንኳ አልሰጠውም። ሴትዮዋ ግን ለአዳኟ እውነተኛ ፍቅር አሳይታለች።

የዚህች የሴትዮ ኃጢአት ይቅር ተብሎላታል፤ ምክንያቱም አምናለችና። ጌታን ወደደችው፤ ምክንያቱም ኃጢአቷን ይቅር ስላላት፤ 7:47። ጌታ በግልጽ ኃጢአቷ ይቅር እንደተባለላት ነገራት። ይህ ለማንኛውም ኃጢአተኛ ጣፋጭ መልእክት ነው። እርግጥ የፈሪሳዊው ወዳጆች ጌታ ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር ለማለት ሥልጣን እንዳለው አላመኑም፤ ቁ.49፡ 5:21። ነገር ግን ሴትዮዋ በእምነት ብቻ እንደዳነች ነገራት። በልቧም ውስጥ ሰላም ሰፈነ፤ ሮሜ 5:1።

በዚህ ምዕራፍ ስለ ፍቅርና እምነት በመጠኑ እንማራለን። የሮሜ መቶ አለቃ ለአገልጋዩ ፍቅሩን አሳየ፤ 7:1-2። እንዲሁም ለቅፍርናሆም ሰዎች፥ ቁጥር 3-5። ጌታ ኢየሱስም እምነቱን በማየቱ ደስ አለው፤ ቁ.9። የናይን መበለት አንድ ልጇን ወደደች፤ ቁ.11-12። ጌታም በእርሱ ላይ እምነት እንዳላት አወቀ። ልጇን ከሞት አስነሥቶ እንደገና መልሶ ሰጣት። የዮሐንስ እምነትና ፍቅር ለጌታ በደከመ ጊዜ ሊያጠነክረው መልእክት ላከ። የከተማይቱ ሴት ለጌታ ኢየሱስ እምነትም ፍቅርም ነበራት። ሌሎች ሦስት ነገሮች ይቀራሉ። እነርሱም፡- እምነት፥ ተስፋና ፍቅር ናቸው። ከእነዚህ ሁሉ ግን ፍቅር ይበልጣል፤ 1ቆሮ.13:13። ስለ አስደናቂው አዳኛችን ገና ብዙ እንማር፤ መንፈስ ቅዱስ የበለጠ እንድንወደው ይረዳናል።

ከእነዚህ ነገሮች በኋላ ስለ ሁለተኛው ጉዞ ብዙ እናነባለን። ጌታ ኢየሱስ ብዙ ከተሞችንና መንደሮችን ጐበኘ፤ 8:1-3። አሥራ ሁለቱም ሐዋርያት እንዲሁም ብዙ ሴቶች ከእርሱ ጋር ነበሩ። ጌታ ከሞት ከተነሣ በኋላ የታየው ማሪያም መግደላዊት የመጀመሪያዋ ሰው ነበረች፤ ዮሐ.20:16። ነገር ግን ዮሐና ደግሞ አይታዋለች፤ ሉቃ.24:10፤ ማቴ.28:9። የዮሐና ባለቤት ከፍተኛ መኰንን ነበር፤ እርሷና ሌሎችም ገንዘባቸውን ለጌታ ሥራ አዋጡ። ይህም ገንዘብ ጌታና ሐዋርያቱ የሚያስፈልጋቸውን ለመግዛ ይውል ነበር።

በባሕር አጠገብ ያስተማረው 8:4-21

ስለ ዘር ዘሪው ምሳሌ እንመለከታለን፤ 8:4-15። ስለ መብራቱ የተሰጠ ትምህርት ቁ.16-18፤ እንዲሁም የጌታ ቃል ለእናቱና ለወንድሞቹ ቁ.19-21። በጣም ብዙ ሰዎች የጌታን ቃል ለመስማት መጡ፤ ነገር ግን ብዙዎች ቃሉን ይሰማሉ፥ ፍሬም አያፈሩም ብሎ አስጠነቀቀ። አራት ምክንያቶች አሉ፡- አራት የተለያዩ የመሬት ዓይነቶች አሉ፤ አራት የተለያዩ ሰዎችም አሉ፤ 8:5-8፤ ቁ.9-15።

ይህ ምሳሌ ምን ማለት ነው? የራሱ ደቀ መዛሙርት እንኳ መጀመሪያ አልገባቸውም ነበር፤ ነገር ግን አስረዳቸው፥ 8:9-10። ሌሎች የሰሙት እንዲገባቸው ከፈለጉ በጣም

በነገሩ ማሰብ ነበረባቸው። በሌላ ምሳሌ ዘሪው የሰው ልጅ እንደሆነ እንማራለን፤ ማቴ.13:37። እዚህ ላይ ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ሉቃ.8:11። ሁሉን አስተውል።

1. አንዳንዱ ዘር በመንገድ ዳር ወደቀ። ሰዎች ረገጡት፤ ወፎችም ለቀሙት። አድጐ ፍሬ ሊሰጥ አልቻለም። ይህም ቃሉን እንደሚሰሙ ሰዎች ነው፤ ነገር ግን ሰይ ጥንና መናፍስቱ ይህንን ዘር ይነጥቃሉ። ሰይጣን ይህንን ለማድረግ ይራወጣል። ማንም ቃሉን አምኖ እንዲድን አይፈልግም።

2. አንዳንዱ ዘር በጭንጫ ላይ ወደቀ። ቦታው በቂ አፈር አልነበረውም። መሬቱ በቂ አፈር ስለሌለው ዘሩ ሥር ሊሰድ አልቻለም። ቶሎ ይበቅላል፤ ዝናቡንም ሊይዝ የሚችል በቂ አፈር የለም። ቡቃያውም ቶሎ ይጠወልጋል፤ በኋላም ይሞታል። ይህ ቃሉን በደስታ እንደሚቀበሉት ሰዎች ነው። ነገር ግን አይገፉበትም። በተፈተኑ ጊዜ ወዲያው ይክዳሉ፤ ምንም ዓይነት ፍሬ አያፈሩም።

3. ሌላው ዘር በእሾህ መሐከል ወደቀ። ዘሩም ማደግ ጀመረ፤ ነገር ግን እሾሁም አደገ። እሾሁም መልካሙ ዘር አድጐ ፍሬ እንዲሰጥ አላስቻለውም። ብዙ ሰዎች ቃሉን የሚቀበሉ እናያለን። ነገር ግን እንደፈለጋቸው የራሳቸውን ኑሮ በዚህ ዓለም ይኖራሉ። ድሆች ከሆኑ ብዙ ጭንቀት አለባቸው። ለእግዚአብሔርም ምንም ፍሬ አያፈሩም። ሐብታም ከሆኑ ለገንዘባቸው ይጨነቃሉ ፍሬም አያፈሩም። ብዙዎች የዚህን ዓለም ደስታ ይፈልጋሉ። አብን አያስደስቱም፤ ፍሬም የላቸውም። የዚህ ዓለም ነገሮች ጠምደውን ፍሬ ሳናፈራ እንዳንቀር እንጠንቀቅ።

4. አንዳንዱ ዘር በጥሩ መሬት ላይ ወደቀ፤ ለዘሪውም ብዙ ፍሬ አፈራለት፤ ከዘራው መቶ እጥፍ አገኘ። አንዳንዱ የመሬቱ ክፍል ሰላሳ ወይም ሰላሳ ጊዜ እጥፍ አፈራ፤ ማቴ.13:23። ቢሆንም ከፊቶቹ ሦስት ዓይነት መሬቶች በጣም ይሻላል። የእግዚአብሔርን ቃል በእውነት ስለ አመኑት ሰዎች ምሳሌው ነው። አንዳንዶች ከሌሎች የበለጠ ፍሬ ያፈራሉ፤ ነገር ግን ሁሉም ያፈራሉ። ይህ ፍሬ ምንድነው? የመንፈስ ፍሬን ማፍራት ማለት ክርስቶስን መምሰል ነው። እስካሁን ከኖሩት ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ራሱ ከፍተኛውን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ደግነት፥ በጐነትና ታማኝነት አሳይቷል፤ 5:22-23። ከክርስቶስ ጋር ሕብረት ካለን እርሱን እየመሰልን እንሄዳለን፤ አብም ይከበራል፤ ዮሐ.15:7-8።

ጥሩ ዘር በጥሩ መሬት ላይ አድጐ ራሱን የመሰለ ብዙ ፍሬ ያፈራል። ስለዚህ በፀጋ የሚያድግ ክርስቲያን ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ያመጣል፤ ክርስቲያናችንም ይሆናሉ። ጳውሎስ ወደ ሮም ሄደ። ፍሬ ሊያፈራና ሰዎችን ወደ ክርስቶስ አመጣለሁ አለ፤ ሮሜ 1:13። ጌታ እኛን መረጠን፤ ሄደንም ለዘለዓለም የሚኖር ፍሬ እንድናፈራ ሾመን፤ ዮሐ.15:16።

ነገር ግን አንዳንድ ክርስቲያኖች ስለ ጌታቸውና አዳኛቸው ለሌሎች ለመንገር ይፈራሉ። ስለ ጌታ ለሌሎች በመመስከር መብራታችን በሰዎች ፊት መብራት እንዳለበት ጌታ አስተምሯል፤ ሉቃ.8:16-18። በጨለማ ውስጥ ነበርን፤ ክርስቶስ ግን ብርሃን

ሰጠን። ያንን መብራት መደበቅ የለብንም። አዲስ ሕይወትህን ሚስጢር አድርገህ አትያዘው። ምንም ቢቆይ አንድ ቀን ስለ አንተ ያውቃሉ። የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ መቀበል አስፈላጊ ነው። ይህንን እውነት የማይቀበሉ ሰዎች በኋላ አያገኙትም፣ ቁ.18። እነዚህ የጌታ ኢየሱስ የምር ቃሎች ናቸው፣ እንድናስብበትም ማድረግ አለባቸው።

እነዚህ ቃሉን ሰምተው የሚፈጽሙት የእርሱ ወንድሞች ይባላሉ፣ 8:19-21። የጌታ እናትና ወንድሞቹ መጡ፣ ነገር ግን ከሰዎቹ ብዛት የተነሣ ወደ እርሱ ሊቀርቡ አልቻሉም። የወንድሞች ስም በማቴዎስ ይገኛል፣ ማቴ.13:55። በዚህን ጊዜ ገና በእርሱ አላመኑም ነበር፣ ዮሐ.7:5። ነገር ግን በኋላ አመኑ፣ የሐዋ/ሥራ 1:14። ሁለቱም ያዕቆብና ይሁዳ ለክርስቲያኖች መልእክት ጽፈዋል። ነገር ግን ራሳቸውን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች ብለው ይጠራሉ፣ ያዕ.1:1፣ ይሁዳ 1።

አንዳንድ ነገሥታትና መሪዎች ለቤተሰቦቻቸውና ለዘመዶቻቸው ልዩ ትኩረት ይሰጣሉ። ጌታ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሚያደርጉ ለእነዚያ ክብር ሰጠ፣ 8:21፣ ማቴ.12:50። ጌታ ኢየሱስ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ሕግ ጠበቀ። ሕጉ እናትና አባታችንን ማክበር እንዳለብን ይናገራል። ጌታ ሊሞት በተቃረበ ጊዜ በጣም ለሚወደው ደቀ መዝሙሩ ዮሐንስ እናቱን እንዲንከባከብለት ጠየቀው፣ ዮሐ.19:27።

የእግዚአብሔር ቃል የተቀበሉ ወንድሞች ይባላሉ። ምክንያቱም እንደ ልጁ ናቸው፣ ዕብ.2:11። እርሱ ሁልጊዜ የአባቱን ፈቃድ አደረገ። በሌላ በኩል ጌታን ወንድማችን ብለን ልንጠራው አንችልም። መምህርና ጌታ ብለን ልንጠራው ግን እንችላለን፣ ዮሐ.13:13።

አራት ተአምራት 8:22-56

የገሊላ ባሕር ትንሽ ሐይቅ ነው። 22 ኪሎ ሜትር ርዝመትና 12 ኪሎ ሜትር ስፋት አለው። በስተምሥራቅ በኩል ረዥም ተራራዎች አሉ፣ ማዕበልም በድንገት ሊመጣ ይችላል። በአጭር ጊዜ ውስጥ በውኃው ላይ ያሉትን መርከቦች ሊገለብጥ የሚችል ኃይለኛ ነፋስ ሊመጣ ይችላል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉም ሰዎች ያላቸው ስሜት እርሱም ነበረበት። ወደደ፣ ማር.10:21፣ ይራራል፣ ማር.1:41፣ አዝኗል፣ ማር.14:34፣ ተራበ፣ ማር.3:5። የሆነ ሆኖ ፈርቶ አያውቅም። በአባቱ አጥብቆ መተማመን ነበር። በሐይቁ ውስጥ ማዕበል ተነሥቶ ወደ ጀልባይቱ ውኃ መግባት ጀመረ። ደቀ መዛሙርቱ ፈሩ። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ በጀልባይቱ ውስጥ ከበስተኋላ ተኝቶ ነበር። አባቱ በሰላም እንደሚጠብቃቸው ያውቅ ነበር። በመጀመሪያ ነፋሱንና ማዕበሉን ፀጥ እንዲል አዘዘ፣ 8:24፣ ማር.4:3። ከዚያም ደቀ መዛሙርቱን ስለ ትንሽ እምነታቸው ጠየቃቸው፣ ቁ.25። የእግዚአብሔር ልጅ በተናገረ ጊዜ ነፋሱና ማዕበሉ ታዘዙት። ደቀ መዛሙርቱና ሌሎችም በሌላ ጀልባ ውስጥ ያሉት ዳኑ፣ ማር.4:36።

በማንኛውም አደጋ ጊዜ መፍራት ሳይሆን ማመን መማር አለብን፤ መዝ.56፡3። ከተጨነቅንና ከፈራን በሚወደን እግዚአብሔር አልተማመንም ማለት ነው። «እምነትህ የት አለ?» እምነትህን በእግዚአብሔር ልጅ ላይ አጥብቅ፤ አትፍራም።

በዚህ ታሪክ ውስጥ የሰይጣንን ኃይል እንመለከታለን። ሰይጣን በአየር ያሉት ኃይላት አለቃ ነው፤ ኤፌ.2፡2። ጌታ ኢየሱስ ሕፃን ሆኖ በነበረበት ጊዜ ሰዎች እንዲገድሉት የመራቸው ሰይጣን ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፤ ማቴ.2፡16፤ ትልቅ ከሆነም በኋላ እንዲሁም፤ ሉቃ.4፡29፤ ዮሐ.8፡59። በማዕበሉም ጊዜ የሰይጣን እጅ እንዳለበት አያጠራጥርም። የጌታ ኃይል ግን ከሰይጣን ይበልጣል። ለጌታ የሞቱ ጊዜ አልቀረበም ነበር።

በቀረው ክፍል ጌታ ሦስት ሰዎችን እንደረዳ እናነባለን። ክርስቶስ ታላቅ ሰው ነበር፤ ግን ሰው ብቻ አልነበረም። እርግጥ አዋቂ ሰው ሊፈውስህ ይችላል፤ ነገር ግን ክርስቶስ እነዚህን ሰዎች የፈወሳቸው በእግዚአብሔር ኃይል መሆኑን እርግጠኞች ነን። ሰው ይህንን ነፋስና ማዕበል ሊያቆም ይችላል ብሎ ማንም አይገምትም። በእግዚአብሔር ካመንን ማንም ሰው ሊያደርገው የማይችለውን ታላቅ ነገር ለማድረግ እንደምችል በእርግጥ ማመን እንችላለን።

አጋንንት ያደሩበት ሰው 8፡26-39

አጋንንት በሰው ውስጥ ገብተው ሕይወቱን ለመቆጣጠር የሚሞክሩ ርኩስ መናፍስት ናቸው። ጌታ በገሊላ ባሕር በሚያልፍበት ጊዜ ብዙ አጋንንት የያዘው ሰው ተገናኘው። ይህ ሰው ልብስ አልለበሰም፤ የሚኖረውም ሰዎች ሙታንን በሚቀብሩበት ዋሻ ውስጥ ነበር። የከተማው ሰዎች ይህንን ሰውዬ በሰንሰለት አስረው ጠባቂ አቁመውለት ነበር፤ ነገር ግን አምልጦ መናፍስት ወደ ምድረ በዳ ወሰዱት።

ጌታ ኢየሱስ ይህንን ሰው አየው፤ አጋንንቱንም ከሰውየው እንዲወጡ አዘዘ። ሰውየው በመናፍስቱ ቁጥጥር ሥር ነበር፤ ጌታንም እንዳይቀጣው ተማፀነው፤ 8፡28-29። ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አወቀ፤ እርሱንም መታዘዝ ነበረበት። ስሙ ለጌዎን ይባላል አለ፤ ለጌዎን ብዙ ሺህ የሮሜ ወታደሮች ቡድን ነው። ስለዚህ ብሷውየው ውስጥ ብዙ ርኩስ ማናፍስት ነበሩ። መናፍስቱ ጌታን ወደ ጥልቁ ጉድጓድ እንዳይሰዳቸው ጠየቁት። ጥልቁ ጉድጓድ መጨረሻ የሌለው ታላቅ ጉድጓድ ነው። በመጨረሻው ቀን ሰዎችን ለማስቸገር መናፍስት ከጥልቁ እንደሚወጡ እናነባለን፤ ራዕ.9፡1-11። መናፍስቱ ጌታን በተራራው ላይ ወደሚበሉት አሳማዎች ውስጥ እንዲገቡ ጠየቁት። መናፍስቱም ወደ አሳማዎቹ ገቡ። አሳማዎችም ቁልቁል ሮጠው ወደ ባሕር ገብተው ሞቱ።

በዚህ ሁሉ ጌታ ሰዎችን ሊያስተምር ፈለገ። ሰውየውን ከአጋንንቱ ኃይል አዳነው። ይህ ሰው ከብዙ አሳማዎች ይልቅ ይበልጣል። አሳማዎችም እንኳ እነዚህን አጋንንት ሊቋቋሟቸው አልቻሉም። ሰዎች አእምሮአቸውን ከፍተው መናፍስትን እንዳይሳቡ መጠንቀቅ አለባቸው። ጌታ እነዚህ አጋንንት በሰው ውስጥ እንዲቆዩ አልፈለገም። ነገር

ግን ሰይጣን አሳማዎች እንዲገቡ ተስማማ። ጸሎታችንን በእምነት ለእግዚአብሔር ክብር ስናቀርብ የቱን ያህል የበለጠ ይሰማን?

የተጣለው ሰዎች አጋንንቱ ከሰፈሩበት ከዚያ ሰው ይልቅ ለአሳማዎቹ አሰቡ። ሰዎች መጡ፣ ሰውየውንም በሰላም በጌታ ኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጦ አዩ። ልብስ ለበሰ፣ እንደ ሰው ግሰብም ጀመረ፤ 8:35። የከተማው ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ይህንን ሰውየ ስላዳነው አላመሰገኑትም። በአፀፋው ግን ከአጠገባቸው እንዲሄድ ጠየቁት። ይህም አንድ ሰው ለጌታ ኢየሱስ ከሚናገረው መጥፎ ነገር የከፋው ነበር፤ 5:8። ነገር ግን እነርሱ ተናገሩ፣ ጌታ ኢየሱስም ከአጠገባቸው እንዳሉት ሄደ።

ሰውዬው ይዘውት የነበረው ሰውየ ከእርሱ ጋር መሄድ ይችል እንደሆነ ጌታን ጠየቀው። ይህ መልካም ጸሎት ነው። ጌታ ኢየሱስን ብዙ ስንወደው ከእርሱ ጋር ለመሆን የበለጠ ደግሞ እንፈልጋለን። ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ወደደን፤ ከእኛም ጋር ሊሆን ይፈልጋል። ታዲያ ለምን በዚህ ዓለም ተወን? በተመሳሳይ ምክንያት ይህንን ሰውየ ከእርሱ ጋር እንዲሄድ አላደረገም። ጌታ ሰውየውን እግዚአብሔር ያደረገለትን ለሌሎች እንዲመሰክር ይፈልጋል፤ 8:39። ሰውየውም ለጌታ ታዘዘ። ለከተማውም ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ያደረገለትን ተናገረ። እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን።

የኢያኢሮስ ልጅና ለአሥራ ሁለት ዓመት የታመመች ሴት 8:40-56

ጌታ ሐይቁን እንደገና አቋርጦ መጣ። ሰዎቹም ተቀበሉት። እዚህ ላይ በሞትና በበሽታ ላይ የክርስቶስን ኃይል የሚያሳይ ሁለት አስደናቂ ሥራዎችን እንመለከታለን። በመጀመሪያ ኢያኢሮስ የይሁዳዊያን ገዢ ሆነ። መጥቶ አንዲት ሴት ልጁን ያድንላት እንደሆነ ጌታን ጠየቀው። ይህች ሴት ልጅ አሥራ ሁለት ዓመቷ ነበር፤ ልትሞትም ተቃርባለች። ጌታ ወደ ኢያኢሮስ ቤት በመሄድ ላይ እንዳለ የታመመች ሴት ወደ እርሱ መጣች። እርሷም ለ12 ዓመት ያህል ታምማ ነበር፤ ብዙ ዶክተሮችም ሊያድኗት አልቻሉም ነበር። ሕመሟም እየባሰባት ሄደ። ከጌታ በስተጓላ መጥታ የነጠላውን ጫፍ ነካች፣ ወዲያው እንደፈወሳት ራሷ አወቀች፤ ማር.5:26-29። ለጌታም ሆነ ለሌላ ለማንም አልተናገረችም ነበር።

ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ ምን እንደተደረገ ያውቅ ነበር። እርሱም ለዚህች ሴት የሆነውን በሰዎች ፊት እንዳዳናት ብትመሰክር ጥሩ እንደሆነ አወቀ፤ ሮሜ 10:9። ግን እንደተለመደው ጠየቀ፤ ሁሉም ግን አናውቅም አሉ። ጴጥሮስም ሰዎች ሁሉ በጌታ ዙሪያ ተሰብስበ ነበዋል አለ። ጌታ አንድ ሰው በእምነት እንደነካውና የመፈወስ ኃይል ከእርሱ እንደወጣ አወቀ። በመጨረሻም ሴትየዋ ሁኔታውን እስከመጨረሻ ለመደበቅ እንዳልቻለች አወቀች፤ ስለዚህ ያደረገችውን ተናዘዘች። በቁ.17 ጌታ ኢየሱስ ያስተምር የነበረው ይህ ነበር። በሰላም እንድትሄድ ነገራት፤ ቁ.48።

በጌታ ዙሪያ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ነበር፤ ነገር ግን አንድ ሰው እውነተኛ እምነት እንዳለው አወቀ። ዛሬም እንዲሁ ነው። ብዙ ሰዎች ክርስቲያኖች ነን ይላሉ፤ ነገር ግን ጌታ እውነት በእርሱ የሚያምኑትን ያውቃቸዋል፤ ዮሐ.10:27።

ጌታ ይህችን ሴት ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል በሚያነጋግርበት ጊዜ በመሃከሉ የኢያኢሮስ ሴት ልጅ ሞተች። ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ሳይረዳት ጊዜ እንዳለፈበት ገመቱ፤ ነገር ግን ጌታ ለልጅቷ አባት፡- ልጅህ ትድናለች አለው። እቤትም በደረሱ ጊዜ ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ያዕቆብን ብቻ ከአባትየውና ከእናትየዋ ጋር ወደ ውስጥ እንዲገቡ ፈቀደ። ጓደኞችዋና ዘመዶችዋ በኃዘን ያለቅሱ ነበር። ወዲያውም ጌታ ልጅትዋ እንቅላፍታለች እንጂ አልሞተችም ባለ ጊዜም ሁሉም ሳቁ። ጌታም ወደ ውጪ እንዲወጡ አደረገ፤ ማር.5:40። ትንሿን ልጃገረድ እንድትነሣ ነገራት፤ ሕይወቷም ተመለሰ። ቤተሰቦችዋንም የምትበላውን እንዲሰጧትና ያደረገውን ግን ለማንም እንዳይነግሩ ነገራቸው።

ጌታ ኢየሱስ እንቅላፍታለች እንጂ አልሞተችም ለምን አለ? በሰዎች ዓይን ልጅቷ በእርግጥ ሞታ ነበር። መንፈሷም ከእርሷ ተለይቷል። ሰውነት ያለመንፈስ የሞተ ነው፤ ያዕ.2:26። የእግዚአብሔር ልጅ በተናገረ ጊዜ ግን መንፈሷ ተመለሰ፤ 8:55። በክርስቶስ በኩል በሞት ላይ ድል አድርገናል፤ 1ቆሮ.15:54-57። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የአማኝ ሞት እንቅልፍ ይባላል፤ ዮሐ.11:11-13፤ የሐዋ/ሥራ 13:36፤ 1ቆሮ.15:51፤ 1ተሰ.4:14። ሞት የአማኝ ጓደኛ እንጂ ጠላት አለመሆኑን ማወቅ በጣም ጥሩ ነገር ነው። አማኝ በሞተ ጊዜ ከጌታ ጋር ለመሆን ይሄዳል፤ ፊል.1:23። ጌታ አለ «እኔ ትንሣኤና ሕይወት ነኝ» ዮሐ.11:25።

ጌታ ልጅቷን ከሞት ባስነሣበት ወቅት ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ውስጥ ሦስቱ ብቻ እቤት ውስጥ ከእርሱ ጋር ነበሩ። እነዚህ ሦስት ሐዋርያት ጌታ በክብር በተገለጠበት ጊዜ በተራራው ላይ አብረውት ነበሩ፤ 9:28። በኋላም ለመጸለይ ወደ አትክልት ቦታ ሲሄድ እነዚሁኑ ሦስቱን ይዞ ሄደ፤ ማቴ.26:37። ጌታ በጣም ለሚቀርቡት ልዩ ደስታ ይሰጣቸዋል።

በእርሱ ባመንን ጊዜ አዲስ ሕይወት ይሰጠናል። አዲስ የመንፈስ ምግብ እንደሚያስፈልገን ያውቃል፤ ቁ.55። ይህም በመጀመሪያ ለሕፃን ወተት እንደሚሰጠው ዓይነት ነው፤ 1ጴጥ.2:2። በእደግን ጊዜ ግን ጠንካራ ምግብ ለመብላት እንችላለን፤ ዕብ.5:14። የእግዚአብሔርን ቃል በየቀኑ መመገብ ያስፈልገናል። በመጀመሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀላል እውነት እንማራለን፤ በኋላም የእግዚአብሔርን ቃል ጥልቅ እውነት እናውቃለን።

በዚህ ምዕራፍ አንዳንድ ታማኝ ሴቶች ለጌታ ሥራ እንዲውል ገንዘባቸውን ሲሰጡ እናያለን። የእግዚአብሔር ልጅ በእርግጥ የእነርሱ እርዳታ አያስፈልገውም። ነገር ግን እንደሚወዱት መመልከቱ በጣም አስደስቶታል። በቀረው የምዕራፍ ክፍል ሌሎች እምነት እንደነበራቸው እንመለከታለን። ነገር ግን ጌታን የተረዱት አይመስልም። ለቤተሰቡ የተለየ ትኩረት ያደርጋል ብለው አስበው ነበር፤ 8:20። በነፋስና በማዕበል ላይ ኃይል ስለነበረው የራሱ ደቀ መዛሙርት የተደነቁ ይመስላል፤ ቁ.25። የጌራሴኖን ሰዎች ከአጠገባቸው እንዲሄድ ጠየቁት፤ ቁ.37። ጴጥሮስ እንኳ ማን እንደነካው መጠየቅ እንደሌለበት አስቧል፥ ቁ.45። በኢያኢሮስ ቤት የነበሩ ሰዎችም ሳቁበት። ስለእርሱ

ብዙ ባነበብን ቁጥር ጌታ ኢየሱስን የበለጠ እንረዳዋለን። አንተም ካወቅኸው ትወደዋለህ፤ ኤር.9:24።

ጌታ አሥራ ሁለት ሐዋርያቱን ላከ 9:1-9

በዘጠነኛው ምዕራፍ ጌታ ለደቀመዛሙርቱ ልዩ ትምህርት እንዳስተማረ እንመለከታለን። አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮች ተፈጽመዋልና በጥንቃቄ መመርመር አለብን።

የአሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ስም አንብበናል፤ 6:13-16። አሁን ጌታ ኢየሱስ እንዲሰብኩና እንዲፈውሱ ላካቸው፤ 9:1-2። ጌታ ነፍሱንና ማዕበሉን በተቆጣጠረ ጊዜ ኃይሉን አሳይቷል። ደግሞም አጋንንትን በቁጥጥር ሥር አዋለ፤ የታመመች ሴት ፈወሰ፥ ልጃገረዲቱን ከሞት አስነሣ። ከዚህ ኃይሉ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው። ለመንገዳቸው የሚሆን ምግብ ወይም ገንዘብ፥ ትርፍ ልብስ እንኳ እንዳይዙ ነገራቸው። ወደ እስራኤል ሕዝቦች መሄድ ነበረባቸው፤ ማቴ.10:5-6። በዚያም በጌታ ኢየሱስ የሚያምኑና ሐዋርያቱንም ወደ ቤታቸው የሚቀበሉዋቸው ነበሩ፤ ቁ.4። ግንም እዚያ ባይቀበላቸው በከተማይቱ መቆየት የለባቸውም፤ ቁ.5። ስለዚህ ሁለት ሁለት እየሆኑ ሄዱ፤ ማር.6:7።

ጌታ ኢየሱስ ዛሬም ደቀ መዛሙርቱን ለመላክ ሥልጣን አለው፤ ሁላችንንም ወንጌልን እንድንሰብክ አዝዞናል፤ ማር.16:15። አንዳንዶቹን ቤታቸውን ትተው ጊዜያቸውን ሁሉ ለዚህ ሥራ እንዲያውሉ ጠራቸው። እነዚህ በቤት የሚቆዩት የሄዱትን መርዳት አለባቸው፤ ለዕለት ተዕለት ፍላጐታቸው ግሚያ ገንዘብ መስጠት አለብን። እነዚህ ሰባኪዎች ወደ ኃጢአተኞችና ለወንጌል ፍቅር ወደሌላቸው ሰዎች ይሄዳሉ። ያልዳኑ ሰዎች ለጌታ ሥራ ይረዳሉ ብለን አንጠብቅም፤ በእርግጥም የእነርሱን ዕርዳታ መቀበል አይገባንም፤ 3ዮሐ.7። በዚህ መንገድ ከሐዋርያት የተለየን ነን፤ እኛ ወደ ኃጢአተኞች ተልከናል፤ እነርሱ ግን ወደ ራሳቸው ሰዎች ሄዱ። ሌላው ነገር ደግሞ ጌታ ኢየሱስ እንደ ሰው ወደሚሄዱበት ቦታ ሁሉ ከሐዋርያቱ ጋር ሊሆን አይችልም። አሁን ግን ቀኑን ሁሉ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቶልናል፤ ማቴ.28:20።

የገሊላ ገዢ ሄሮድስ ስለዚህ ነገር ሁሉ ሰማ። አጥማቂው ዮሐንስ ከሞት ተነሥቶ ይሆን ብሎ ተደነቀ፤ 9:7-9፤ ማቴ.14:2። ሄሮድስ ሚስቱን ሄሮድያዳን ለማስደሰት የዮሐንስን አንገት ቆረጠ፤ ማር.6:14-29። ሄሮድስ የጌታ ኢየሱስን አስደናቂ ሥራዎች ለመግለጽ እግዚአብሔር ዮሐንስን ከሞት አስነሣው እያለ ለማስረዳት ሞከረ። እግዚአብሔር ዮሐንስን አስነሥቶት ቢሆን ኖሮስ ሄሮድስ እርሱን በመግደሉ አስቸኳይ ፍርድ እንደሚደርስበት በማወቅ ይፈራ ነበር። በዚያ ፋንታ ኢየሱስን ለማየት ፈለገ። በመጨረሻም ሄሮድስ አየው፤ 23:8። ነገር ግን አሁንም በእርሱ አላመነም።